

ኢህአዴግ፣ ምርጫ 2002 እና የወ/ሪት ብርቱካን ጉዳይ

በግርማ ካሳ (ከቺካጎ)

4

የሕዝብና የአገር ክብር ከየትኛውም አመለካከትና ቁሳዊ እሴት የላቀ ነው

2

«እንደ አመት በዓል የተከበረው ብላቴና!»

አቤ ቶኪቻው

10





# አውራምባ ታይምስ

ለመረጃ ቅርብ ይሁኑ


2ኛ ዓመት ቁጥር 86 ጥቅምት 10 ቀን 2002 ዋጋ 3.50 ብር


# ባልተደላደለ ሜዳ፣ ወደ ምርጫ 2002



4ኛው አገር አቀፍ ምርጫ ሲካሄድ የቀሩት ሰባት ወራት ብቻ ናቸው:: ይህ ደግሞ ምርጫ ከሚጠይቃቸው የአደረጃጀት፣የእጩ አቀራረብና የቅስቀሳ ዝግጅቶች አንጻር በእጅጉ አጭር ነው:: የቀድሞው የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በዚሁ መጣጥፋቸው የምርጫውን መቃረብ ተከትሎ ገዢው ፓርቲ በዘረጋው ሰፊ የቁጥጥር መዋቅር አማካይነት እየተካሄዱ ያሉ ምስጢራዊ ክትትሎችን፣የመንግስት ተቋማት የገንዘብ አወጣጥ ህጸፆችንና አሉ ያሏቸውን አፈናዎች ይዘረዝራሉ:: በዚህ ሁኔታ እንዴት ወደ ምርጫው መግባት እንደሚቻል መገመት ይሳነኛል ሲሉም ስጋታቸውን ይገልጻሉ::

ዝርዝሩን በገጽ 3 ይመልከቱ



## 'መድረክ' እስካሁን ለምርጫ ቦርድ የእውቅና ጥያቄ ያለማቅረቡን ገለፀ

### «ሰነዶቹን በማጠናቀቅ ላይ እንገኛለን»


ዶ/ር መረራ ጉዲና

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ መስከረም 30 ቀን 2002 ዓ.ም ከስምንት ፓርቲዎች በተወከሉ 56 አባላት አማካይነት ምስረታውን በይፋ አካሂዶ ለቀጣዮቹ አራት ወራት መድረኩን የሚመሩ ስራ አስፈፃሚዎችን መምረጡ ይታወሳል:: በወቅቱ ያነጋገርናቸው የመድረኩ አመራሮች ምስረታው በተካሄደ ማግስት የህጋዊ እውቅና ሰርተፍኬት ለማግኘት ወደምርጫ ቦርድ እንደሚሄዱ ገልፀው የነበረ ቢሆንም እስካሁን ለቦርዱ የቀረበ ማመልከቻ ያለመኖሩን የመድረኩ ሊቀ መንበር ገለጹ::

ለ18 ወራት ያህል በምስረታ ሂደት ላይ የቆየው የፓርቲዎች ስብስብ መለስተኛ ፕሮግራሙን አዘጋጅቶ ማጠናቀቁን፣ ምስረታው ሲፈፀምም በአስፈላጊ ሰነዶች ላይ የስምምነት ፊርማ ማኖሩን በምስረታው እለት ይፋ ሆኗል:: የመድረክ አባል ፓርቲዎች የሆኑት አፈዴንና

ወደ ገፅ 13 ዞሯል

## በአዲሱ ሕግ:- ውሸት 10 ዓመት፣ ዛቻ እስከሞት ሊያስቀጣ እንደሚችል ያውቃሉ?



12


በውስጥ ገፆች

▶ ቢ.ፒ.አር እና የክ/አገር አውቶቡስ ተራ ቀውስ

▶ ሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽን በ2009 የሚሸለም የአፍሪካ መሪ አለመኖሩን አስታወቀ

▶ ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት ለአንዱ ወንጀል ለሌላው መብት

ኤዲቶሪያል

# የሕዝብና የአገር ክብር ከየትኛውም አመለካከትና ቁሳዊ እሴት የላቀ ነው

## ወሳኝ የታሪክ ምዕራፎችን በግብታዊና አሉታዊ ተግባራት አናምክናቸው

ከተጀመረ ጥቂት ቀናት ያለፈው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የስልጣን ዘመን 5ኛ ዓመቱን በያዝነው ዓመት መጨረሻ ላይ አጠናቆ ለቀጣዩ ፓርላማ መቀመጫውን ይለቃል። የቀሩት ከአንድ አመት እድሜ በታች የሚቆጠሩ ጊዜያት ናቸው ማለት ነው። የያዝነው ዓመት ያለውን ከፍተኛ ፖለቲካዊ ስፍራ የሚያመለክት ሁነት ነው ብለን እናምናለን። ጥያቄው ለዚህ ከፍተኛ ፖለቲካዊ የክንውን ምዕራፍ ያለው ዝግጁነት ምን ይመስላል? ክንውኑን አስመልክቶ የሚወሰዱ ተቋማዊ ትግበራዎች በሰፊው የታሪክ ማህደር ላይ በምን መልኩ ይሰፍሩ ይሆን? ያሉት ነባራዊ ሁኔታዎችስ ምርጫው ስኬታማ በሆነ መንገድ እንዲጠናቀቅ ምን ያህል አመቺ ናቸው የሚሉትና የመሳሰሉትን ያካትታል። ሁላችንም ልንጠይቀው የሚገባን ጥያቄ ነው።

ግንቦት ወር 2002 ዓ.ም ላይ ይደረጋል ተብሎ የሚጠበቀው አገር አቀፍ ምርጫ በአገራችን የመድብለ ፓርቲ ስርአትና የዴሞክራሲ ግንባታ መመስረት ላይ በአንዳንድ የተለዩ ሁኔታዎች ከሚኖረው ከፍተኛ አንድምታ አንፃር ገዢው ፓርቲ፣ ተቃዋሚዎችና ምርጫ ቦርድ ሊኖራቸው ስለሚገባው አስተዋጽኦ የተወሰኑ ነጥቦችን ማንሳት አስፈላጊ ነው ብለን እናምናለን።

በአገራችን የምረጡኝ ዘመቻ ተካሂዶ የሕዝብ ወኪሎችን ለስልጣን የማብቃት ታሪክ ግማሽ ምዕት አመት ያህል ያሳለፈ ነው ብለናል። የዓፄ ኃ/ስላሴ ዘመነ መንግስት ህገ መንግስት ተሻሽሎ ከወጣ በኋላ ህገ መንግስቱ በሚደነግገው መሰረት፤ የተወካዮች ለምርጫ ብቁ የመሆን መስፈርት ባህርያዊ ሁኔታ በሚፈቅደውና የፓርላማ ዕጩዎቹ ተወዳድረው አሸናፊ በመሆናቸው የሚኖራቸው ትግበራዊ ፋይዳ እንዳለ ሆኖ የተከፈተው ምዕራፍ ከ50 አመታት በኋላ ካለንበት ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር እድሜ ጠገቡ ሂደት ያመጣው የቅርጽ ወይስ የይዘት ለውጥ? የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም። በተለይ የምርጫ ሳይሆን የመንግስነት ታሪካቸው እንኳ ከግማሽ ምእተ ዓመት በእድጉ ያነሰ አገራት በመድብለ ፓርቲ ስርአትና በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ጉልብተው ስንመለከታቸው የፍተሻችን ዝማሜ በተጠየቅ መሰረት ላይ ጭምር መሆን አለበት።

የምርጫ ውድድር ለማካሄድ የተለያዩ አማራጮች ያሏቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደሚያስፈልጉ ይታወቃል። እስካሁን ባለው መረጃ 93 ያህል ክልላዊና አገር አቀፍ ፓርቲዎች በህጋዊነት ተመዝግበው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ። ቁጥራቸው የቱንም

ያህል የተጋነነ ይሁን እንጂ የአብዛኞቹ ተሳትፎ በጣም ዝቅተኛና ከአሃዛዊ ስሌትነት የዘለለ ያልሆነባቸው ሁኔታዎችን እየተመለከትን ነው። የብሔራዊ ም/ቦርድ አንድ ከፍተኛ ሃላፊ በቅርቡ ከአንድ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ስለእነዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሲገልፁ "እውቅናውን ከማግኘት ውጪ ተጨባጭ ተሳትፎ የሌላቸው፣ በአንድ ሰው መሪነት የሚንቀሳቀሱ..." ብለዋቸዋል። አብዛኞቹን የተቃውሞ ፖለቲካ ጎራ ይህ እውነታ ይገልፃቸዋል ተብሎ ይታመናል። አገርና ሕዝብ ያላቸው ጥልቅ ክብር ከየትኛውም አለመካከትም ሆነ ቁሳዊ እሴት የላቀ ነውና።

በምርጫ ፉክክሩ ተሳታፊ ይሆናሉ ተብለው የሚጠበቁት ፓርቲዎች ዝግጅት ምን ይመስላል ስንል በዋነኝነት የሚነሳው ፓርቲዎቹ ያላቸው ውስጣዊ አደረጃጀትና የፖለቲካ ፕሮግራሞቻቸውን ለማስፈፀም ከአባሉቻቸው ጋር ያላቸው መስተጋብር ነው። ራሳቸው ለሚያወጧቸው መመሪያና ደንቦች ያላቸው ተገዢነት፣ የፓርቲዎቹ ግልጽ መዋቅርና ዴሞክራሲያዊ አሰራር፣የደንብና መመሪያዎቻቸው ህገ ጠገግነት የሚኖረው ተቀባይነት ነው። እዚህ ላይ የምናነሳው ቀደም ሲል የተጠቀሱትና «እውቅና ከማግኘትና በአንድ ሰው ከመመራት ውጪ የጐላ ተሳትፎ የሌላቸው» የተባሉት " ገና በማደግ ላይ ያሉ" አይነቶቹን አይደለም። ቢያንስ በመርህ ደረጃ ዴሞክራሲያዊ መርህና አሰራሮችን ተቀብለው የስልጣን ገደባቸው ህገ ደንባቸው በሚያዘው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የሚከለስ፣ በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆን አላማዎቻቸውን በህዝብ ውስጥ ለማስረጽ ጥረት የሚያደርጉትንና ለመራጩ ህዝብም የራሳቸው የሆነ ዋጋ ያላቸውን ነው። ፓርቲዎች በውስጣቸው ያሉ ችግሮችን አጥርተው፣በዴሞክራሲያዊ መንገድ ችግሮቻቸውን ፈተው፣ግለኝነትን ማዕከል ካደረገ እልህ መጋባት ይልቅ አገራቸው ያለችበትን ተጨባጭ ሁኔታ ተመልክተው ለቀጣዩ ምርጫ ቢዘጋጁ አገራዊ ፋይዳ የማምጣት አቅማቸው ቀላል የሚሰኝ አይደለምና ቆም ብለው ራሳቸውን ቢፈትሹ እንላለን።

የህዝብና የአገር ክብር ከየትኛውም አመለካከትና ቁሳዊ እሴት የላቀ ነው በሚለው ጥልቅ መርህ ላይ ተመስርተን የተቃዋሚዎችን ሌላኛውን አደረጃጀት ስንመለከት በጋራ የሚካሄዱ ፓለቲካዊ እንቅስቃሴዎችና ትብብሮች ሆነው እናገኛቸዋለን። እንደሚታወቀው ሁሉ በተለያዩ ጊዜያት በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ የተቃውሞ ፖለቲካ ፓርቲዎች ህብረት ይመሰረቱ እንደነበር ይታወሳል። የፊታችን ግንቦት ወር ይደረጋል ተብሎ ለሚጠበቀው ምርጫም መሰል የትብብር ዝማሜዎችና እንቅስቃሴዎች እያየን ነው። ከእነዚህ የትብብር ፓርቲዎች የአንዱ አመራር «ህብረቶች ሲኮላሹ የነበሩት ለስልጣን በሚደረግ ሽሚያ፣ መጠላለፍና በገዢዎች ጫና ነበር። ዛሬ ግን ከዚያ ተምረናል።» ሲሉ ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል።

የተለያዩ የፖለቲካ ፕሮግራሞችና የፖሊሲ አማራጮች ያሏቸው ወገኖች እንዲተባበሩና በአንድ ላይ እንዲቆሙ እንፈልጋለን። ይህን የምንለው አንዱ ወደ ስልጣን

መውጣት ሌላው መውረድ አለበት ከሚል እምነት በመነሳት አይደለም። የዚህ አይነቱ እምነትና ውሳኔ በሚሊዮኖች ድምጽ የሚታወቅና እኛም የምናከብረው ነው። ስለመተባበር የምንነጋገረው የአገራችን ኢኮኖሚያዊ፣ ምጣኔ ሃብታዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ሰፊ፣ ውስብስብና ለአንድ ወገን የሚተው ሳይሆን ለአገራችን እንቆረቆራለን የሚሉ ሁሉ በጋራ የሚሸከሙት ሸክም በመሆኑ ብቻ ነው።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ህብረት እየተገነቡ የመፍረስ ተደጋጋሚ ታሪክ ተወግዶ፣ የጠራ አመለካከትና ህዝባዊ አጀንዳዎችን በማንገብ በመጪው ምርጫ እንዲስተናገዱ በተስፋ እንጠብቃለን። ምንም እንኳን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር በመጪው ምርጫ ጉልህ ለውጥ ይመጣል የሚለው ተስፋ የጨፈገገ ቢሆንም። ከዚሁ ጋር አያይዘን በተደጋጋሚ ቅሬታ የሚቀርብበት ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በቀጣዮቹ ወራት ነፃና ገለልተኝነቱን የሚፈትኑ መሆናቸውን፤ እያንዳንዱ እርምጃውም በአገሪቱ የልማትና የዴሞክራሲ ግንባታ ላይ ወሳኝ መሆናቸውን አበክረን ለማስታውስ እንወዳለን።

አገር አቀፍ ምርጫ በሚካሄድበት ወቅት ሁሉ ሂደቱን እየተከታተሉ ለህዝብ አይንና ጆሮ የሚያበቁ የመገናኛ ብዙሃን (በተለይም የህትመት ሚዲያዎች) ገንቢ ሚና እንደሚጫወቱ ይታወቃል። የነፃ ፕሬስ አላማ ለአንባቢው ትክክለኛ ሚዛናዊና ወቅታዊ መረጃ ማቀበል፣ አስተማሪ ዘገባዎችንና አዝናኝ ጉዳዮችን በህግ የተጠያቂነት ማዕቀፍ ስር ሆኖ ማንሸራሸር ነው። ባደጉ አገራት የእነዚህ ተቋማት ሚና «ጋዜጣ ከሌለው አገር፤ መንግስት የሌለው አገር ይሻላል» በሚል አባባል ይወደሳል። በአገራችንም ህዝባችን ለምናቀርባቸው ስራዎች አክብሮት በመስጠት የሚያደርገው ክትትልና በፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ ሁሉ ከጎናችን በመቆም በትጋት እንድንሰራ የኃይል ምንጭ እንደሆነን በዚህ አጋጣሚ መግለጽ እንፈልጋለን። ይሁንና የቱንም ያህል የሙያ ስነ ምግባራችንና የህግ ድንጋጌዎችን ጠብቀን ብንሰራም ፈታኝ ሁኔታዎች ግን ከተለያየ አቅጣጫ መሰንዘራቸው አልቀረም።

በዛሬውና በነገው እለት የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ የቀድሞውና የአሁኑ ዋና አዘጋጆች አቅርበውት ከነበረው ዘገባ ጋር በተያያዘ ፍ/ቤት የሚቀርቡ ሲሆን አንደኛው ክስ ሳይመሰረትበት ለቀናት በቁጥጥር ስር ውሎ እንደነበር ይታወሳል። በቀጣዮቹ ቀናትም የሌሎች ጋዜጦች ዋና አዘጋጆች በተመሳሳይ ሁኔታ ፍ/ቤት ይቀርባሉ። ጋዜጠኞች ከህግ በላይ አይደለንም። መሆንም አንፈልግም። እየተወሰዱ ያሉት እርምጃዎች ግን የህግ መሰረታዊ ሂደቶችን በጥብቅ በመከተል መርህ ብቻ ሊሆኑ ይገባል የሚል ጠንካራ እምነት አለን። ለዚህ መርህ መከበርም ጉዳያችንን በቅርብ ከሚከታተለው ህዝባችን (አንባቢያን) ጋር በመሆን ሙያችን እስከሚጠይቀው የመስዋእትነት ጥግ ድረስ ለመጓዝ የገባነውን ቃል መጠበቃችንን እናረጋግጣለን። የህፀፁ ዳራ መለስ ግን በዚህ ብቻ የማያቆም መሆኑን እየተመለከትን ነው።

አንዳንድ የመንግስት የመገናኛ ብዙሃን ሰሞኑን የጀመሩት ተገቢነት የጐደለውና ግቡ ያልታወቀ አፍራሽ ዘመቻም በአፋጣኝ ሊታረም ይገባዋል ስንል  መልዕክታችንን እናስተላልፋለን:: በተለይ አንዳንዶቹ አፍራሽ ዘመቻዎች የህግ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ጠንቅቀው ይረዳሉ ተብሎ በሚታመንባቸውና የአቅማቸውን ያህል ሙያዊ ግዴታቸውን እየተወጡ በአጭር ጊዜ ሰፊ ተቀባይነትን ባገኙት ላይ ሲሆን «ለጥፋት አደግድገው የተነሱ» የሚል አሽማቃቂ አገላለጾችን በመጠቀም ጭምር  የሚሰነዘረው የጥቃት ሙከራ ነው::  እንኳን የህዝብ አይንና ጆሮ የሆኑትና ትልቅ አገራዊ ኃላፊነት ያነገቡ ሚዲያዎች ቀርቶ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በአገሩ ላይ ለጥፋት  አደግድጎ ይቆማል ብለን አናምንም:: ማንኛውም ሚዲያ ዜጎች ሀሳባቸውን በነጻነት የሚገልጹበት መድረክ መሆኑ እሙን ነው:: የዚህ አይነቱ ዘመቻ አቀራረብ ግን ሃሳብን በነጻነት ከመግለጽ መብት ጋር ምንም ተዛምዶ የለውም:: በተለይ የኤዲቶሪያል ፖሊሲያቸው ዋነኛ ግብ የመንግስትን ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎችን ማስተዋወቅ እንደሆነ የሚታመንባቸው ሚዲያዎች ይህን ሲሉ «ሀሳብን የመግለጽ ነጻነት» ብቻ እንደሆነ ተደርጎ ሊታለፍ እንደማይችል ይታወቃል:: ምንም ሆነ ምን የአፍራሽ ዘመቻ ፍሬው «አንት መግፋት ምን  ለማውጣት?» ይሉት አይነት ባዶ ጩኸት ሲሆን ለህግ የበላይነት እንቆማለን የሚሉ ሁሉ ሊያወግዙት የሚገባው አካሄድ ነው:: ወሳኝ የታሪክ ምዕራፎችን በግብታዊና አሉታዊ ተግባራት አናምክናቸው፤ስነ አመክንዮአዊ አስተሳሰቦች ይጎልብቱ ይንሸራሸሩ፣ ፍቅር፣ መቻቻልና ህብረታችን ይጠንክር:: ለህዝብና ለአገር ክብር እንቁም!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

## Verbatim

**«ይህ ውይይት በራሱ ኤሌክትሪክ አያመነጭም፤ኤሌክትሪክ የሚያመነጨው ፊንጫአና ግልገል ጊቤ ነው::»**

**ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ**

ፓርላማው የ2002 የስራ ዘመኑን በጀመረበት እለት በፕሬዝዳንቱ ንግግር ውስጥ የመብራት ችግር መካተት እንደነበረበት ተቃዋሚዎች ያቀረቡትን የማሻሻያ ሞሽን አስመልክቶ ከተናገሩት የተወሰደ::

**«የአለም የንግድ ድርጅትን የምንቀላቀለው ለኢኮኖሚያችን ስንል እንጂ ሌሎችን ለማስደሰት ስንል አይደለም:: ኢኮኖሚያችንን እስከጠቀመ ድረስ ተቋማትን ወደግል**

**ይዞታ እናዛውራለን:: እርምጃው ንግዱንና ልማቱን የሚያመጣው ከሆነ ግን እናደርገውም:: ደግሞስ ለምን እናደርጋለን?»**

አቶ ግርማ ብሩ / የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚ/ር /

ኢትዮጵያ የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ለመሆን ጥረቷን ብትቀጥልም ለዚህ ሲባል እንደቴሌ ኮሙኒኬሽንና የገንዘብ ተቋማት ላይ ያላትን ፖሊሲ የመቀየር እቅድ እንደሌላት መናገራቸውን «Capital» ጋዜጣ ምንጮችን ጠቅሶ ያሰፈረው

**[ክብ በሆነው ሰማያዊ መደብ ላይ ያረፈው] ቢጫ ጨረር፤ በመፈቃቀድ አንድነት ለመሰረቱት ብሔር፣ ብሔረሰቦች የፈነጠቀውን ብሩህ ተስፋ ይጠቁማል::**

የኢፌዴሪ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 58/2001 የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ

ስለ አርማው ትርጓሜ በሚያስረዳበት አንቀጽ 8(4) የተቀመጠ::

## ዜናዎች

# 'መድረክ' እስካሁን ለምርጫ ቦርድ የእውቅና ጥያቄ ያለማቅረቡን ገለፀ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ መስከረም 30 ቀን 2002 ዓ.ም ከስምንት ፓርቲዎች በተወከሉ 56 አባላት አማካይነት ምስረታውን በይፋ አካሂዶ ለቀጣዮቹ አራት ወራት መድረኩን የሚመሩ ስራ አስፈፃሚዎችን መምረጡ ይታወሳል:: በወቅቱ ያነጋገርናቸው የመድረኩ አመራሮች ምስረታው በተካሄደ ማግስት የህጋዊ እውቅና ሰርተፍኬት ለማግኘት ወደምርጫ ቦርድ እንደሚሄዱ ገልፀው የነበረ ቢሆንም እስካሁን ለቦርዱ የቀረበ ማመልከቻ ያለመኖሩን የመድረኩ ሊቀ መንበር ገለጹ::

ለ18 ወራት ያህል በምስረታ ሂደት ላይ የቆየው የፓርቲዎች ስብስብ መለስተኛ ፕሮግራሙን አዘጋጅቶ ማጠናቀቁን፣ ምስረታው ሲፈፀምም በአስፈላጊ ሰነዶች ላይ የስምምነት ፊርማ ማረፉን በምስረታው እለት ይፋ ሆኗል:: የመድረክ አባል ፓርቲዎች የሆኑት ኦፌዴንና አህኮ ከስምንት ወር በፊት «ኦፌኮ» በሚል ስያሜ በቅንጅት ለመስራት ላስገባው እውቅና የማግኘት ማመልከቻ ብሔራዊ ም/ቦርድ ተገቢውን ምላሽ ነፍጉናል

በሚል መግለጫ ያወጡትም አባል ፓርቲዎቹ ምስረታቸውን ካካሄዱ በኋላ በነበሩት ቀናት ሲሆን ጥያቄያቸው የደረሰበትን ደረጃ አስመልክቶ በትናንትናው ዕለት አስተያየታቸውን የጠየቅናቸው ዶ/ር መረራ ጉዲና «ህጉ የሚለውና ቦርዱ የሚለው የተለያየ ነው። እስካሁን ተገቢ ምላሽ አላገኘንም።» ሲሉ ቅሬታቸውን ገልፀዋል።

የኦሮሞ ብሔር ድርጅቶች የሆኑት ኦፌዴንና ኦህኮ ባለፈው ሳምንት ባወጡት የጋራ መግለጫ ላይ እንደገለፁት ምርጫ ቦርዱ የሁለቱን ፓርቲዎች የስምምነት ሰነድ መርምሮ የአገልግሎት ዋጋ ያስከፈለ ቢሆንም «በትዕግስት ጠብቁ» ከማለት ውጪ ፍላጎታችንን አልፈፀመልንም ብለዋል። ስምንት ወራት እንደፈጀ የተገለፀው የሁለቱ ፓርቲዎች የቅንጅት ጥያቄ ምላሽ ሳያገኝ ሌላ ህብረት ውስጥ በመግባት በሂደት ላይ የሚገኘው የስምንት ፓርቲዎች የመቀናጀትና ህጋዊ እውቅና አግኝቶ ለቀጣዩ ምርጫ በጋራ መዘጋጀት ከጊዜ ሽሚያ ጋር የተያያዘ መሆኑ እየተነገረ ይገኛል።

ከአውራምባ ታይምስ እስካሁን ወደ ምርጫ ቦርድ ያለመሄዳቸውን አስመልክቶ የወቅቱ የመድረክ ሊቀ መንበር ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ « በእርግጥ እስካሁን የህጋዊነት ማመልከቻውን አላስገባንም።ይህ የሆነው ግን ምንም የተለየ ችግር አጋጥሞን አይደለም። አንዳንድ ሰነዶችን በማዘጋጀት ላይ ስለሆንን ነው።» ብለዋል።

# ቢ.ፒ.አር እና የክ/ሃገር አውቶብስ ተራ ቀውስ

«ትራንስፖርት ባለስልጣን አቅሙ ከሌለው ለፖሊስ ውክልና ሊሰጥ ይችላል።»

*አቶ ጥላሁን ፈንታ/የአቻ ማህበራት ጥምር ኮሚቴ ሰብሳቢ/*

ከጥቅምት 2 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ በአገር አቋራጭ አወቶቡስ ተራ መተግበር በጀመረው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ከለላ አንዳንድ ህገ ወጥ ተግባራት እየተፈፀሙ መሆናቸውንና በተጓዦች ላይም እንግልት እየደረሰ መሆኑን የአቻ ማህበራት ጥምር ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ጥላሁን ፈንታ ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ።

የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራው ከጀመረበት ጥቅምት 2 ቀን 2002 ዓ.ም አንስቶ ተጓዦች ወደ መናኸሪያው ሲገቡ የጉዞ ትኬት ማሳየት እንዳለባቸው የተደነገገ ሲሆን ሾፌሮች እንዳይገቡ በመታገዳቸው በተለይ በአቅመ ደካሞች ላይ ከፍተኛ መጉላላት እየደረሰ መሆኑን ያነጋገርናቸው ተጓዦች በምሬት ገልፀዋል። በሌላ በኩል 17 ያህል የተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበራት ሲኖሩ ባለንብረቶቹ ችግሮቹን ከተለያየ አቅጣጫ በማንሳት መፍትሄ እንዲፈለግላቸው ጠይቀዋል «ችግሩ የመሰረታዊ ሂደት ለውጥ መተግበር መጀመሩ አይደለም።» ያሉን አንዳንድ ባለንብረቶች «ትግበራው ከመጀመሩ በፊት መሟላትና መታረም ያለባቸው ነገሮች ነበሩ። የመጀመሪያው

መናኸሪያውን የማስፋፋት፣ በአዋጁ መሰረት ስራቸውን የሚያከናወኑ ወኪሎችን ማጠናከርና ከግቢ ውጪ በህገ ወጥ መንገድ የሚጭኑ አነስተኛ ተሽከርካሪዎችን /ሚኒባሶችና አይሱዙዎች መቆጣጠር ያስፈልግ ነበር፡፡በተለይ 'ደንበኛ ክቡር' ነው በሚል ጥብቅ መርህ ተጓዦችን ያስተናግዱ የነበሩ የባለንብረት ስምሪት ተቆጣጣሪዎችን ያለህግ ስርአት ባጃቸውን በመንጠቅ ተግባራቸውን እንዳያከናውኑ መደረጋቸው ችግሩን በማባባስ ተጓዦችን ለእንግልት ዳርጓል፡፡» ብለዋል፡፡

በመንገድ ትራንስፖርት መመርያ መሰረት ሚኒባሶች ከ80 ኪ.ሜ እንዲሁም አይሱዙዎች ከ150 ኪ.ሜ ርቀት በላይ በአንድ ጉዞ እንዳይጓዙ የሚያግድ ቢሆንም የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን ይህን ህገ ወጥ ተግባር መቆጣጠር ባለመቻሉ ህገ ወጦቹ እንዳሻቸው እየተንቀሳቀሱ ነው ሲሉ አቶ ጥላሁን በአጽንኦት ገልፀዋል፡፡በትናንትናው እለትም ጉዳዩ ለሚመለከተው የባለስልጣኑ ቢሮ ቅሬታው መቅረቡን ጠቁመዋል፡፡ «ትራንስፖርት ባለስልጣን አቅሙ ከሌለው ለፖሊስ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡» ሲሉም የአቻ ማህበራት ጥምር ኮሚቴ ሰብሳቢው ምክራቸውን ለግሰዋል፡፡

በህገ ወጥ መንገድ የሚንቀሳቀሱት ሚኒባሶች በዜጎች ህይወት ላይ በተደጋጋሚ ጊዜያት እያደረሱ ያሉት ጥፋት ሊገታ ይገባል ያሉት አንዳንድ ባለንብረቶች የተወሰኑትን ብቻ በምሳሌነት ጠቅሰዋል፡፡ ከትናንት በስቲያ ከወላይታ አዲስ አበባ (ከመመሪያው ውጪ 300 ኪ.ሜ ተጨማሪ/ ሲጓዝ ቡታጅራ ላይ የተገለበጠ ሚኒባስ በህይወት ላይ ጉዳት ያደረሰ ሲሆን መሰል የተሽከርካሪ አይነት በትናንትናው እለትና ከሳምንት በፊት ከጎንደር ወደ አዲስ አበባ / ከተፈቀደው ውጪ ከ600 ኪ.ሜ በላይ) ሲጓዝ ፍቼ አካባቢ ከፍተኛ የመገልበጥ አደጋ እንደደረሰበት ለማወቅ ተችሏል፡፡የዚህ ሁሉ ችግር መንስኤ የሆኑ ህገ ወጥ አሰራሮች በአፋጣኝ እርምጃ ካልተወሰደባቸው መናኸርያው በየዕለቱ የሚያስተናግዳቸው 14 ሺህ ያህል ተጓዦች/ከግቢው የሚወጣውና የሚገባው አማካይ/ለከፋ እንግልት መዳረጋቸውን እንደሚቀጥሉ ተገለጸ ሲሆን ቦርድ አመራሩም ያለበትን ኃላፊነት ለመወጣት እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ ከሚጠበቀው በታች ነው ሲሉ ያነጋገርናቸው ባለንብረቶች አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

## ሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽን በ2009 የሚሸለም የአፍሪካ መሪ አለመኖሩን አስታወቀ

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በጥቅምት 2006 ዓ.ም በአፍሪካ የተሻለ የአመራር ሁኔታን ለመፍጠርና መልካም አስተዳደርን ለማበረታታት የተቋቋመው «ሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽን» ከሰሃራ በታች የሚገኙ አገራትን የመልካም አስተዳደር ጥራት ደረጃ

ላለፉት ሁለት ዓመታት «Ibrahim Index» በማለት ማውጣቱ ይታወሳል:: ተቋሙ የመልካም አስተዳደር የጥራት ደረጃ ከማውጣት በተጨማሪ በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ሥልጣን ላይ ወጥተው በሀገራቸው ሕገመንግስት በተቀመጠው ጊዜ ገደብ መሠረት አገልግለው የሥልጣን ዘመናቸውን ከመጨረሻ ሦስት ዓመታት በፊት ለለቀቁ ከቀድሞ የአፍሪካ ፕሬዝዳንቶች ወይም መሪዎች ለአንዱ ዳጐስ ያለ የገንዘብ ሽልማት ያለው የሎሬትነት ማዕረግ ይሰጣል::

የመጀመሪያውን የኢብራሂም ፕሬይዝ የተቀበሉት ባሳዩት የአመራር ብቃትና ስኬት የክብር ሎሬት የተሰጣቸው ኔልሰን ማንዴላ ሲሆኑ፣ የቀድሞ የሞዛምቢክ ፕሬዝዳንት ዩኪም ቺሳኖ እና የቀድሞ የቦትስዋና ፕሬዝዳንት ፌስተስ ጐትባኜ ሞጋዬ በተከታታይ ሽልማቱን አግኝተዋል:: እነዚህ የቀድሞ የአፍሪካ ፕሬዝዳንቶች በተቋሙ ተሸላሚ ሲሆኑ እያንዳንዳቸው አምስት ሚሊዮን ዶላር ሲሰጣቸው ከ10 ዓመታት በኋላ ደግሞ በህይወት ዘመናቸው በዓመት 200 ሺህ ዶላር ይቀበላሉ::

የአገራቱን የአስተዳደር ብቃት ደረጃ ለመወሰን ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት፣ እንዲሁም ከዓለማቀፍ ተቋማት የሚሰበሰቡ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን የሚጠቀመው ፋውንዴሽኑ መልካም አስተዳደርን ይወስናሉ የሚላቸውን አራት መስፈርቶች እንደጠቋሚ ይጠቀማል:: በአንድ አገር ውስጥ ያለው የዜጐች ደህንነትና የሕግ የበላይነት አከባበር፤ የህዝብ ተሳትፎና የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ፤ ዘላቂነት ያለው የኢኮኖሚ ሥርዓትና አተገባበር፤ እንዲሁም ሰብዓዊ ልማትና የሰዎች ማህበራዊ ጉልበታ የደረጃ አወጣጡ ጠቋሚዎች ተደርገው ይወሰዳሉ::

ሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽን የ2009 የአገራቱን የመልካም አስተዳደር ደረጃ ሰንጠረዥ መስከረም 25 ቀን ይፋ ያደረገ ሲሆን በፀጥታና የሕግ የበላይነት ረገድ 86.96፣ በተሳትፎና በሰብዓዊ መብቶች 80.71፣ በዘላቂ ኢኮኖሚ 80.47፣ በሰብዓዊ ልማት 83.16 በማስመዝገብ፣ በ82.83 አጠቃላይ ውጤት ሞሪሺየስ የአንደኝነቱን ደረጃ ይዛለች:: ኬፕ ቨርዴ በ78.01፣ ሲሸልስ በ77.13 አጠቃላይ ውጤቶች ይከተላሉ::

በዘንድሮ የሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽን 37ኛ ደረጃ የተሰጣት ኢትዮጵያ በፀጥታና የሕግ የበላይነት 49.85፣ በህዝብ ተሳትፎና በሰብዓዊ መብት 35.22፣ በዘላቂ ኢኮኖሚ 51.16፣ እና በሰብዓዊ ልማት 46.11፣ እንዲሁም በአጠቃላይ ውጤት 45.59 የተመዘገበላት መሆኑ ታውቋል:: አጎራባቾቿ ኬንያ 22ኛ፣ ጂቡቲ 36ኛ፣ ኤርትራ 46ኛ፣ ሱዳን 49ኛ፣ እና ሶማሊያ 53ኛ ደረጃ የተሰጣቸው መሆኑን ከፋውንዴሽኑ የመልካም አስተዳደር የደረጃ ሰንጠረዥ ለማወቅ ተችሏል::

ሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽን የደረጃ ሰንጠረዡን ይፋ ባረገበት ማግስት በጊኒ የሚገኘው ችግር እንዳሳሰበውም በቦርዱ አማካኝነት መግለጫ አውጥቶ ነበር:: «ልክ ሦስተኛውን የአፍሪካ አስተዳደር የኢብራሂም ኢንዴክስ እንዳጠናቀቅን ለዴሞክራሲ

በአንድነት በቆሙት የጊኒ ዜጐች ላይ አሰቃቂ ጭቆና እየተፈፀመ መሆኑን ታዝበናል፡፡» ብሏል፡፡

ይሁንና ግን በትላንትናው ዕለት ፋውንዴሽኑ በድረ-ገፁ ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ በ2009 ለቀድሞ የአፍሪካ ፕሬዝዳንት (ወይም መሪ) የኢብራሂም ፕራይዝ እንደማይሰጥ መወሰኑን አስታውቋል፡፡ የፋውንዴሽኑ ትኩረት በአፍሪካ መልካም አስተዳደርን ማበረታታትና በአፍሪካ አመራር ላይ ልቀው ለተገኙት እውቅና መስጠት እንደሆነ የሚጠቁመው በፋውንዴሽኑ ቦርድ አማካኝነት የተለቀቀው የሽልማት ኮሚቴው መግለጫ «በሌሎች አገራት ያሉትን ችግሮች በአጽንኦት ቢገነዘብም የሽልማት ኮሚቴው በአንዳንድ የአፍሪካ አገራት የታየውን የመልካም አስተዳደር መሻሻል ተመልክቷል፡፡» ይላል፡፡

ሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽን ተሸላሚውን መምረጥ ያልቻለበትን ቀጥተኛ ምክንያት እንዳልገለፀ ሁሉ የፋውንዴሽኑ መስራች የሆኑት ሱዳናዊ ባለሀብት ሞ ኢብራሂም ቀድሞውኑም ፋውንዴሽኑ መሪዎችን ሳይሸልም ሊቀር የሚችልበት ዓመት ሊኖር እንደሚችል መገለፁን ከማስታወስ በቀር ያስቀመጡት ምክንያት አልነበረም፡፡ ሽልማቱ ያስፈለገበት ምክንያት የአፍሪካ መሪዎች ወደ ሥልጣን የሚመጡት ከአነስተኛ የሀብት ተሞክሮ በመሆኑ ሥልጣን በሚለቁ ሰዓት ድህነቱ እንደሚጠብቃቸው በመስጋት ሥልጣንን የሙጥኝ ወደማለቱ ሊያዘምሙ በመቻላቸው እንደሆነ ሞ ኢብራሂም ይናገራሉ፡፡ ይሁንና ግን የሽልማቱን ውጤታማ መሆን፣ አለመሆን የሚያመላክቱ የቅርብ ጊዜ ማስረጃዎች አበረታች አለመሆናቸውን አንዳንድ ተንታኞች ይጠቁማሉ፡፡

ዩጋንዳ፣ ቻድ እና ካሜሮን መሪዎቹ በሥልጣን ይቀጥሉ ዘንድ ሁሉም ሕገ መንግስቶቻቸውን ለውጠዋል፡፡ ከዚህም በላይ በጊኒ፣ በሞሪታኒያ እና በማዳጋስካር መፈንቅለ መንግስት ከመካሄዳቸውም ባሻገር ዓለም አቀፍ መመዘኛዎችን የማያሟሉ ብዙ ምርጫዎችም መስተናገዳቸው የሽልማቱን ውጤታማነት ይታገላሉ፡፡ እንዲሁም በሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽን የላቀ ቦታ የተሰጣቸው ሞሪሺየስ፣ ኬፐ ቨርዴ እና ሲሸልስ የአህጉሪቱ የኃይል ማዕከላት ከመሆን እጅግ የራቁ መሆናቸውም ይገለፃል፡፡

የደቡብ አፍሪካው ታቦ 'ምቤኪ እና የጋናው ጆን ኩፎር ዘንድሮ በፋውንዴሽኑ የሎሬትነት ማዕረግ ሊሰጣቸው ከታጩት ውስጥ እነደነበሩበት ቢነገርም መሪዎቹ ማዕረጉንም፣ ተያያዥ የገንዘብ ሽልማቱንም እንደማያገኙ የሽልማት ኮሞቴው ትናንትና አመላክቷል፡፡

የሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽን የሽልማት ኮሚቴ በቀድሞ የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሃፊ ኮፊ አናን የሚመራ ሲሆን የቀድሞ የፊንላንድ ፕሬዝዳንትና የኖቤል ሎሬት ማርቲ አቲሳሪ፣ የቀድሞ የጊኒ የትምህርት ሚኒስቴርና በዩኔስኮ የመሠረታዊ ትምህርት ዳይሬክተር የሆኑት አኢቻ ባህ ዲያሎ፣ የዓለም አቀፍ አቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተርና የኖቤል ሎሬት ሞሐመድ ኤልባራዴ፣ የኬፕ ታውን ዩንቨርሲቲ ቻንስለርና

የሞዛምቢክ የቀድሞ የትምህርት እና የባህል ሚኒስትር ግራሻ ማሼል፣ የቀድሞ የአየርላንድ ፕሬዝዳንትና በሰብዓዊ መብቶች ገዳይ የዩ.ኤን. ከፍተኛ ኮሚሽነር ሜሪ ሮቢንሰን፣ እንዲሁም የቀድሞ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ፀሀፊና የቀድሞ የታንዛኒያ ጠ/ሚኒስትር ሳሊም አህመድ ሳሊም በኮሚቴው ውስጥ ይገኙበታል።

የሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽን በትናንትናው ዕለት ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ በዚህ ዓመት የሎሬትነት ማዕረግ የሚሰጠው ባይኖርም እንኳን በህዳር 14 እና 15 2002 በዳር ኤስ ሰላም እንዲካሄዱ የታቀዱት ፕሮግራሞች እንደሚቀጥሉ አረጋግጧል። እነዚህ ዝግጅቶች የአየር ጠባይ ፍትህን፣ ግብርናን፣ የምግብ ዋስትናን እና ክልላዊ የኢኮኖሚ ጥምረትን ጨምሮ ለአፈሪካ የወደፊት መሻሻል ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮችን ለመወያየት ባለድርሻዎችን የሚያሰባስብ የውይይት ፎረም ያካተቱ መሆናቸው ተገልጿል።

## መጣጥፎች

# ባልተደላደለ ሜዳ፤ ወደ ምርጫ 2002

**በነጋሶ ጊዳዳ (ዶ/ር)**

በኦሮሚያ ክልል በቄለም ወለጋ ዞን ደምቢ ዶሎን ከመስከረም 8 እስከ 18/2002 ዓ.ም ጉብኝቼ ነበር። በጉብኝቴ ወቅት የወቅቱን የፖለቲካ ሁኔታ በተመለከተ የተቻለኝን ያህል መረጃ ለማሰብሰብ ሞክሬአለሁ። የአካባቢው አስተዳደር ፈቃደኛ ስላልነበር ህዝባዊ ስብሰባዎችን ለማካሄድ አልቻልኩም። ስለዚህም ከብዙ ግለሰቦች ጋር ለመገናኘት ሞከርኩኝ። በአስር ቀናት ውስጥ ከሁለት ደርዘን በላይ ግለሰቦችን ያነጋገርኩ ሲሆን የኦሕዴድ/ኢሕአዴግ ካድሬዎችን ጨምሮ ከነጋዴዎች፣ ከአካባቢ ሽማግሌዎች፣ ከመንግስት ሰራተኞች (መምህራን እና የጤና ሰራተኞች)፣ ከቀበሌ ኃላፊዎች፣ እረፍት ላይ ከሚገኙ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች፣ ከሀይማኖት አባቶች፣ በግል ሙያ ከተሰማሩ ሰዎች፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች አባላት እና ተቀጣሪዎች፣ እንዲሁም ከኦፌዴን ደጋፊዎች ጋር ተገናኝቻለሁ።

ይህ ገለፃዊ ትንታኔ በጥቂት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በማተኮር የቀረበ ነው። በአጠቃላይ ድምዳሜ ኦሕዴድ/ኢሕአዴግ የአካባቢውን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሯል፣ ስለዚህም በደምቢ ዶሎ አካባቢ ለተቃዋሚ የተደላደለ የመጫወቻ ሜዳ ሊኖር አይችልም። የወቅቱን ሁኔታ ለማረም የመጀመሪያው እርምጃ በምርጫ

አስፈፃሚው የተለያዩ እርከኖች ላይ ብቁ ሥልጠና ያላቸው የምርጫ አስፈፃሚዎችን መሾም ነው፡፡

## 1. ጥብቅ የፀጥታ ቁጥጥር እና ክትትል

የ1997 እና የ2000 ዓ.ም ምርጫዎችን ማሸነፉን የሚገልፀው ኦሕዴድ/ኢሕአዴግ በአካባቢው ሊፎካከሩት ለሚችሉ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ላለመፍቀድ የቆረጠ ይመስላል፡፡ ይህ ወደ አካባቢው የሚመጡ ግለሰብ ጐብኚዎችን እስካለመቀበል ይደርሳል፡፡ የት እንደሄዱ፣ ማንን እንደጐበኙና ምን እንዳሉ ለማረጋገጥ በጐብኚዎች ላይ ምስጢራዊ ክትትልም ይደረጋል፡፡ አልፎ አልፎም ጎብኚዎች ለጥያቄ ይጠራሉ ወይም የፀጥታ ሰዎች ወደነሱ ይመጣሉ፡፡ በፀጥታ ኃላፊዎች ከሚጠሩትና ከሚጠየቁት ጎብኝዎች ጋር ግንኙነት ያላቸው የአካባቢው ሰዎች ናቸው፡፡ የኔን ጉዳይ ብንመለከት፣ ከፓርላማ ይገፄው የሄድኩትን ደብዳቤ ለፀጥታ ቢሮ ያደረሰው በእንግድነት የተቀበለኝ የእህቴ ባለቤት ነው፡፡ በተጨማሪም ከደምቢ ዶሎ እና ከነቀምቴ የፀጥታ ቢሮዎች የስልክ ጥሪዎች ደርሰውታል፡፡ ለምን እንደመጣሁ፤ ለቀጣዩ ምርጫ ለመዘጋጀት፣ ወይንስ ለሌላ ዓላማ መምጣቴ ተጠይቋል፡፡

ኦሕዴድ/ኢሕአዴግ የፖሊስና የፀጥታ ቢሮዎችን እና ሰራተኞችን ለራሱ ጥቅም ከማዋሉም ባሻገር በደምቢ ዶሎ ከእያንዳንዱ መኖሪያ ቤት በሌላ መንገዶች መረጃ ይሰበስባል፡፡ ከነዚህ ዘዴዎች አንዱ በኦሮሞ «Shanan» ወይም በአማርኛ «አምስቱ» የተሰኙ ድርጅቶች ወይም መዋቅሮች መጠቀምን ያካትታል፡፡ አምስት የአባወራ ቤተሰቦች በአንድ መሪ ስር ይቧደናሉ፤ ይህ መሪ በየቀኑ ከእያንዳንዱ ቤተሰብ መረጃ በመሰብሰብ «Gare» ወይም «ጐጥ» ለሚባል የበላይ አስተዳደራዊ አካል ያስተላልፋል፡፡ «Gare» የሚባለው ቡድን ሊቀ መንበር፣ ፀሃፊ፣ የፀጥታ ኃላፊ እና ሁለት ሌላ አባላት ያሉት ሲሆን በስሩ ከ30 እስከ 40 ቤተሰቦች አሉ፡፡ የፀጥታ ኃላፊው የሰበሰበውን መረጃ በቀበሌ ደረጃ በሚገኝ በበላይ አስተዳደራዊ አካል ኃላፊው ለሆነው ሲያስተላልፍ ይሄኛውም በበኩሉ ለወረዳ ፖሊስ እና ለፀጥታ ቢሮ ያቀብላል፡፡

እያንዳንዱ ቤተሰብ እንግዶቹን እና ጐብኚዎቹን በተመለከተ የጉብኝቱን ምክንያት፣ የሚቆዩበትን ጊዜ፣ ምን እንደተናገሩና እንደሰሩ፣ እንዲሁም በምን ዓይነት እንቅስቅሴዎች ላይ እንደተሰማሩ ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ አምስቱ የአባወራ ቤተሰቦች «በልማት ሥራ» ላይ መሳተፋቸውን፣ በተለያዩ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች ላይ ማዋጣታቸውን፤ በቀበሌ ስብሰባዎች መካፈላቸውን፣ ለምርጫ የተመዘገቡ መሆናቸውን፣ እንዲሁም መምረጣቸውንና ለማን ድምፃቸውን እንደሰጡ «Shanan»/«ሸነን» ተብሎ የሚጠራውን ቡድን የሚመራው ያውቃል፡፡ የኦሕዴድ/ኢሕአዴግ ብዙሃን ማህበራት (የሴቶች፣ የወጣቶች እና የአነስተኛ ብድር ቡድኖች) እና የፓርቲ ንዑሶች («አባቶች»፣ «እናቶች» እና «ወጣቶች»)፣ እንዲሁም

በትምህርት ቤቶች፣ በጤና ተቋማት እና በሀይማኖት ተቋማት የሚገኙ የፓርቲ ንዑሳን ለተመሳሳይ ግልጋሎት ይውላሉ::

## 2. ድርጅታዊ መዋቅሮች

እዚህ ላይ ራሱ ኦሕዴድ/ኢሕአዴግ እና የወረዳ መዋቅሩ እንዴት እንደተደራጀ መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው:: የኦሕዴድ/ኢሕአዴግ ቁለም ወለጋ የዞን ቢሮ በደምቢ ዶሎ ይገኛል:: ይህ ቢሮ አዲስ አበባ ከሚገኘው ክልላዊ ቢሮ መረጃ እና ትዕዛዝ ይቀበላል:: መልዕክቶችን ለበታች መዋቅሮች በማቀበል ፕሮፓጋንዳውንና የፓርቲውን ድርጅታዊ እንቅስቃሴዎች ይከታተላል:: ይህ ቢሮ በእያንዳንዱ መንደር፣ በትምህርት ቤቶች እና በጤና ተቋማት ቅርንጫፎች አሉት:: እነዚህ ቅርንጫፎች ወደ ዋና ዋና ንዑሶች የተከፋፈሉ ናቸው:: የንዑሶቹ ቅርንጫፎች የተዋቀሩት በደጋፊ ቡድኖች፣ በእጩ ተመራጭ ቡድኖች እና ሙሉ ለሙሉ አባል በሆኑ ቡድኖች ነው::

በተጨማሪም ፓርቲው የበለጠ ቁጥጥር ለማስፈንና ፕሮፓጋንዳውን በቀላሉ በማሰራጨት የፓርቲ እንቅስቃሴዎችን ለመስራት ህዝቡን ወደ ወጣቶች፣ ሴቶች እና አነስተኛ የብድር ማህበራት በመመደብ አደራጅቶ ቆይቷል:: ደምቢ ዶሎ ከተማ ልዩ የወረዳ ከተማ መስተዳደር ናት:: መስተዳደሩ በአራት ሰፋፊ «Ganda» ወይም መንደሮች የተከፋፈለ ነው:: ቀድሞ ከተማዋ ሰባት ቀበሌዎች የነበሯት ቢሆንም የ2000 ዓ.ም የቀበሌ ምርጫን ተከትሎ ዳግም ተዋቅራለች:: በወረዳ ምክር ቤት እያንዳንዱ ቀበሌ 15 ተወካዮች አሉት:: ኢሕዴድ/ኢሕአዴግ አስቀድሞ የተመረጡ የምክር ቤት አባላትን ስም ዝርዝር ለቀበሌ ምክር ቤት እንዳቀረበና እንዲደገፉ እንዳደረገ ይነገራል:: እንዲሁም ሰዮ ወረዳም አለ (24 ቀበሌዎች አሉት):: የሰዮ ወረዳ መስተዳደርም በደምቢ ዶሎ ከተማ መቀመጫ አለው:: እነዚህ ሁሉ የፓርቲው ተሿሚዎች ሲሆኑ ለፓርቲው «እጅግ ቁርጠኛ» መሆናቸውም ይታመናል:: አራቱ «Ganda» (መንደሮች ወይም ክፍለ ከተማ ሊባሉ የሚችሉት) እያንዳንዳቸው የራሳቸው ምክር ቤቶች አሏቸው:: አንድ ምክር ቤት 300 አባላት አሉት:: አባላቱ በ2000 ዓ.ም ነው «የተመረጡት»:: ያነጋገርኳቸው ሰዎች ሁሉ ፓርቲው እጩዎቹን አስቀድሞ እንደሰየማቸው አረጋግጠውልኛል:: ቀበሌ የራሱ ካቢኔ ሲኖረው እነዚህም የፓርቲ አባላቶች ናቸው:: አንድ ቀበሌ ደግሞ ወደተለያዩ ቀጠናዎች ይከፋፈላል:: ቀጠናዎቹ እንደገና ወደ «Gare»/«ጐጥ» ይከፋፈላሉ:: በአንድ ቀጠና ውስጥ እስከ 17 የሚደርሱ «ጐጦች» አሉ::

## 3. የህዝብ ንብረትን፣ ገንዘብን እና የመንግስት ሠራተኞችን አላግባብ መጠቀም

የፓርቲው የፕሮፓጋንዳ እና የድርጅት ኮሚቴዎች በዞን፣ በወረዳ እና በቀበሌ መስተዳደር ህንፃ ውስጥ ይገኛሉ:: ፓርቲው ለሚጠቀምባቸው ክፍሎች [ህንፃዎች]

ኪራይ አይከፍልም:: የኮሚቴ አባላቱ የፓርቲው ካደሬዎች ናቸው፤ ነገር ግን ወርሃዊ ደሞዛቸው እና የቀን አበላቸው የሚከፈለው በመስተዳደሩ ከመንግስት ካዝና ነው:: ፀሃፊዎቻቸው፣ የጽዳት ሠራተኞቻቸው እና ተላላኪዎቻቸውም ደሞዛቸውን የሚያገኙት ከመንግስት ካዝና ነው:: ሁሉም የመንግስት ሠራተኞች ጭምር የፓርቲው አባላት ናቸው:: አባላቱ ለፓርቲው የሚያደርጉት ወርሃዊ መዋጮ ወርሃዊ ደሞዛቸው በሚከፈላቸው ጊዜ በወረዳው የፋይናንስ ቢሮ ይሰበሰባል:: የፓርቲው ኃላፊዎች የመንግስት ተሽከርካሪዎችን ጨምሮ የቢሮ ቁሳቁሶችን እና መሣሪያዎችን ይጠቀማሉ:: ፓርቲው የኪራይ ክፍያ ሳይፈጽም የከተማ እና የቀበሌ አዳራሾችን ይጠቀማል:: የጤና እና የትምህርት ተቋማት መሰብሰቢያ አዳራሾች ያለክፍያ ጥቅም ላይ ይውላሉ:: ይህ አሰራር ከዞን እስከ «ጐጥ» እርከኖች ድረስ ይተገበራል:: ይሁንና ግን የኦሕዴድ/ኢሕአዴግ ተቃዋሚ የሆነ ከግለሰብ ባለቤቶች ለቢሮ የሚሆኑ ክፍሎችን ወይም ለስብሰባዎች በከተማው ያሉ የስብሰባ አዳራሾች ለመከራየት አይፈቀድላቸውም:: ፕላዝማ ቴሌቪዥኖች ለትምህርት ቤቶች የታሰበ ነው፤ ነገር ግን በወረዳዎች መካከል የፓርቲውን ፕሮፓጋንዳ ለማሰራጨት ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው::

## 4. የኦሕዴድ/ኢሕአዴግ የፖለቲካ ፕሮግራሞች ስርጭት

በቀበሌዎች የሚገኙ ሁሉም አዋቂ ሰዎች እና የመንግስት ሠራተኞች በተለያዩ ሴሚናሮች እና አውደጥናቶች ላይ እንዲሳተፉ ይገደዳሉ:: በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሙያ ሥልጠና ተቋማት ለሚገኙ ተማሪዎችም እንዲሁ ተመሳሳይ ነው:: በእረፍት ላይ የሚገኙ እና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችም በእንዲህ ዓይነት ፕሮግራሞች ላይ መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል:: የ«Tarsimo» (የስትራቴጂ) እና «Bulchiinsa Gaarii» (የመልካም አስተዳደር) ትምህርቶች ለሁሉም ነዋሪዎች (ለመደበኛ ት/ቤት ተማሪዎች፣ ለኮሌጅና ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች፣ እንዲሁም ለግል እና ለመንግስት ሠራተኞች) እየተሰጠ ነው:: በቢ.ፒ.አር ላይ አውደጥናቶች የተካሄዱ ሲሆን እያንዳንዱ የመንግስት ሠራተኛ ለተሳትፎ 25 ብር ተከፍሎታል:: የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሴሚናር በአምስት ቀናት የተጠናቀቀ ቢሆንም በዚህ ሴሚናር ለሚሳተፉት ለዘጠኝ ቀናት ለእያንዳንዳቸው በቀን 35 ብር የቀን አበል እንደሚከፈል የታሰበ ነበር:: በየሁለት ሣምንቱ ዓርብ ከሰዓት በኋላ ሁሉም የመንግስት ሠራተኞች በሥራ ሰዓት እና በህዝብ መሰብሰቢያ ክፍሎች ውስጥ በፓርቲው እና በንዑስ የጥናት ክበብ ስብሰባዎች ይሳተፋሉ:: ለመሰብሰቢያ ክፍሎቹ የተከፈለ የኪራይ ሂሳብ የለም:: አልፎ አልፎ ለፓርቲው መደጐሚያ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች ይካሄዳሉ:: የመስተዳደሩ የፋይናንስ ኃላፊዎች ናቸው ቃል የተገባውን የገንዘብ መጠን ከሠራተኞቹ በመቀነስ ለፓርቲው የሚያስተላልፉት::

## 5. ምርጫዎች

በ1997 ምርጫ ለኦሕዴድ/ኢሕአዴግ የምርጫ ቅስቀሳ የመንግስት ሰራተኞች ለሁለት ሣምንት እንደተመደቡና የመንግስት ተሽከርካሪዎች (መኪናዎች እና ሞተር ሳይክሎች) ለዚሁ ዓላማ እንደዋሉ ታዝቤያለሁኝ። የኦሕዴድ/ኢሕአዴግ አባላት እና ካድሬዎች እኔ የጠራኋቸውን ህዝባዊ ስብሰባዎች በማደናቀፍ በኩል ሥራ በዝቶባቸው ነበር። ከታዛቢዎች አንዱ በማባበያ እኔ ያገኘሁትን ድምጽ ለተፎካካሪዬ (ኦሕዴድ/ኢሕአዴግ) ለመስጠት ተስማምቶ ነበር። በአንድ ቀበሌ ከገበያ ቦታ በ500 ሜትር ርቀት የምርጫ ቅስቀሳ እንዳላደርግ ተከልክዬ ነበር። የቀበሌው ኃላፊዎች የሚካሄደው ስብሰባ ገበያውን እንደሚያውክ ነገሩኝ። የመቀስቀሻ ፖስተሮቼ ከተለያዩ ቦታዎች የተነሱ ሲሆን የበተንኳቸው በራሪ ወረቀቶች ተሰብስበው ተወግደዋል። ለምርጫ ኃላፊዎቹ እነዚህን ሕገ-ወጥ እንቅስቃሴዎች እንዲያስተካክሉ ወይም በምርጫ ሕጉ መሠረት ከምርጫ ውድድሩ እንዲሰርዙት በተደጋጋሚ አመልክቼ ነበር፤ ነገር ግን ለአቤቱታዎቼ ቦታ የሰጠ አልነበረም።

እንዳነጋገርኳቸው ሰዎች ከሆነ፣ በ2000 ዓ.ም ምርጫ የምርጫ ቢሮ ኃላፊው የኦሕዴድ/ኢሕአዴግ አባል ነበር። ይኸው ተመሳሳይ ግለሰብ ለ2002 ዓ.ም ምርጫ በኦሕዴድ/ኢሕአዴግ እየታጨ እንደሆነ የሚወራ ወሬም አለ። ኦሕዴድ/ኢሕአዴግ ለመራጮች በየትኛው ሳጥን ውስጥ ምልክታቸውን እንደሚያስቀምጡ ወይም እንደሚፈርሙ የሚናገሩ ደጋፊዎችን ወይም አባላትን በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያዎች ሰይሞ ነበር።

## 6. ተቃዋሚዎች የሚገኙበት ሁኔታ

የኦፌዴን ቢሮ ከ1997 ጀምሮ እንደተዘጋ ቆይቷል። አባላት እና ደጋፊዎችም ለብዙ ጊዜያት ፈታኝ ዕጣዎች ገጥመዋቸዋል። ትንኮሳ ደርሶባቸዋል። ደምቢ ዶሎ ከመሄዴ አስቀድሞ በነበሩት ሦስት ሣምንታት በሰዮ ወረዳ 60 ሰዎች እና በደምቢ ዶሎ 15 ሰዎች ታስረውና እስከ 48 ሰዓታት በፖሊስ እጅ ቆይተው ነበር። ከመለቀቃቸው በፊት የመቶ ብር ዋስትና መክፈል ነበረባቸው። ለመጪው ምርጫ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል። «ተጠንቀቁ፣ በ1997 ዓ.ም እንዳደረጋችሁት ለተቃዋሚ እንዳትደግፉ፣ አባል እንዳትሆኑ፣ አልያም ድምፃችሁን እንዳትሰጡ። እንደያኔው አንሸነፍም...» ተብለዋል። ኦፌዴን ከኦነግ ጋር የተነፃፀረ ሲሆን ቅንጅት ወይም በኦሮሚያ እንደሚጠራው «Qindomina» ከ«ነፍጠኛ» ጋር ተነፃጽሯል። አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲን እንደ «ነፍጠኛ» ድርጅት እንዲታይ የሚደረገው ቅስቀሳ ከአሁኑ ተጀምሯል።

## 7. ሚዲያ

በደምቢ ዶሎ የግል ወይም ገለልተኛ ጋዜጣ አይገኝም። ከፌዴራል እና ከኦሮሚያ መንግስት ሚዲያዎች ባሻገር አማራጭ የዜና ምንጮች የአሜሪካ ደምጽ ራዲዮ እና

የጀርመን ድምጽ (ዶቼ-ቬሌ) ብቻ ናቸው:: የኦሮሚያ ማስታወቂያ ቢሮ እና ኦሕዴድ የፕሬስ ሚዲያቸውን ወደአካባቢው በአውቶቡስ ይልካሉ:: እነዚህንም የመንግስት ሠራተኞች ተረክበው ለተለያዩ ተቋማት እና ቢሮዎች ያከፋፍላሉ:: ሁሉም ሠራተኞች እነዚህን ጋዜጦች እንዲገዙ ይደረጋሉ::

## 8. መደምደሚያ

በደምቢ ዶሎ እና በአካባቢዋ ቆይታ ላደረገ ለማንኛውም ሰው የተደላደለ የፖለቲካ መጫወቻ ሜዳ አለመኖሩ ግልጽ ነው:: እንዲህ ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ ተቃዋሚው እንዴት ወደምርጫ ሂደት ሊገባ እንደሚችል መገመት ይሳነኛል:: ገዢው ፓርቲ በ2002 ሰላማዊ፣ ፍትሃዊ እና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ የማካሄድ ጠንካራ ዓላማ ካለው ሁሉንም የፖለቲካ እስረኞች መልቀቅን ጨምሮ የተቃዋሚ አባላትን ማሰር፣ መተንኮስ፣ አፈና መፈፀምና ማባበልን በማስቀረቱ ረገድ፣ እንዲሁም የተዘጉ የተቃዋሚ ቢሮዎች በአፋጣኝ እንዲከፈቱ፣ በመንግስት ሚዲያ ላይ እኩል ሽፋን እንዲሰጥ፣ የተቃዋሚዎች ስብሰባዎች በነፃነት እንዲካሄዱ በመፍቀዱ ረገድ፣ ብሎም ገለልተኛ የምርጫ አስፈፃሚ ኃላፊዎች ይሾሙ ዘንድ የምርጫ ሕጉን በማሻሻሉና ፍትሃዊ ምርጫዎችን ለማረጋገጥ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች የመታዘብ እድሉን እንዲያገኙ በማመቻቸት፣ እንዲሁም ደጋፊዎቹ እና አባላቱ ሕገመንግስቱን እና የምርጫ ሕጉን እንዲያከብሩ የመቆጣጠሪያ ዘዴዎችን በመዘርጋቱ ረገድ አያሌ ሥራዎች ይጠብቁታል::

***/ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፣ የቀድሞው የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንትና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ናቸው/***

# *<u>በአዲሱ ሕግ</u>*

# ውሸት 10 ዓመት፤ ዛቻ እስከሞት እንደሚያስቀጣ ያውቃሉ?

## /ፕሬስ እና የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ/

**በግዛው ለገሠ**

የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ለሕግ አውጭው የመንግስት አካል ከመቅረቡ በፊትም ሆነ በዚሁ አካል ከፀደቀ በኋላ በተለያዩ መንገዶች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን አወያይቷል፣ ተሰሚነት ያላቸው ዓለም አቀፍ ተቋማት አውግዘውታል:: መንግስትም ከነገረ ቀደም ዲፕሎማቶችን ከማማከሩ ባሻገር በሚሰነዘሩት ትችቶች ላይ መልስ

ሰጥቷል፤ እንዲያውም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አማካኝነት መድረክ አሰናድቶ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን አወያይቷል። የተቃዋሚ ፓርቲዎቹም የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሚገኙበት ፓርላማ ውስጥ የፀደቀው የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ሰብዓዊ መብትን ከመግፋቱ በተጨማሪ የፖለቲካ ምህዳሩንም እንደሚያጠብ ሲሟገቱ ተመልክተናል።

ዛሬ ይህንን ጽሁፍ ለማዘጋጀት የተነሳሳነው አንዳንድ ወገኖች የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁ የፕሬስ ነፃነትን የሚጋፋ እንደሆነ አድርገው ይረዱታል ተብሎ ሳይገመት አይቀርም በሚል ነው። እናም ዳሰሳችን በጥቂት የአዋጁ አንቀጾች፣ በተለይም በአንቀጽ 6 ላይ የተመረኮዘ ሲሆን ከፕሬስ ነፃነት ጋር ያላቸውን ተዛመዶ (ወይም ተቃርኖ) እንመለከታለን።

በቅድሚያ ምንም እንኳን በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን በተደጋጋሚ የተገለፀ ቢሆንም ለበለጠ መረጃ ይሆን ዘንድ፣ እንዲሁም ሕግን አለማወቅ ይቅርታ የማያሰጥ በመሆኑ ለህብረተሰቡ ግንዛቤን ለማድረስ በአዋጁ የሽብርተኝነት ድርጊቶች ተብለው የተዘረዘሩትን እናስታውስዎ።

## «ዛቻ» ሞት ሊያስቀጣ እንደሚችል ያውቃሉ?

በአዋጁ አንቀጽ 3 ላይ ከ15 ዓመት እስከ እድሜ ልክ በማደረስ ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጡ ሰባት ድርጊቶች ተዘርዝረዋል። የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ አንቀጽ 3 እንዲህ ይነበባል፡-

**ማንኛውም ሰው ወይም ቡድን የፖለቲካ፣ የሃይማኖታዊ ወይም የአይዲዮሎጂ ዓላማን ለማራመድ በማሰብ በመንግስት ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር፣ ህብረተሰቡን ወይም የህብረተሰቡን ክፍል ለማስፈራራት ወይም የሃገሪቱን መሰረታዊ ፖለቲካዊ፣ ህገመንግስታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ ተቋማትን ለማናጋት ወይም ለማፍረስ፡-**

1) **ሰውን የገደለ ወይም በአካሉ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤**
2) **የህብረተሰቡን ወይም የህብረተሰቡን ክፍል ደህንነት ወይም ጤና ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ እንደሆነ፤**
3) **እገታ ወይም ጠለፋ የፈፀመ እንደሆነ፤**
4) **በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፤**
5) **በተፈጥሮ ሀበት፣ በአካባቢ፣ በታሪካዊ ወይም በባህል ቅረስ ላይ ከፍተኛ ገዳት ያደረሰ እንደሆነ፤**
6) **ማናቸውንም የህዝብ አገልግሎት ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ፣ የያዘ፣ በቁጥጥር ስር ያደረገ፣ ያቋረጠ ወይም ያበላሸ እንደሆነ፤ ወይም**
7) **በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (6) ከተመለከቱት ድርጊቶች መካከል ማናቸውንም ለመፈጸም የዛተ እንደሆነ፤**

**ከ15 አመት እስከ እድሜ ልክ በሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል።**

በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት የሽብርተኝነት ድርጊቶች በሰባተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠው የመዛት ድርጊት ከተጨባጭ ድርጊቶች እኩል ሞት ሊያስቀጣ መቻሉ ተመጣጣኝነትን ያጣ ስለመሆኑ በአንዳንድ ሰዎች ይነገራል። ይኸውም፣ ለምሳሌ አንድ ሰው የፖለቲካ ዓላማውን ለማራመድ በማሰብ በመንግስት ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር (የማስረጃ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ) ከአንድ እስከ ስድስት የተዘረዘሩትን ድርጊቶች ለመፈፀም ቢዝት ከ15 ዓመት እስከ እድሜ ልክ የሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም የሞት ቅጣት ሊገጥመው እንደሚችል ተደንግጓል።

የአዋጁ አንቀጽ 4 ከላይ ከአንድ እስከ ስድስት የተዘረዘሩትን ለመፈፀም ማቀድ፣ መዘጋጀት፣ ማሴር፣ ማነሳሳትና መሞከር ተመሳሳይ ቅጣት እንደሚያስቀጣ በግልጽ ያስቀመጠ ሲሆን አንቀጽ 5 ደግሞ ለሽብርተኝነት ድርጊት አፈፃፀም ወይም ለሽብርተኛ ድርጅት በአንቀጹ ስር ተዘርዝረው በተቀመጡ መንገዶች ድጋፍ መስጠት ከ10 እስከ 15 ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት፣ እንዲሁም የሽብርተኝነትን ድርጊት ለፈፀመ ሰው ከለላ መስጠት ወይም መደበቅ ወይም እንዲያመልጥ መርዳት ከ10 ዓመት እስከ እድሜ ልክ የሚደርስ ጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ያስገነዝባል።

በርግጥ ለአንድ ድርጊት መከናወን የነበረው የዓዕምሮ ዓላማ (intent) ችላ የማይባል ቢሆንም፣ ያ ግን የማስረጃ ጉዳይ መሆኑ አይቀርም። አንድ ግለሰብ በደረሰበት የአገልግሎት በደል ምክንያት እጅጉን ተማርሮ (በአንቀጽ 3 (7) የተጠቀሰውን ዓይነት) «*ይሄንን መሥሪያ* ቤት አወድመዋለሁ!» ብሎ ቢዝት እስከ ሞት የደረሰ ቅጣት ይገጥመው ይሆን? እዚህ ላይ ይህ ግለሰብ እንዲህ ሲል የዛተው የፖለቲካ፣ የሃይማኖታዊ ወይም የአይዲዮሎጂ ዓላማን ለማራመድ በማሰብ በመንግስት ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ይሁን፣ አልያም ደግሞ እንዲሁ መተንፈሻ ያጣበትን ብሶት ለመተንፈስ በጥንቃቄ ሊጣራና ማስረጃ ሊቀርብበት ይገባል። ሆኖም ይህ ሁሉ እስኪሆን በግለሰቡ ላይ ሊደርሱ የሚችሉትን የነፃነት ገደቦች ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል። ለማንኛውም መዛት ከ15 ዓመት እስከ እድሜ ልክ እስራት፣ ብለም ሞት ሊያስቀጣ እንደሚችል ማወቅ የሚጠቅም ሲሆን አለማወቅ ደግሞ ከቅጣት አያድንም።

## መዋሸት 10 ዓመት ሊያስቀጣ እንደሚችልስ?

በቀን ውስጥ ስንቶቻችን ስንት ጊዜ እንዋሻለን? ምንም እንኳን ለመልካም ተግባር ሲባል (ሰው ለማስታረቅ) መዋሸት የተለመደ ቢሆንም በሥነ-ምግባር እንፃር አንድ ሰው እንዲዋሽ አይመከርም፤ ምክንያቱም ውሸት ወደተሳሳተ መንገድ ይመራናልና። የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁም በአንቀጽ 11 ላይ በሀሰተኛ የሽብርተኝነት ድርጊት ስለማስፈራራት የሚለው አለው።

«ማንኛውም ሰው ሀሰተኛ መሆኑን እያወቀ ወይም እያመነ የሽብርተኝነት ድርጊት እንደተፈፀመ ወይም እየተፈፀመ እንደሆነ ወይም እንደሚፈፀም በማናቸውም መንገድ ስሌላ ሰው ሆነ ብሎ የገለፀ እንደሆነ ከ3 እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡»

በርግጥም ያልተፈፀመን ነገር ተፈፀመ ብሎ መንዛት ህዝብን ሊያሸብር ይችላል፡፡ ነገር ግን የአነዛዙ ሁኔታ በዚህ አንቀጽ በግልጽ አለተቀመጠም፡፡ ለምሳሌ አቶ አበበ የተባለ ግለሰብ አቶ ከበደ ለተባሉ ግለሰብ «እንዲህ ቦታ ላይ እንዲህ ነገር ተከስቷል ሲል ሆን ብሎ ቢዋሻቸው የዋሾነቱን ሥነ-ምግባር ቢገልጽ እንጂ ምን ያህል ህዝብን የማሸበር አቅም አለው የሚለውን አያመላክትም፡፡ ይህንን ያልንበት ምክንያት ደንጋጌው አንድ ሰው ለሌላው ሰው የሚዋሸውንም ውሸት በማጠቃለሉ ሲሆን ይህም በማናቸውም መንገድ ሊፈፀም የሚችል መሆኑን በማስቀመጡ ነው፡፡ ከዚህ በላይ ደግሞ ደንጋጌው ከውጤት ይልቅ ለድርጊት ትልቅ ቦታ መስጠቱ ሰፊ ክፍተትን ይፈጥራል፡፡ አንድ ግለሰብ ወሸት ተናግሮ ሌላ አንድ (ወይም ብዙ) ሰው አስፈራርቷል ከተባለ የአስር ዓመት እስራት ሊገጥመው ይችላል፡፡ መፍራት በምን ይገለፃል፣ ይረጋገጣል የሚለውም ሌላ ጥያቄ ይሆናል፡፡ ለማንኛውም የሽብርተኝነት ድርጊትን በተመለከተ መዋሸት ቅጣት ያስከትላልና ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

## ውሸት እና ፕሬስ

ይህንኑ ከላይ የጠቀስነውን አንቀጽ ስንመለከት ከመገናኛ ብዙሃን ጋር የሚየገናኘ ው መሰረታዊ ነገር አለ፡፡ ደንጋጌው በግልጽ ባያስቀምጠውም «በማናቸውም መንገድ» በማለቱ ብቻ የመገናኛ ብዙሃን ወይም ፕሬስ ወይም ማንኛውም የህትመት ውጤት ሀሰተኛ መሆኑን እያወቀ (ወይም እያመነ) የሽብርተኝነት ድርጊት እንደተፈፀመ፣ እየተፈፀመ እንደሆነ፣ ወይም እንደሚፈፀም በዘገባም ሆነ በሌላ መንገድ ከገለፀ ተመሳሳይ እጣ ይገጥመዋል፡፡

በሕገመንግስቱ የተቀመጠው የፕሬስ ነፃነት ይከበርልኝ እየለ የሚታገል መገናኛ ብዙሃን በተለይ ሀሰተኛ መሆኑን እያወቀ ለህዝቡ ውሸትን የማስተላለፍ ሞራል ካለው በርግጥ የጋዜጠኛነት ቦታ አይገባውም፡፡ ነገር ግን ሀሰተኛ መሆኑን ስለማወቁና ዘገባውን ያስተላለፈው ሆነ ብሎ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ምንያህል ሥራ እና ቅንነት ይጠይቃል? በሌላ በኩል ማንኛውም መገናኛ ብዙሃን ለሚያቀርበው ዘገባ የተለያዩ ምንጮችን ይጠቀማል፤ ለምሳሌ በህትመት ውጤቶች ረገድ ከፍተኛውን ኃላፊነት የሚይዘው ዋና አዘጋጅ የደረሰው መረጃ ሀሰት ስለመሆኑ ለማወቅ ወይም ለማመን በቦታው ከመገኘት በቀር ምን አማራጭ አለው? እነዚህ ክፍተቶች በዋና አዘጋጅ ላይ ሊፈጥሩ የሚችሉት ጭንቀት ምን ያህል ነው? ይህ ሁኔታ በፕሬስ ያልተገደበ ነፃነት ላይ ሊያስከትለው የሚችል ተጽዕኖ ይኖር ይሆን?

# ሽብርተኝነትን ስለማበረታታት

በሽብርተኝነት በቻ ሳይሆን በሌሎችም ወንጀሎች ማበረታታት እራሱ እንደወንጀል የሚቆጠርባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁም የሽብርተኝነት ድርጊትን ስለማበረታታት የሚለው አለው፡፡ ሆኖም ከዚህ በመቀጠል የምትመለከቱት አንቀጽ 6 ከሌሎች የመገናኛ ብዙሃን ለይቶ የፕሬስ (የህትመት) ውጤቶችን በቀጥታ ይመለከታል፡፡

«ማንኛውም ሰው መልእክቱ እንዲታተምሳቸው የተደረገው የህብረተሰቡ አባላት በከፊል ወይም በሙሉ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 [ከላይ አስቀምጠነዋል] የተመለከተ ማናቸውንም የሽብርተኝነት ድርጊት እንዲፈጽሙ ወይም ለመፈፀም እነዲዘጋጁ ወይም እንዲነሳሱ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያበረታታቸው ወይም በማናቸውም ሌሳ ሁኔታ የሚገፋፋቸው እንደሆነ አድርገው ይረዱታል ተብሎ ሲገመት የሚችል መልእክት ሆነ ብሎ ወይም በግዴለሽነት ያተመ ወይም ያሳተመ እንደሆነ ከ10 እስከ 20 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡»

ይህ ድንጋጌ «ያተመ ወይም ያሳተመ» በሚልበት ሰዓት በተለይ የህትመት ውጤቶችን እንደሚመለከት ግልጽ ነው፡፡ «መልእክቱ እንዲታተምላቸው የተደረገው የህብረተሰቡ አባላት» የሚለውም የጋዜጣው ወይም የህትመት ውጤቱ አንባቢዎችን ሊያመለክት ይችላል፡፡ እናም ድንጋጌው እነዚያ አንባቢዎች ዛቻን ጨምሮ ከላይ በአንቀጽ 3 ስር የተዘረዘሩትን የሽብርተኝነት ድርጊቶች (አንዱን ወይም የተወሰኑትን ወይም ሁሉንም) «እንዲፈጽሙ ወይም ለመፈፀም አንዲዘጋጁ ወይም እንዲነሳሱ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያበረታታቸው ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ የሚገፋፋቸው እንደሆነ አድርገው ይረዱታል ተብሎ ሊገመት የሚችል መልእክት» የሚል ሀረግ በውስጡ ይዟል፡፡ አንባቢዎቹ የሚያበረታታቸው ወይም የሚገፋፋቸው «እንደሆነ አድርገው ይረዱታል ተብሎ ሊገመት የሚችል መልእክት» ምን ዓይነት መልእክት ነው?

አንድ የህትመት ውጤት ዋና ተግባሩ መረጃን ማስተላለፍና ሀሳብን የመግለጫ መድረክ እንደመሆኑ የፃፍኩትን አንባቢው በዚህ መልኩ ይረዳዋል ብሎ መገመት የአንባቢን ግንዛቤ መፈታተን አይሆንም? ማለትም «የተፃፈው እኮ የሚገፋፋ ነው» ብለው ይረዱታል ብሎ የህትመቱ ኃላፊ ጽሁፉን ከማሰራጨቱ በፊት ሊገምት ይገባዋል፡፡ በድንጋጌው ውስጥ «በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ» የሚለው ሀረግ የአዘጋገብ ሁኔታን ይሁን የአንባቢዎቹን የአረዳድ ሁኔታ ግልጽ አይደለም፡፡ ሆኖም የአዘጋገብ ሁኔታን ነው ብለን ብንወስደው «በቀጥታ» ሲል «ምን ትጠብቃላችሁ፤ ተነሱና የሽብርተኝነት ድርጊቶችን ፈጽሙ እንጂ!» ዓይነት ህትመቶችን ሲወክል «በተዘዋዋሪ» ደግሞ አንድ በሽብርተኝነት የተሰየመን ቡድን እንቅስቃሴ በዜና መልክ መዘገቡ አንባቢው ዘገባው የሚያበረታታው እንደሆነ አድርጐ ይረዳዋል ተብሎ ሊገመት የሚችል መልእክትን እንደማስተላለፍ መቆጠሩን የሚያመላክት ይመስለናል፡፡

እዚህ ላይ አንድ ምሳሌ መፍጠር ተገቢ ሳይሆን አይቀርም:: በሀገሪቱ የሆነ ቦታ ላይ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን በአዋጅ የተቀመጡትን የሽብርተኝነት ድርጊት መስፈርቶች የሚያሟላ ተግባር ፈፀመ:: መፈፀሙ ላይ ጥርጥር የለውም፣ በአንድ የህትመት ውጤት ላይ ዋና አዘጋጅ ሆኖ የሚሰራው አቶ አበበ (የተፈጠረ ስም ነው) የተባለው ግለሰብ በቦታው ተገኝቶ አረጋግጧል:: ውሸት አይደለም:: እናም አቶ አበበ (ዋና አዘጋጁ) ይህ ደርጊት በሀገሪቱ የሽብርተኝነት ሕግ ማስፈለጉን የሚያረጋግጥና ለመጽደቁም ትክክለኛነት ማሳያ ስለመሆኑ በማመኑ፣ ብሎም ወቅታዊና ተጨባጭ በመሆኑ ለዜና ብቁ እንደሆነ ወሰነ:: ዋና አዘጋጅ በሆነበት የህትመት ውጤት ላይም በፊት ገጽ ላይ እንዲወጣ አደረገ (የመገናኛ ብዙሃን እና የመረጃ ነፃነት አዋጅ ሙሉ የኤዲቶሪየል ሥልጣን ሰጥቶታልና)::

እንግዲህ ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባው የአዋጁ አንቀጽ 6 የሚያበረታታ ወይም የሚገፋፋ መልዕክት ስለማስተላለፍ በግልጽ አለማስቀመጡ ነው:: ድንጋጌው የሚለው የሚያበረታታቸው ወይም የሚገፋፋቸው «እንደሆነ አድርገው ይረዱታል ተብሎ ሊገመት የሚችል መልእክት» ነው:: የአገማመቱ ሁኔታ የሚከናወነው በማን ነው? ወደዋና አዘጋጁ አቶ አበበ ስንመለስ፣ ምንም እንኳን በህትመት ውጤቱ ላይ ያስተናገደው ዜና ያበረታታው ወይም የገፋፋው አንባቢ ባይኖርም ያ አንባቢ ዜናው የሚያበረታታ ወይም የሚገፋፋ እንደሆነ አድርጐ ይረዳዋል ተብሎ ከተገመተ ዜናው መተላለፉ ብቻ ከአስር እስከ 20 ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ሊያስከትል ይችላል፤ በወቅቱ የተበረታታም ሆነ የተገፋፋ ሰው ባይኖርም:: እዚህ ላይ አንድ የዜናው አንባቢ (ወይም ዜናው የተዘጋጀለት የህብረተሰብ አባል) ዜናው «ዛቻ» ለመፈፀም እንደሚያበረታታው ወይም እንደሚገፋፋው አድርጐ ይረዳዋል ተብሎ ከተገመተም ውጤቱ ተመሳሳይ ነው::

## ዋና አዘጋጅ፣ አታሚና አሳታሚ

በ2001 ዓ.ም በህዳር ወር በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ የወጣው የመገናኛ ብዙሃን እና የመረጃ ነፃነት አዋጅ የህትመት ውጤቶችን በተመለከተ ዋና አዘጋጅ ሙሉ የኤዲቶሪያል ሥልጣን እንዳለው ያስቀምጣል:: ይኸው አዋጅ ማንኛውም የመገናኛ ብዙሃን የሕግ ሰውነት እንዲኖራቸውና በአዲስ መልክ ምዝገባ እንዲያካሂዱም ደንግጓል:: ይህንን ድንጋጌ ለማስፈፀምም የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን የመመዝገቢያ ቅጾችን በሚያዘጋጅበት ወቅት የመገናኛ ብዙሃን ባለቤት (አሳታሚ ሊባልም ይችላል) ዋና አዘጋጅ መሆን እንደማይችል በአዋጁ መቀመጡን በመግለጽ፣ ይህም የሆነው የህትመት ውጤቶቹ በባለቤቶች አላስፈላጊ ተጽዕኖ እንዳይደርስባቸው መሆኑን ማስታወቁ ይታወሳል::

ከላይ «ሽብርተኝነትን ስለማበረታታት» በሚል ርዕስ ውስጥ ያስነበብናቹ የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁ አንቀጽ 6 «ሆነ ብሎ ወይም በግዴለሽነት ያተመ ወይም ያሳተመ» የሚል ሀረግ የያዘ ሲሆን በድንጋጌው መሰረትም ከአስር እስከ ሃያ ዓመት የሚደርስ ጽኑ አስራት ሊቀጣ የሚችለውም ያተመ ወይም ያሳተመ ሰው ነው:: እነዚህ አታሚዎች (ማተሚያ ቤቶች) ወይም አሳታሚዎች (የመገናኛ ብዙሃን ባለቤቶች) ሆን ብለው የፈፀሙት ተግባር ከሆነ የዋና አዘጋጁን ሥልጣን ከማጋፋታቸው ባሻገር በርግጥም ከተጠያቂነት አይድኑም:: ነገር ግን ስለግዴለሽነት ስናነሳ ከበስተጀርባው በህትመት ውጤቶቹ ላይ የሚወጡትን ነገሮች የመቆጣጠር ድርሻ ተሰጥቷቸው እንደነበር የማመላከት ጠባይን ያንፀባርቃል:: ይሁንና ግን በመገናኛ ብዙሃን እና የመረጃ ነፃነት አዋጅ አንቀጽ 6 (1) ላይ የህትመቶች ይዘትን የመቆጣጠር ሥልጣን ለዋና አዘጋጅ የተሰጠ ነው::

በነገራችን ላይ አንቀጹ ሰፊ ሁኔታዎች ሊያቅፍ የሚችል መሆኑን በመመርኮዝ ስለመገናኛ ብዙሃንና ስለፕሬስ አነሳን እንጂ ድንጋጌው በራሪ ወረቀቶችን በመጠቀም መልእክት ማስተላለፍንም ያካትታል:: ሆኖም ከፕሬስ ነፃነት አንፃር በአዋጁ ላይ ይቀርብ የነበረውን ከፍተኛ ትችት በተመለከተ በጥቂቱ እንዲህ ብለናል:: ለነገሩ ርዕሳችንን አጥብበን ይህንን አልን እንጂ ብዙ ነገሮች ሊባሉ እንደሚችሉ ብዙዎች ያምናሉ፣ ብዙዎችም ብዙ ብለዋል:: በዚች አጭር ጽሁፍ ግን ለማለት የሞከርነው ሕግ አውጪው የሰራው ይህ ሕግ በዛ ያሉ ክፍተቶችን ያቀፈ በመሆኑ በሌሎች የመንግስት አካላት በሚተገበርበትና በሚተረጎምበት ጊዜ አቅጣጫውን ሊስት የሚችልበት ሁኔታ ስለመፈጠሩ ለማታወስ፣ እንዲሁም በአንፃሩ ህብረተሰቡም ለሕጉ ትኩረት ሰጥቶ የተከለከለን ከተፈቀደ እንዲለይ ነው::

# «እንደ አመት በዓል የተከበረው ብላቴና!»

አቤ ቶኪቻው

abeto2007@yaoo.com

የታደለው ሜዳ አዲስ አበባ ስቴድየም የሰንደቅ አላማ ክብረ በዓልን ባስተናገደ በሳምንቱ ሌላ የተቀደሰ አላማ ቀንን አስተናገደ:: ሜዳው አንድ ጊዜ ሲፈጠር «በየሰበባ ሰበቡ በባንዲራ ድመቅ!» የሚል ንግር አለው መሰለኝ አንዳንዴ ቡና እና ጊዮርጊስ ሲጋጠሙ እንኳ የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ በጀርባው አንግቶ የሚመጣ ጎረምሳ ማየት የተለመደ ነው:: አሁን ለታም በአዲስ አበባ ስቴድየም የነበረውን ቅዱስ ስራ ላይ ለመሳተፍ ከመጡ «ወጣት የነብር ጣቶች!» ውስጥ በርካቶች ሰንደቅ አላማ አነግተው ሰንደቅ አላማ ለብሰው ነበር:: ይህንን የተመለከተ እንግዳ ሰው «ይህ በሰንደቅ የሚከበር ልዩ በዓል ምንድነው?» ብሎ መጠየቁ አይቀርም መልሱም «የአመቱ ቴዲ አፍሮ ነው!» ይሆናል:: ስለ ሰንደቅ

ካነሳን አይቀር በቴዲ ኮንሰርት ላይ ያጋጠመን የሰንደቅ ገጠመኝ የሚከተለውን ይመስላል፡-

***መንደርደሪያ***

ባለፈው ጊዜ የሰንደቅ አላማ አዋጅ ወጥቷል፡፡ አዋጁ በርካታ ህገ ደንቦችን የያዘ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ አንዱ «በአረንጓዴ ቢጫ ቀዩ ሰንደቅ መሃከል ላይ ከከብ የሌለውን ባንዲራ መጠቀም አይቻልም፡፡» የሚል ይገኝበታል፡፡ በዚህም ሁላችንም ተስማምተን፤ ባንስማማም «የመንግስትን አዋጅ እና ደንብ ማክበር ህገ መንግስቱን ማክበር እንዲሁም ልማታዊ ህዝብ መሆን ነው፡፡» ብለን ቀድሞ የነበረንን ኮከብ አልባ ባንዲራ ላይ እንደየ አቅማችን ኮከብ እየሳልንም የተሳለ እየገዛንም በመለጠፍ ለህገ መንግስታችን ያለንን ታማኝነት ለማሳየት ጥረት አድርገናል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ብለን እንቀጥል፡-

በድሮ ጊዜ

«የእኛ ሙሽራ ሹራብ ሰሪ
ወሰዳት አስተማሪ»

ተብለው የተዳሩ ባለሙያ እናቶቻችን በሚሰሩት ሹራብ ላይ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለም መቀላቀልን የጥራት ምልክት አድርገው ይዘውት ይሁን፣ ከቀለሙ ፍቅር ይዟቸው ይሁን ብቻ ነጭ ሹራብም ይስሩ ጥቁር በመሃከል የሰንደቃችን ቀለም በትንሹም ቢሆን አይጠፋም፡፡ እናቶቻችን ምንም እንኳ ለባንዲራ አዋጁ ቀንአዊ ስሜት ቢኖራቸውም ምንም እንኳ ኮከቧን ከእኛ ከልጆቻቸው እኩል ቢወዷትም በሰርጋቸው ሳይቀር ሞገስ ባገኙበት የሹራብ ስራ ግን ባንዲራውን ከኮከቧ ማዋሃድ አልቻል ብሏቸው እነሆ እስከዛሬም ኮከብ አልባ ባንዲራ ያለው ሹራብ እየሰሩልን እኛም ኮከቡን በልባችን ይዘን የእናቶቻችንን ሹራብ ስጦታ እየተቀበልን በመልበስ ይኸው የጥቅምቱን ብርድ እየተከላከልን እንገኛለን፡፡

***ገጠመኝ***

በእንዲህ አይነት መልኩ እናቱ የሰሩለትን ባለ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የሹራብ ስጦታ አክብሮ የለበሰ አንድ ወጣት የቴዲ ኮንሰርት በአዲስ አበባ ስቴድየም ሲደረግ ከተሰለፉት መሃከል ተገኘ፡፡ አንድ «የጸጥታ አስከባሪ» ተንደርድሮ ባለባንዲራ ሹራብ የለበሰውን ጎረምሳ ለማነቅ እየቃጣው «ይሔንን ሹራብ ለምን ለበስክ?» ሲል አይኑን በቁጣ አፍጥጦ ጠየቀው፡፡ ወጣቱ በህይወቱ እንዲህ ደንግጦ አያውቅም (እዚች ጋ ቃል አጋኖ እናድርግ) ብቻ ደነገጠ፡፡ እናም መናገር ተስኖት ዝም.. ፖሊሱ ድጋሚ ጠየቀው «ይሔንን ሹራብ ለምን ለበስክ?» ወጣቱ የሞት ሞቱን «ብርድ ስለሆነ!» ሲል መለሰ፡፡ ጸጥታ አስከባሪው በወጣቱ ንግግር በሸቀ፡፡ ከሰልፉ መሃከልም አውጥቶ ከከብ የሌለው አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ልብስ መልበስ ተገቢ አለመሆኑን «መክሮት» መለሰው፡፡ ወጣቱ ሲመከር ያየ ሌላ ወዳጃችን የራሱን አለባበሰ ልብ ብሎ ሲመለከት ለካስ የለበሰው ባንዲራ ነው፡፡ አረንጓዴ ሹራብ ቢጫ ቀበቶ እና ቀይ ሱሪ፡፡ ወዳጃችን በጸጥታ አስከባሪ «መመከር» አጥብቀው ከሚፈሩት መሃከል ነበርና ከሰልፉ ውስጥ ሹልክ ብሎ ወጣ ቆይቶ ሲመለስ የት ተሰውሮ

እንደመጣ ብንጠይቀው ንቅሳት የሚሰሩ ሰዎች ዘንድ (ታቱ ቤት) መሄዱን ነገረን ምን ፍለጋ? ብለን ስንጠይቀው አረንጓዴ ሹራቡን ገልጦ አሳየን እንብርቱ ላይ ኮከቧን ተነቅሷታል። አሁን የወዳጃችን አለባበስ አረንጓዴ ሹራብ ኮከብ እንብርት ቢጫ ቀበቶ ቀይ ሱሪ ሆነ ማለት ነው። እንዲህ ሁላችንም ህግ እና ህገ መንግስት ላማክበር ብንተጋ የት እንደርስ ነበር!?

ወዳጄ እርስዎ እንዴት ሰንብተዋል? «በጥቅምት አንድ አጥንት!» ቆረጠሙ ወይስ በእቅድ ደረጃ ተይዟል? አይዞት ሃገራችን ለተከታይ ስድስት አመት ካስመዘገበችው «ባለ ሁለት ዲጂት» እድገት ቢያንስ ለጥቅምት የሚሆን አንድ አንድ አጥንት ሳይዳረሰን አይቀርም የሚል ነገር በሹክሹክታ ሰምቻለሁኝ።

እኔ የምለው ወዳጄ... የቴዲ አፍሮ ኮንሰርት እንዴት አዩት? የሚገርም ብላቴና ነው። እውነቱን ለመናገር የሃገር ሃብት የሆነ ልጅ ነው። በርግጥ እኔ ወደ ስቴድየም ለመግባት ዕድሉን አላገኘሁኝም ነገር ግን በዕለቱ በስቴድየሙ ዙሪያ ባሉ ጨዋታ ቤቶች እና በአካባቢው የመገኘት ዕድል ገጥሞኝ ነበር። ከአርባ ሺህ ሰው በላይ በስቴድሙ ቅጥር ግቢ ከገባ በኋላ ከገባው የሚበልጥ ህዝብ ደግሞ በስቴድየም ዙሪያ ነበር። በውጪ ካሉት ውስጥ ጥቂት እድለኞች የስቴድየም ዙሪያ ጨዋታ ቤቶችን ወንበር፣ ድራፍት እና ቢራ ለመጨበጥ ታድለዋል። ሁሉም በአንድነት ስለ ብላቴናው ይዘምራል። በጨዋታ ቤቶቹ ውስጥ

«የምትበሉ ብሉ የምትጠጡ ጠጡ
በቴዲ ላይ ብቻ ግርግር አታምጡ
ቴዲዬ አንተን ያለው ማነው
ሰው ነገረኛ ነው

አለምሽ ዛሬ ነው ዛሬ ... ኢትዮጵያ ሃገሬ»። እየተባለ ሲዘፈን እና ምስሉን የያዘ ቲሸርት እንዲሁም ስሙ የተፃፈበት ሪባን ሺቸበቸብ የተመለከተ አንድ ወዳጄ «እንደ አመት ባል የተከበረ ብላቴና!» ብሎታል። እውነት አለው። ይህ «እንደ አመትባል የተከበረ ብላቴና!» ያዘጋጀው ኮንሰርት «ገቢው በሃገራችን ልመናን ለማስቀም እንዲያግዝ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።» በእውነት እንዲህ ያለው ነገር በሌሎች ታዋቂ እና ተወዳጅ ሰዎቻችንም ዘንድ ቢለመድ መልካም ነው።

በርግጥ በተለይ አብዛኞቹ አርቲስቶቻችን እንኳንስ እንዲህ ባለው ግዙፍ መድረክ ይቅርና በ«ከተፋ ቤቶች»ም እንኳ የራሳቸውን ዘፈን አስመስሎ መዝፈን የሚያቅታቸው ስለሆኑ በእንዲህ አይነቱ በጎ ስራ ላይ በፀሎት ያግዙን እንደሆነ ነው እንጂ በኮንሰርት የሚታሰብ አይደለም። ለማንኛውም ግን ሁሉም የበኩሉን በአቅሙ እገዛ ቢያደርግ ድህነትን ልመናን በካልቾ የምንመታበት ጊዜ ቅርብ ነው። ብላቴናው እንዳለው «ኢትዮጵያ የምትነሳበት ባቢሎን የምትወድቅበት»ን ጊዜ በመተባበር ማፋጠን ይቻላል ማለት ነው።

በነገራችን ላይ ኮንሰርቱ በግልም ሆነ በመንግስት ሚዲያዎች ሰፊ ሽፋን ተሰጥቶት ይበል የሚያሰኝ ስራ እንደተሰራ ሲወደስ ሰንብቷል፡፡ ታድያ በመንግስት ሚዲያዎች (በቅንፍ ያው የመንግስት ሚዲያዎች በማለት የጠቀስነው ኢቲቪ ብሎ ስም ላለመጥቀስ መሆኑን ማስታወስ ይገባል፡፡) ዘገባው ሲቀርብ «ገና ምን አይታችሁ ምቀኛ አይኑ ይፍዘዝ እና ለስድስት አመታት የዘለቀው ባለሁለት ዲጂቱ እድገት ለሰባተኛ አመትም ይረጋገጣል!» በሚል መፈክር ታጅቦ ነበር፡፡ ይህንን ልብ ያለ አንድ ወዳጃችን ምን እንዳለ ያውቃሉ? «ኮንሰርቱ «በተከታታይ ለተመዘገበው» ባለ ሁለት ዲጂት እድገት የደስ ደስ ነው እንዴ የተዘጋጀው?» አለን፡፡ እኛም የባለ ሁለት ዲጂቷ አድናቂዎች ይህንን የሀገሪቱን እድገት ሲያይ አይኑ የሚቀላ ምቀኛ በተናገረው ንግግር ከገሰፅነው በኋላ «አይዲያውን» ግን ከሰሞኑ ለመጠቀም አስበናል፡፡ እናም በቅርቡ ለባለ ሁለት ዲጂቱ እድገት የደስደስ ኮንሰርት ተዘጋጀ የሚል ማስታወቂያ ከሰሙ አዘጋጆቹ እኛነን ማለት ነው፡፡ እናም «ኑ ኑ ኑ...» ብለናችኋል፡፡

ወዳጄ ወደመጨረሻ ወሬዎቻችን እናምራ፡-

በመጨረሻም 1

ባለፉት ሳምንታት ከአሁን አሁን አወጋዎታለሁኝ እያልኩኝ ቀልብ በማጣት ስረሳው የነበረ አንድ ጉዳይ የዛሬው መጨረሻ ላይ ላንሳው፡፡

እኔ የምለው ዘንድሮም የተራብ ሰው ቁጥር ይጭበረበራል? (ልብ አድርጉ አጭበርባሪዎቹ የተለየ አጀንዳ ያላቸው ተራድኦ ድርጅቶች እንጂ መንግስት ነው አላልኩም፡፡ ወደፊትም አልልም፡፡ ነገር አልፈልግም፡፡) አልገባህ የሚለኝ ነገር ግን እነዚህ «የተለየ አጀንዳ ያላቸው» ሰዎች ሁልጊዜ እኛ ሳንራብ ተራቡ የሚሉበት ምክንያት ነው፡፡ እኛ ጥጋብ በጥጋብ ሆነን «ምግብማ ሞልቷል» በሚለው ሙዚቃ ስንጫፈር እነርሱ የርሃብተኛን ቁጥር ሰማይ እየሰቀሉ ለምን እንደሚያሳጡን አይገባኝም፡፡ የምፈራው እነዚህ የጥፋት ሃይሎች ቁጥር በመጨመር አባዜያቸው ሁለት ዲጂት እድገት ስንል ሰምተው አስራ ሁለት ዲጂት እድገት እንዳይሉ እና ራሳቸው ጉድ እንዳይሆኑ ነው፡፡

**በመጨረሻም 2**

ትምህርት ሚኒስቴር ባለፈው ሰሞን የርቀት ትምህርት እያስተማሩ ያሉ ኮሌጆችን በአንድ ደብዳቤ «ከ2002 ጀምሮ እውቅናችሁ ተነስቷል፡፡ ከዚህ በኋላ በርቀት ትምህርት በተለይ «ቲቪኢቲ» ፕሮግራም ብትሰጡ ወዮላችሁ!» ሲል አስጠንቅቋል፡፡

ይህንን ተከትሎ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማህበር የትምህርት ሚኒስቴርን ደብዳቤ «አይሰማም» በሚል ዜማ የአቋም መግለጫ አውጥቶ አጣጥሎታል፡፡ ታድያ ኢቲቪ የማህበሩን መግለጫ በልማታዊ ቋንቋ ተርጉሞ ዘገበው አሉ፡፡ ማኅበሩ «አረ ተዉ ባትነኩን ምን አለበት ትምህርት ሚኒስትሮች ስራ እንስራበት» ብሎ ያለውን ቴሌቪዥናችን «የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትህርት ሚኒስቴር የወሰደውን እርምጃ አደነቀ፡፡» ብሎ ዘግቧል፡፡ ታድያ ይህንን በቅርበት የተከታተሉ ሰዎች በኢቲቪ ቋንቋ

«አደነቀ» ማለት ተቃወመ ማለት ከሆነ ለሌሎቹም የኢቲቪ ንግግሮች መዝገበ ቃላት ቢዘጋጅ ጥሩ ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። መዝገበ ቃላት አዘጋጆች ሃሳቧን ብትጠቀሙባት ጥሩ ነው። ከአማርኛ ወደ እንግሊዘኛ ከኦሮምኛ ወደ እንግሊዘኛ እንደሚባሉት አይነት ከኢቲቪ ወደ ገሃዱ አለም የሚተረጉም መዝገበ ቃላት ብታዘጋጁ አሪፍ ቢዝነስ ይመስለኛል።
ወዳጄ ይበቃህ በሉኝ እና እንሰነባበት!
አማን ያሰንብተን!

# ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት

# ለአንዱ ወንጀል ለሌላው መብት

በታምራት ታረቀኝ

ሰው ሆነን በመፈጠራችን የተቀዳጀነው ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት የአለቃና የምንዝር የጌታና የሎሌ የባለሥልጣንና የተራ ዜጋ ተብሎ መስፈርት ሊወጣለት ገደብ ሊደረግበትና አመሳሶ ሊበጅለት አይገባም። የሰውን ሀሳብን በነጻነት መግለፅን ከሥልጣን ጥማታቸው አንፃር የጦር ያህል የሚፈሩት አንባገነነኖች ይህን የሰው ልጅ ሰው በመሆኑ የተቀዳጀውን መብት ለማፈን በመጣጣር ኢ- ዴሞክራሲያዊነታቸውን ማጋለጥ ብቻ ሳይሆን አዳዲስ የነፃነት ጥያቄዎች እንዲነሱ የመብት ትግሎችም እንዲቀጣጠሉ ያደርጋሉ።

ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብታችን በገዢው ፓርቲ እየተገደበ ነው። ዴሞክራሲያዊ መብታችን እየታፈነ ነው። በማለት የሚጮኹት ተቃዋሚዎች እነርሱ በበኩላቸው በሚመሩት ፓርቲ ውስጥ ከእነርሱ ፍላጎት ውጪ የሚሰራ ለማየት እነርሱን ከሚያስደስት ሀሳብ በስተቀር ለማዳመጥ የማይሹ በዚህም ከውግዘት እስከ ማባረር የሚደርሱ መሆናቸው ነው።

አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ በጥቅምት 3/2002 ዕትሙ አንድነት ፓርቲ ዋና ጸሐፊው «አንድነት የብርቱካንን እስራት ለምርጫ 2002 ቅድም ሁኔታ አድርጎ አያቀርብም» በማለት የተናገሩትን ማስተባበሉን አስነብቧል። ለዜናው ምንጭ አድርጎ የጠቀሳቸው ማስተባበል የማይሰለቻቸው ዶ/ር ኃይሉ አርዓያ ናቸው። ዶ/ር ኃይሉ «ዋና ፀሐፊው የተናገረው የግል ሀሳቡን ነው። ሐሳቡን የመግለፅ ዴሞክራሲያዊ መብት አለው» ብለዋል ። የፓርቲን ውሳኔ የሚጠይቅ ጉዳይን በዘፈቀደ ምርጦቹ አመራሮች ባሰኛቸው ሰዓት እንዲናገሩ የሚፈቅድ ነፃነት አንድነት ውስጥ ተፈጥሮ ከሆነ የጉዳዩ ሥርዓት አልበኝነት

ማነጋገሩን ለጊዜው ትተነው ሀሳብን በመግለፅ ነጻነት አፈጻጸም ላይ በአንድነት ፓርቲ ውስጥ ያለውን እጅግ የተራራቀና ህገ ወጥ የሆነ ድርጊት የዶ/ር ኃይሉን አነጋገር መነሻ አድርገን እንነጋገር፡፡

አቶ አስራት ጣሴ በሀገረ ስውዲን የሚደመጥ የአማርኛ ፕሮግራም ያለው ራዲዮ ጣቢያ ቃለ ምልልስ ሲያደርግላቸው የሚናገሩት ነገር በአንድ ጊዜ በአለም ሁሉ መሰራጨት የመቻሉ የዘመኑ ተክኖሎጂ ምስጢር ሳይገባቸው ቀርቶ ወይንም የማን አለብኝነት ስሜታቸው የደረሰበት ደረጃ ይህን ለማገናዘብ አላስችል ብሏቸው እንጂ «አንድነት ብርቱካንን ለምርጫ 2002 በቅድመ ሁኔታነት አያቀርብም» ሲሉ ክህደታቸውን በድፍረት በአየር ላይ ነዙት፡፡ በዚህም ሳያበቁ እንኳን አንድነት፤ አንድነት አባል የሆነበትም መድረክ ይህን አያደርግም፡፡ ፖለቲካውን ያሳንሰዋል አሉ፡፡

ይህ ማስተዋል የጎደለው ወይንም እብሪት የተጫጫነው አባባል የዘመኑን የመረጃ ተክኖሎጂ በሚጠቀሙ በተለይ ከሀገር ውጪ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ሁሉ ደረሰና ቁጣ ቀሰቀሰ፡፡ ቀድመው ለማስተባበል ድረ ገፆች ላይ የታዩት ኢ/ር ግዛቸው ናቸው፡፡ ዜናው በሀገር ውስጥ ጋዜጦች ላይ መነበብ ሲጀምር ደግሞ ዶ/ር ኃይሉ አርዓያ በአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ላይ ብቅ አሉ፡፡

ዶ/ር ኃይሉ የአቶ አሥራትን ንግግር ከማስተባበላቸው በፊት የራሳቸውን አቋም ግልፅ ማድረግ ይገባቸው ነበር፡፡ አዋሳ ስብሰባ ላይ እሳቸውም እንደ አቶ አሥራት «ብርቱካንን ለምርጫ ቅድመ ሁኔታ አናቀርብም በማለት የተናገሩትን ተመሳሳይ ንግግር ሀሳብን በነጻነት የመግለፅ መብትን ተጠቅሜ የግሌን ነው የተናገርኩት፡፡ ፓርቲውንም ሆነ የእኔን ቃል አቀባይነት አይመለከትም ማለት ይችላሉ፡፡ እሳቸውም ሁሉን ነገር ማድረግም ሆነ መንገር ከሚቻላቸው ወገኖች በኩል ናቸውና፡፡

የአቶ አስራትን ንግግር ዶ/ር ኃይሉ ሲያስተባብሉ ይህ የመጀመሪያቸው አይደለም፡፡ ከዚህ ቀደም  አውራ አምባ ታይምስ ጋዜጣ ቃለ ምልልስ አድርጎላቸው እንዳሻቸው መናገር የማይታክታቸው አቶ አሥራት ጣሴ ቀጥሎ የተመለከተውን ተናገሩ፡

- ብሄራዊ ምክር ቤቱ ተቀብሎ የውሳኔ ሀሳብ እንዲቀርብለት ኮሚቴ ያቋቋመበትን በእነ ፕ/ር መስፍን የተጻፈ ችግር አመላካችና መፍትሄ ጠቋሚ ፅሁፍ የማይረባ ትርክ ምርኪ የታጨቀበት ሲሉ አንቋሸሹ፡
- አባላትን ባዕድ አካል ፓርቲ አፍራሽ ተቧድነው የመጡ ወዘተ በማለት ወነጀሉ፡
- የሥራ አስፈፃሚ አባል በሆኑት በአቶ አምሀ ዳኘው ላይ በቅርብ ጊዜ እርምጃ እንደሚወሰድ ገለፁ
- ለዚህ ሁሉ ህገወጥ ተግባር የሚያበቃቸውም የፖለቲክ ውሳኔ እንደሆነ በመሆኑ ከዚህ በኋላ የፓርቲ ደንብ ማክበር የትም አያደርሰንም የፖለቲክ ውሳኔ እንወስናለን አሉ፡፡

ይህ ንግግር ተሰምቶ ለገንዘቡ ሲሉ ከሚፈሩትና ከሚታዘዙለት ወገን በኩል ተቃውሞ ሲመጣ ዶ/ር ኃይሉ በለመዱት መንገድ ይህ የፓርቲው አቋም አይደለም አሥራት የተናገረው የግሉን ነው:: ሀሳቡን የመግለፅ መብት አለው አሉ:: የሰሞኑም የፓርቲ ውሳኔ የሚጠይቅ ግን በአቶ አሥራት ማን አለብኝነት የተነገረ ነገር የፓርቲው አቋም አይደለም:: አቶ አሥራት ግን መናገር መብቱ ነው ሲሉ አስተባበሉ::

ከአንድነት ፓርቲ በመታገድ የመጀመሪያው የሆኑት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባሉ አቶ አመሀ ዳኘው ናቸው:: አቶ አመሀ ለዚህ የበቁት ደግሞ ሥራ አስፈፃሚው በአደባባይ ከመድረክ ጋር ተቀላቅለናል ብሎ ባወጀበት እና የተለያዩ የፓርቲው አመራሮች በየጋዜጣው በተናገሩት ጉዳይ ላይ የግል አስተያየታቸውን በሰንደቅ ጋዜጣ ላይ በመፃፋቸው ነው:: አቶ አስራት ለአውራምባ ታይምስ እና በስውዲን ሀገር ለሚገኝ ራዲዮ ጣቢያ የተናገሩት ከላይ የተጠቀሰው አባባል ሀሳብን በመግለፅ ነፃነት ስር ከዋለ የአቶ አምሀ ወንጀል ሆኖ ለእግድና ለማባረር ያበቃበት ምክንያት ምን ይሆን ?

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እኔ ከፓርቲው እንድታገድ የተደረኩትና በግንባር ቀደምትነት የተባረርኩት ጉግል በሚባለው ሳምንታዊ ጋዜጣ ላይ ዶ/ር ያዕቆብን የተመለከተ አስተያየት በመፃፌ ነው:: በጽሁፌ ያነሳሁት ነጥብ ዶ/ር ያዕቆብ ወ/ት ብርቱካን በፖሊስ ስትጠራ መልቀቂያ ማቅረባቸውና ስትታሰር መመለሳቸውን፡ መድረክን አስመልክቶ የዘጠኝ ወር ጥረታቸው ተሳከ ዶ/ር ያዕቆብ አሸነፉ ተብሎ በየጋዜጦች የተፃፈውን አስመልክቶ ነው:: ታዲያ ይህ እንዴት ሆኖ ነው አቶ አስራት ከተናገሩት በላይ የከፋ ወንጀል ሆኖ ለመባረር የሚያበቃው:: ስለ ብርቱከን መናገር መብት ስለ ዶ/ር ያዕቆብ መናገር ወንጀል!!

አንድነት 22 የአመራር አባላቱን በማባረር አዲስ ክብረ ወስን ያስመዘገበበት እርምጃ የተወሰደው በፓርቲው ውስጥ አሉ ያሉዋቸውን ችግሮች የሚገልፅና መፍትሄ የሚያመላከት ፅሁፍ በማቅረባቸው ነው:: እንግዲህ እኔ የምላችሁን ብቻ ዝም ብላችሁ ተቀበሉ ማለት መሆኑ ነው::

ከዚህ ድርጊት የምንረዳው አንድ ግልፅ ጉዳይ ቢኖር አንድነት ውስጥ «ሁሉም ሰዎች እኩል ናቸው ይበልጥ ሰዎች ደግሞ እኩል ናቸው» የሚለው አባባል በተግባር የሚሰራ መሆኑን ነው::

ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት ለሁሉም የሰው ልጆች በሁሉም ቦታ በዕኩልነት ተግባራዊ ሊሆን የሚገባው ቢሆንም አንባገነኖች ሥልጣን ሲጨብጡ ይረገጣል ይታፈናል:: ይህን የትግላቸው አንድ አካልና አንገኳር ጉዳይ አድርገው ሊታገሉ መመስረታቸውን የሚናገሩ ተቀዋሚዎች እንቃወመዋለን የሚሉትን ድርጊት ራሳቸው ሲፈፅሙት ማየት ከዛሬው ጉዳታችን በላይ የነገ ተስፋችንን ያጨልመዋል::

ሀሳብን የመግለፅ ነፃነትን ከታማኝነት አንፃር ተፈፃሚ የሚያደርጉ፣ በሀሳብ የተለያቸውን ለትግል እንጂ ለሎሌነት ያለመሰለፉን በተግባር የሚያሳየውንና

ለሥልጣናቸው እንቅፋት መስሎ የተሰማቸውን የፓርቲ አባል ለማባረር ህግ የሚጥሱ መርህ የሚያዛቡ ተቀዋሚ ፖለቲከኞች ምኒልክ ቤተ መንግሥት የመግባት እድሉ ቢገጥማቸው ምን ሊሰሩ እንደሚችሉ አንባቢ የየራሱን ግምት ይውሰድ::

ገዚው ፓርቲ ከሚወቀስበትና ከሚከሰስበት ጉዳይ አንዱ ለሥልጣኑ የሚያሰጋ መስሎ እስካልታየው ድረስ ማንም የፈለገውን ቢናገር የትኛውንም ህግ ቢጥስ አይቶ እንዳላየ ያልፋል:: ሲለውም ለዴሞክራሲ ጀማሪ ስለሆንን ነው:: ዜጎች መብታቸውን እየተለማመዱ ነው በማለት ያልፈዋል::

ለሥልጣኑ የሚያስፈራ ሆኖ ሲሰማው ግን ዜጎች ትክክለኛ መብታቸውን ተጠቅመው ህግ ሳይተላለፉ የሚፈፅሙትን ህጋዊ ተግባር የተለያየ ሥም በመስጠት ይወነጅላል ያስራል ከስራ ያባርራል የሚል ነው:: ይህን ተቃውሞ የሚያሰሙት ተቀዋሚዎች በራሳቸው ቤት የተቀዋሚ ወንበር ሥልጣን ሆኖ የፈሯቸውን በተለያየ ሥም በመወንጀል ከፓርቲ ያባርራሉ:: ለታማኞቹ መብት የሆነ ለሌሎቹ ወንጀል ሆኖ ያስከስሳል ከፓርቲም ያስባርራል:: ከዚህ ያለፈ ለማድረግ የሚያስችል ሥልጣን የሌላቸው መሆኑ በጀ እንጂ እንደ አያያዛቸውና አነጋገራቸው ቢሆን አስከፊ የታሪካችን ገፅታ ዛሬም ይደገም ነበር:: አንድነት 22 የአመራር አባላቱን አባረረ የሚለውን ዜና በተሰማበት ወቅት በጉዳዩ በጣም ያዘኑ የፓርቲው አባላት በጋራ ሁነው ሶስት የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ አባላት ጋር ስልክ ደውለው ነበር:: ዶ/ር ያዕቆብ እኔ በድርጊቱ የለሁበትም በውይይት እንዲፈታ ነበር የምፈልገው:: አሁንም ጠንከራ ሰዎች ይዛችሁ ቀጥሉ በማለት ተስፋ ሲሰጡአቸው ኢ/ር ግዛቸው ግን ረፍዷል በማለት ጠ/ሚ መለስ ይሉን የነበረውን አይነት መልስ ሰጧቸው:: እነኚሁ አባላት በሶስተኛ ደረጃ ያነጋገሩት የፓርላማ አባሉ አቶ እንዳልከቸው ደግሞ በተወሰደው ርምጃ ሁሉ ደስተኛ ነኝ :: ከዚህ ሌላ ሊወሰድ የሚችል እርምጃ ቢኖርና ቢወሰድም ደስተኛ ነኝ አሉአቸው::

እንግዲህ በሌላው ላይ ይህን የሚሉት የፓርቲው አመራሮች የአቶ አስራት የትናንቱ የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ዘገባ እና የዛሬው የስውዲን ራዲዮ ንግግር ምንም ማለት አይደለም:: ምክንያቱም የንግግሩም የድርጊቱም ተባባሪዎች ናቸውና::

በበኩሌ ዶ/ር ኃይሉ ፓርቲውን ለውድቀት በሚዳርግ አሳዛኝ ተግባር ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሚናገሩትን በየጊዜው ለማስተባበል ከመቸገር ይልቅ የአፍ ወለምታ የሚያበዙ አመራሮችን መልክ ለማስያዝ ቢታገሉ ሳይበጅ አይቀርም:: ከእነርሱ ታማኝነት የፓርቲው ደህንነት መቅደም ይኖርበታል::

የአንድነት አመራሮች ሀሳብን በመግለፅ ነፃነት ላይ ያላቸውን አቅዋም እንዲሁም ሀሳብን የመግለጽ ነጻነት ለአንዱ ወንጀል ለሌላው መብት የሚሆንበትን ምክንያት እንዲያጣሩ ከጋዜጠኞች ብዙ ይጠበቃል:: ለሚቀጥለው ምርጫ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ብርቱኳንም ታስራ እንወዳደራለን እያሉን ነው:: ሀሳብን በመግለፅ ነፃነት ላይ ልጅና የእንጀራ ልጅ

መድልዎ የሚያሳዩ ፖለቲከኞችን ለመምረጥ የሚፈቅድ ይኖራል ተብሎ ይጠበቃልን? ይህ ከወዲሁ ግልፅ መሆን ይኖርበታል።

# ኢህአዴግ፣ ምርጫ 2002 እና የወ/ሪት ብርቱካን ጉዳይ

**በግርማ ካሳ**

**(ከቺካጎ)**

ምርጫውን በተመለከተ የተለያዩ አስተያየቶች እየተሰጡ ነው። በተለይም የአንድነት ፓርቲ ዋና ጸሃፊ አቶ አሥራት ጣሴ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ዙሪያ የሰጡት ቃለ መጠይቅ ትንሽ እሳትን እንደለኮሰ እያየን ነው። (ምንም እንኳን ኢ/ር ግዛቸውን ጨምሮ ሌሎች አመራሮች እሳቱን የማጥፋት ሙከራ እያደረጉ ቢሆንም)

በውጭ አገር ካሉ የአንድነት ደጋፊዎች እንዲሁም በተለያዩ የፓልቶክ ክፍል ያሉ ኢትዮጵያውያን የሚሰጡት አስተያየቶችና በየድረ-ገጾች የሚጻፉ ጽሁፎች የሚያመለክቱት ነገር ቢኖር፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በታሰረችበት ሁኔታ ወደ ምርጫው መግባት ትልቅ ተቃውሞን ሊያስነሳ እንደሚችል ነው።

በአገር ቤትም ተመሳሳይ ሁኔታ ያለ ይመስላል። የአውራምባ ታይምሱ አቶ ዳዊት ከበደ ላቀረበላቸው ጥያቄ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ሲመልሱ «ብርቱካን የአንድነት ሊቀመንበር ነች። መሪያችን ነች። ስለዚህ እሷን ከሌሎች ሰዎች ጋር አናያትም በመሪነቷ፣ በእናትነቷና በመስራችነቷ ለብቻዋ ነው የምንመለከታት። እና እርሷን እሥር ቤት አስገብተን ምርጫ ሊኖር አይችልም የሚል አስተሳሰብ እና አቋም ነው ያለን።» ነበር ያሉት።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የታሰረችው ለአንድ አላማ ነው። እርሱም በኢትዮጵያ ሕግ የበላይ ሆኖ፣ የዜጎች መብት ተከብሮ በነጻነቷና በአንድነቷ ታፍራና ተከብራ የምትኖር አንዲት የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመመስረት ነው። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ከሁሉም በላይ የእርሷ መታሰር ሳይሆን የሚያሳስባት፣ የታሰረችበት ዓላማ ከግቡ የመድረሱና ያለመድረሱ ጉዳይ ነው እንጂ። ይህማ ባይሆን ኖሮ መጀመሪያውኑ እውነትን ሰርዛ፣ ያልሆነውን ሆነ ብላ አገዛዙ የጠየቃትን አሟልታ አለመታሰር ትችል ነበር።

እስቲ ትንሽ አእምሮቻችን እንዲጫር አንዳንድ ጥያቄዎችን ላቅርብ። እርስ በርስ ሳንስማማና አንድነት ሳይኖረን፣ ዝም ብለን ወደ ምርጫው ብንገባ ምን የምናመጣው ለውጥ አለ? በእውኑ አቶ አሥራት ጣሴ እንዳሉት አሁን ባለው አሳዛኝ የፖለቲካ ሁኔታ ምርጫውን አሸንፈን ብርቱካን ሚደቅሳን ማስፈታት እንችላለን? በአገር ቤት እነ

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም፣ በውጭ አገር ደግሞ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች እንደሚሉት፣ ከምርጫው እራሳችን ብናገል ደግሞ ምን ጥቅም እናገኛለን? ምርጫ ውስጥ አለመግባታችንስ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ሊያስፈታት ይችላልን?

ቁም ነገሩ ምርጫ መግባቱና አለመግባቱ ላይ አይደለም:: እኛ አንድነትና ጥንካሬ ከሌለን ምርጫ ገባን አልገባንም ምንም ለውጥ አናመጣም:: ገዢው ፓርቲ ስልጣን ከተቆናጠጠ አሥራ ስምንት አመት አልፎታል:: (ደርግ በሥልጣን ላይ ከነበረበት ጊዜ የበለጠ) አንዳንዶቻችን ይህ የሆነበት ምክንያት ጠመንጃ ስላለው ነው እንላለን:: አይደለም:: ገዢው ፓርቲ በሥልጣን ላይ ያለው በተለያዩ መንገዶች ህዝቡንና ጠንካራ ተቃዋሚዎችን መከፋፈል በመቻሉ ነው:: አሁንም ከአሥር ወራት በኋላ ይደረጋል የሚባለው ምርጫ እየከፋፈለን እንደሆነ በግልጽ እየታየ ነው:: «ብርቱካን ሚደቅሳ ካልተፈታች ምርጫ አንገባም፣ ወይ እንገባለን» እያለን የምንጨቃጨቅና የምንከፋፈል ከሆነ፣ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ መታሰር እስከ አሁን እንደነበረው የአንድነታችን ምክንያት መሆኑ ይቀርና የመለያየታችን ምክንያት እየሆነ በመምጣት ላይ እንዳለ እናያለን:: እኔ እንደማምነው ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የታሰረችው ለዚህ አልነበረም::

ገዢው ፓርቲም እርሷን አስሮ እርሷ ካልተፈታች «ምርጫ እንግባ፣ አንግባ» የሚል ግጭት በተቃዋሚዎች ውስጥ በቀላሉ መዝራት ከቻለ፣ ገዢው ፓርቲ እርሷን የሚፈታበት ምንም ምክንያት አይኖረውም:: የርሷ መታሰር አሁን እንዳለው ተቃዋሚዎችን የሚሰነጣጥቅም ከሆነ፣ ምን ቸገረውና፣ እርስ በርስ እያጋጨ ስልጣኑን ያራዝማል እንጂ፣ ብርቱካን ሚደቅሳን ይፈታታል? ደግሜ እጠይቃለሁ በዚህ ሁኔታ ኢህአዴግ ለምንድነው ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን የሚፈታት?

ስለዚህ ከአሥር ወራት በኋላ በሚደረገው ምርጫ ዙሪያ አሁን እየተደረገ ያለው ክርክር ትግልን የሚጠቅም ክርክር ሳይሆን ትግሉን የሚጎዳ፣ የምንወዳትና የምናከብራት የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የቃሊቲ አሰቃቂ ኑሮን የሚያራዝም፣ አምባገነኖችን ጮቤ የሚያስረግጥና ያለምንም ጥርጥር ገዢውን ፓርቲ የሚጠቅም ወቅታዊ የሆነ ክርክር ነው:: ስለሆነም ሁላችንም ቆም ብለን እንድናስብና መሰረታዊ የሆኑ ጥያቄዎችን ለራሳችን እንድንጠይቅ ያስፈልጋል::

ይህን ብዬ ወደፊት እንድንራመድ ይረዳን ዘንድ፣ ይጠቅማሉ የምላቸውን የሚከተሉት ስምንት ሃሳቦች በአክብሮት አቀርባለሁ::

1. ምርጫው አሥር ወራት ይቀሩታል:: በመድረክ ውስጥ ያሉ ድርጅቶች እንዲሁም መኢአድ በምርጫ እንሳተፋለን ወይም አንሳተፍም የሚሉ አስተያየቶችን ከመስጠት ተቆጥበው፣ ምርጫው ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን በጋራ እንዲሰሩ ያስፈልጋል:: በምርጫው ወቅት ምርጫ ማድረግ የማይቻልበት ሁኔታ መሆኑ ግንዛቤ ላይ ከተደረሰ፣ ባለፈው የወረዳና የማሟያ ምርጫ እንዳደረጉት

ሁሉ፣ ወቅቱ ሲደርስ በጋራ እራሳቸውን ከምርጫው ማግለል ይችላሉ:: በምርጫው መሳተፍ ጥቅም ካለው ደግሞ በጋራ ወደ ምርጫው ይገባሉ:: ይህንን ውሳኔ በጊዜው እንዲወስኑ ለነርሱ እንተውላቸው::

2. በአገር ቤት የሚኖሩ ተቃዋሚዎች ለምርጫው ከአሁን ጀምሮ፣ ምርጫ እንደሚሳተፉ በመገመት መዘጋጀት፣ የምርጫ ስትራቴጂ ማውጣት፣ ተወዳዳሪዎችን መመደብ፣ ህዝብን ማስተባበር ይኖርባቸዋል::
3. ከገዢው ፓርቲ ጋር የሚደረገው ውድድር መቋረጥ የለበትም:: ምርጫውን በተመለከተ እስከሆነ ድረስ ድርጅቶች በድርድሩ ላይ በጋራ መካፈሉ ችግሩ አይታኝም:: አላወቅንበትም እንጂ ገዢው ፓርቲ ድርድሩን በመኢአድና በመድረክ መካከል መከፋፈልን ለመፍጠር እየተጠቀመበት ነው:: ስለዚህ በሚቀርቡ አጀንዳዎች ሁሉ ላይ መወያየት እስከተቻለ ድረስ፣ ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ መድረኩ ወደ ድርድሩ ገብቶ ከመኢአድ ጋር አብሮ መሥራት ይኖርበታል ባይ ነኝ::
4. በኢ/ር ኃይሉ ሻውል የሚመራው መኢአድ የመድረኩ አባል ድርጅት ሆኖ የሚሰራበት መንገድ መፈለግ ይኖርበታል:: ይህም ካልተቻለ ደግሞ መድረኩና መኢአድ ከገዢው ፓርቲ ጋርም ሆነ ከዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ጋር የሚያደርጉት ውይይት በጋራ በመሰለፍ የጋራ አቋም ማሳየት ይኖርባቸዋል:: በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ የምንኖር ኢትዮጵያውያን በዚህ ረገድ ፓርቲዎቹን ትልቅ ግፊት ማድረግ ይኖርብናል ብዬ አምናለሁ::
5. የአንድነት ፓርቲ፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያምን ጨምሮ በርካታ የድርጅቱ የምክር ቤት አባላትን ከፓርቲው አግዷል:: ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያምና አብረዋቸው ያሉ በአንድነት የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ላይ ቅሬታ ያቀረቡ ወገኖች፣ አልተሳሳቱም ባልልም፣ ከድርጅቱ መታገዳቸው ግን ፓርቲውን ያዳከመና ጠቃሚ ያልሆነ ውሳኔ ነው ባይ ነኝ:: የተወሰደውም ውሳኔ ምን ያህል የድርጅቱን ሕግና ደንብ እንደጠበቀ በግል የሚታወቅ ነገር የለም::

   እነ ፕሮፌሰር መስፍን፣ ያለውን ችግር በውይይት ለመፍታት ፍቃደኝነታቸውን እንደገለጹ አውራምባ ታይምስ ዘግቧል:: በመሆኑም አሁን ያሉት የአንድነት ፓርቲ አመራር አባላት በሌሎች የድርጅቱ አመራር አባላት ላይ የወሰዱትን እርምጃ ቀልብሰው፣ በድርጅቱ ውስጥ ያለውን ችግር በውይይትና በንግግር መፍታት የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርባቸዋል የሚል ጠንካራ እምነት አለኝ::

   የአንድነት ፓርቲ የሰለጠነ ፖለቲካን የሚያራምድ ፓርቲ ነው:: ችግሮችን በንግግር መፍታት ሊያቅተው አይገባም:: የአንድነት ፓርቲ አመራር አባላት አብረዋቸው ፓርቲውን ከመሰረቱና አብረዋቸው ብዙ መስዋእትነትን ከከፈሉ

የአንድነት መሥራች ወገኖች ጋር አብረው መሥራትና ችግሮቻቸውን በንግግር መፍታት ካልቻሉ፣ በመድረኩ ውስጥ ካሉ ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ጋር በዘላቂነት አብረው ይሰራሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡ በጥቂቱ ያልታመነ በብዙ እንዴት ሊሾም ይችላል? (በዚህ አጋጣሚ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ያሉ የአንድነት ደጋፊዎች ጭፍን ድጋፍ ለፓርቲው ከመስጠት ተቆጥበን ፓርቲው ለድርጅቱ የሚጠቅመውን መንገድ እንዲከተል ከፍተኛ ግፊት ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ፓርቲው የድርጅቱ የአመራር አባላት ብቻ አይደለም፡፡)

6. አቶ አስራት ጣሴ እንዳሉት «ምርጫ በማሸነፍ ወ/ት ብርቱካንን እናስፈታለን» የሚለው አባባል ተቀባይነት የሌለው አባባል ነው፡፡ ምርጫ ተደረገም፣ አልተደረገም ይህችን ታላቅና ጀግና ሴት ለማስፈታት፣ ከምርጫው ጋር ያልተገናኘ፣ ሕዝባዊ ንቅናቄዎችን ማጧጧፍ ያስፈልጋል፡፡ የውጭ ዲፕሎማቶችን ከማነጋገር፣ አንድ በአባላት ብቻ የተደረገ ሰልፍ ከማድረግና በጽ/ቤት ውስጥ በየወሩ ከሚደረግ የሻማ ማብራት ሥነ-ሥርዓት ውጭ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ለማስፈታት ይሄ ነው የሚባል እንቅስቃሴ ሲደረግ አላየሁም፡፡ እውነቱን እንነጋገር ህዝቡን እንደሚገባ አላንቀሳቀስነውም፡፡

በዚህ ረገድ የአንድነት ፓርቲ ብቻ ሳይሆን የመድረክ አባል ድርጅቶች ሁሉ እንዲሁም በኢ/ር ኃይሉ ሻውል የሚመራው መኢአድ ትልቅ ትኩረት ሰጥተውበት የተቀናጀ ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች መጀመር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበርና መሪ ብቻ አይደለችም፡፡ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የመኢአድ፣ የአንድነት፣ የአረና፣ የኦሕኮ..... መሪም ናት፡፡ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ ዳግማዊት ጣይቱ ብጡል፣ የሁላችንም መሪ ናት፡፡

7. በውጭ አገር ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችና የፖለቲካ መድረኮች ምርጫውን በተመለከተ በየጊዜው ከሚያወጡት መግለጫ እራሳቸውን እንዲቆጥቡ ያስፈልጋል፡፡ በአገር ቤት ያሉ ወገኖቻችን ናቸው አፈና፣ ችግር፣ እስር እየገጠማቸው፣ እየታገሉ ያሉት፡፡ «ወደምርጫው መግባት ያስፈልጋል፣ አያስፈልግም» ለሚሉት ጥያቄዎች፣ በጊዜው እና በሰዓቱ እነርሱ እራሳቸው የሚወስኑት ይሆናል፡፡ አሁን ማንሳት የማያስፈልገንን ነጥብ እያነሳን አላስፈላጊ ጭቅጭቅና ትርምስ ከመፍጠርና፣ ለገዢው ፓርቲ መጠቀሚያ ከመሆን መቆጠብ ይኖርብናል፡፡ የገዢው ፓርቲ ጥንካሬ የኛ መከፋፈል ነው፡፡

8. በኢትዮጵያ ያሉ ወገኖቻችን፣ አገዛዙ ፍጹም ኢዴሞክራሲያዊና ግትር ከመሆኑ የተነሳ የሕዝቡ ሰቆቃና ስቃይ እየጨመረ ከመጣ፣ የፊታችን ምርጫም እንኳን 97 ወደነበረው አይነት ሊቃረብ ቀርቶ ፍጹም አፈና የበዛበት ከሆነ፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎችም እራሳቸውን ከምርጫው ያገላሉ የሚል ግምት አለኝ፡፡

ተቃዋሚዎቹ እራሳቸውን ከምርጫው ካገለሉ ደግሞ ገዢው ፓርቲ በፎርፌ ብቻውን፣ ወይንም በስም ተቃዋሚ ነን ከሚሉና የአጋርነት ሚና ካላቸው ጋር ተወዳድሮ አሸነፍኩ ማለቱ አይቀርም። የውጭ ኃይላትም አገዛዙ ጥቅማቸውን እስከጠበቀ ድረስ ይቃወሙታል ብዬ እራሴን አላሞኝም። በኢራን እንደታየው ከተቃወሙም ተቃውሟቸው ለትንሽ ጊዜ ብቻ ነው የሚሆነው። ጥቂት ሳምንታት እንዳለፉም ዝም ማለታቸውና ገዢውን ፓርቲ በእርዳታ ማንበሽበሻቸው አይቀርም። የማታ ማታ ባዶአችንን ልንቀር ነው ማለት ነው።

ለዚህም እንዲረዳ በአስቸኳይ የኢትዮጵያን አንድነትና ሉዓላዊነት ለድርድር ያላቀረበ ትብብር መፈጠር ይኖርበታል ባይ ነኝ። ይህ ትብብር «ምርጫው ከተጭበረበረና አገዛዙ የዘረጋውን አፈና ከቀጠለ፣ በኢትዮጵያ ያለ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምንም ማድረግ ካልቻሉ፣ እነ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ካልተፈቱ ምንድን ነው መደረግ ያለበት?... »

እዚህ ላይ ትብብር እንፍጠር ስል «ትብብር እንፍጠር» እያልን ለአመታት እናውራ ማለቴ አይደለም። ውጭ አገር ባሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ዘንድ ስንሰማ የከረምነው የእንተባበርን ጥሪ መስማት ያልሰለቸው ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም። የምንፈልገው ሁላችንንም ያደከመን የ«ትብብር እናድርግ» ወሬ ሳይሆን ትብብሩን ነው።

## ውድ የአገሬ ልጆች:-

አገዛዙ ተከፋፈሉ ሲለን አሜን ብለን መከፋፈል ማቆም አለብን። በዘር መከፋፈል መቆም አለበት። ምርጫ እንግባ አንግባ የሚል መከፋፈል መቆም አለበት። ሰላማዊ ትግል ይጠቅማል አይጠቅም በሚል መከፋፈል መቆም አለበት። በግለሰቦች ተክለ ሰውነት ምክንያት የተፈጠሩ መከፋፈሎች መቆም አለባቸው። ሁላችንም የድርሻችንን እንስራ። ሁላችንም በሌላው ሥራ ጣልቃ አንግባ። ሁላችንም ልዩነቶቻችንን እንደያዝን መስማማት በምንችልበት ጉዳዮች ላይ አብረን እንሰለፍ። ሌላውን ከማጥቃትና ከመቃወም እኛ የሰራነውን ሥራ በተግባርና በተጨባጭ እናሳይ። እኛ የድርሻችንን ሳንወጣ የሚሰሩ ሌሎችን አናጣጥል። ትናንት ያጠፋን ካለንም ዛሬ አስተዋጽኦ ማድረግ ስንችል፣ በትናንት ጥፋታችን እየተደጋገመ አንኮነን። በትንሹም በትልቁም ልዩነት ሲፈጠር ለክስና «ወያኔ ነው» ለማለት አንቸኩል። እርስ በርስ በቅንነት እንቀባበል። የበሰልንና የነገውን የምናይ እንጂ ወደኋላ የምናስብ፣ ትናንት የሰራናቸውን ስህተቶች እየደጋገምን የምንሰራ፣ የማንማር ሰዎች አንሁን!

እግዚአብሄር ሁላችንንም ይርዳን!

# የማይበገረው መልዕክተኛ

**በአበበ ገለው**

በማይበገር መንፈስ የተባረኩ የተወሰኑ ሰዎች አሉ፡፡ ብርቱ ፈተናዎችን በድል መውጣትና የኋልዮሽ የሚጎትቱትን ደግሞ ወደ ለውጥ ማምጣት ይቻላቸዋል፡፡ የእነዚህ አይነቶቹ ሰዎች ሕይወት እንደሰሜን ተራራዎች በወጣ ገባዎች፣ በማግኘትና በማጣት፣ በጠመዝማዛና በእሽክርክሪት፣ በድሎችና ሽንፈቶች . . . የተሞላች መሆኗን በጥልቀት ይገነዘባሉ፡፡ የሀዘን፣ የምሬት፣ የሕመም፣ የወድቀቶች፣ የፈተናዎች ወይም የአስከፊ ስቃይ ወቅቶችን በጸጋ በመቀበል ከሚገጥሟቸው ከማናቸውም ያልተለመዱ ነገሮች ራሳቸውን ነፃ ያወጣሉ፡፡ እርግጥ ነው እውነተኛ ወንዶችና ሴቶች ጀግኖች ጠላቶቻቸውን በበቀልና በጥላቻ ቀስቶች ወግተው የሚገድሉ አይደሉም፤ ይልቁንስ የሕይወትን የጨለማ ወቅቶች በመገዳደር አሸንፈው በማንጸባረቅ የሚወጡ እንጂ፡፡

ቴዲ አፍሮ በሚለው የመድረክ መጠሪያው በይበልጥ የሚታወቀው ቴዎድሮስ ካሳሁን፣ ከወሂኒ ሲወጣ ቅስሙ የተሰበረ፣ ጭንቀት የወረረው እና እድሉንና ኃያሉን እግዚአብሔር የሚያማርር ሰው መሆን ነበረበት፡፡ አስፈሪ አይጦችና ተባዮች በወረራቸው አስቀያሚ ጨለማ ወሂኒ ቤቶች ባሳለፋቸው የፈተናና የስቃይ ወቅቶች ዘፈኖቹን፣ ዜማዎቹን፣ ግጥሞቹንና የፍቅር፣ የአንድነትና የለውጥ መልዕክቶቹን እንደሚዘነጋቸውም እንዲሁ የተገመተ ነበር፡፡ አንዳች ተጨባጭ ነገር ማድረግ የማይቻለሙ «ዞምቢ»ም ሆኖ መለወጡ ተገምቷል፡፡

ግና እውነተኛ ኮከቦች በጭራሽ አያሸልቡም፡፡ ከሕዋ የመጨረሻ ሩቅና ድብን ያለ ጨለማ ጥጎች፣ የጨለማን ገዥነት በድል በማሸነፍ ማንፀባረቃቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ቴዲ አፍሮ፣ የበርካታ ወንዶችና ሴቶች ደፋሮችን መንፈስና እምነት ከሰበሩ ከእነዚያ ጨካኝ ወሂኒ ቤቶች ከወጣ ከጥቂት ቀናት በኋላ ይህን እውነታ አረጋግጧል፡፡

ገጣሚና ጸሐፊ ካሮል ሲን ፒርሰን፣ «ጀግኖች ይጓዛሉ፣ ድራጎኖችን ይጋፈጣሉ፣ በመጨረሻም የእውነተኛ ማንነታቸውን ኃብት ያገኛሉ፡፡» ይላል፡፡ እንደማንኛውም የፍርድ ሂደት መሆን የሚገባውን ገና ማስረጃ ሳይሰበሰብና ክስ ሳይመሰረት ጨካኝ ፍርድና ቅጣት በመወሰኑ የበርካቶች መሳለቂያ ወደሆነ የፌዝ ሰርከስ ትርኢት የፍርድ ሂደቱን የለወጠውን የይስሙላ ፍርድ ቤት ድራጐኖችን፣ እንዲሁ በተመሳሳይ ቴዲ አፍሮ ተጋፍጧቸዋል፡፡ ያ ሁሉ ቢደርስበትም፣ ከወሂኒ የወጣው አንዳች ሳይደርስበትና ቅስሙ ሳይሰበር ነበር፡፡ ይልቁንስ እንደአርቲስትነት የስኬቱ መሰረት ለመሆን የጠበቀውን የእውነተኛ ማንነቱን የበለጠ ጸጋ - በሂሊናችን ኃያል መልዕክቶች የሚያጭር - በማግኘ ት ነበር ከእስር የወጣው፡፡

የቴዲ የቅርብ ነጠላ ዜማው፣ ከእስር ቤት በተለቀቀ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ የተለቀቀው፣ በሚሊዬኖች የሚቆጠሩ አንደበት የሌላቸው ኢትዮጵያውያንን የልብ ምትና ትርታ ለማስተጋባት ተልዕኮ ያነገበ አርቲስት ስለመሆኑ እውነታ ሌላው ምስክርነት ነው፡፡ «ሰው» የተሰኘውን የበጎ አድራጎት ነጠላ ዜማውን በአሰቃቂ ድህነት ስለሚሰቃዩ ብዙ ኢትዮጵያውያን በሚያዜምበት ወቅት፣ የደነደነ የአእምሮአችንን ነርቨና ስሜት

የሚኮረኩር ነው፡፡ መጠለያ፣ ምግብና እርቃናቸውን ለመሸፈን ልብስ የሌላቸውን የተረሱ ሚሊዬኖች ኢትዮጵያውያንን አስመልክቶ ሳይጤን የማይታለፍ ያገጠጠ መልዕክት ወደልባችን አቅርቦ ያደርስልናል፡፡

አብዛኛው ዓለም ታላላቅ እመርታዎችን እያከናውነ ባለበት በ21ኛው ክ/ዘመን፣ የተከፋፈለችና የተሰነጣጠቀች ኢትዮጵያ አሁን ድረስ በየዓመቱ ከሩቅ ምግብ ለመለመንና እርዳታ ለማግኘት እጇን በመዘርጋቷ፣ ከሚገመተው በላይ ማብቂያ በሌለው የድግግሞሽ ጥልቅ ሕመም እንደተያዘች ነው፡፡ በሆነ ወቀት የአፍሪካ «የዳቦ ቅርጫት»ና «የውሃ ማማ» ተብላ የምትጠራው ኩሩ አገር፣ ልመናና ረሃብ መለያ መልክቶቿ ሆነዋል፡፡ የሕወሓት ደብል ዲጂት የተባለው የኢኮኖሚ እድገት ለተራቡ ምግብ መሆን እንኳን አዳግቶታል፡፡ ሆኖም፣ ብሔርን ማዕከል ያደረጉ ኤሊቶችን ግን እያደለበ ነው፡፡ በሕዝብ ስም ከምንገምተው በላይ ሀብት ማከማቸቱን የሚያስወራው «ኤፈርት»፣ በሚገኝበት ትግራይ ክልል እንኳ፣ በሚሊዬኖች በምግብ ዋስትና ሴፈቲ ኔት ላይ ነው የሚተማመኑት፡፡

አማካኙ በሕይወት የመቆያ ዓመታት ከ40 በታች ለሆነባቸው አብላጫ ኢትዮጵያውያን፣ ሞት የእምቦቀቅላነት ዕድሜያቸው መቀጫ ጥሪ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የእናቶች ሞት በከፍተኛነት ከሚጠቀሱት የዓለማችን አገሮች ከቀዳሚዎቹ ጋር የሚያስጠራት ነው፡፡ ከሌላው ዓለም በይበልጥ፣ በኢትዮጲያ የሚወለዱ ሕፃናት በተመጣጠነ የምግብ እጥረት፣ ረሀብና በሽታ አምስተኛ ዓመታቸውን ከመያዛቸው አስቀድሞ የመሞት እድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ሕውሓት ድህነትን በትጋ እየተዋጋ መሆኑን ቢናገርም፣ በዴሞክራሲ፣ እኩልነት፣ ፍትህ እና ተጨባጭ እድገት እና ለውጥ ላይ አንዳች ስራ አልሰራም፡፡

ሕወሓት በዝናብ ውሃ የተመሰረተ እርሻን በጥረት ለመገላገል በጣም ጥቂት ነው የሰራው፡፡ ከዚያ ይልቅ ያልተነኩና በመስኖ ሊለሙ የሚችሉ የእርሻ መሬቶችን በነዳጅ ለበለፀጉ ባላባቶች እየሸጠ ይገኛል፤ ለመካከለኛው ምስራቅ እህል ለማምረት በቅርብ ግዙፍ ዘመናዊ የእርሻ ማሳዎችን በማረስ መሳተፍ የጀመሩት በሼይክ ሞሀመድ አል አሙዲ የተመሩ ኢንቨስተሮች የሚከጠቀሱ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ የተመረተ ምግብ የሳዑዲና ገልፍ አገሮችን ለመመገብ ኤክስፖርት በማድረግ ኢትዮጵያ የአረብ የዳቦ ቅርጫት በምትሆንበት ወቅት፣ በሚሊዬኖች የሚቆጠሩ የረሀብ ድግግሞሽን የማምለጠ ተስፋ የሌላቸው በመሆኑ ኢትዮጵያ ምግብ መለመኗን ትቀጥልበታለች፡፡

ማብቂያ የለሽ ተቃርኖሽ በሞላባት አገር፣ የቴዲ አዲሱ ነጠላ ዜማ የኛዎቹን ያጡ፣ የተረቡና በበሽታ የተጠቁ ሚሊዬኖች ኢትዮጵያውያንን ያስታውሰናል፡፡ እንደአለመታደል፣ ወራጅ ወንዞቿ ጎረቤት አገሮችን በሚመግቡበት ምድር የእነዚህን ኢትዮጵያውያን በመሆናቸው የተሸከሙትን ከባድ ቀንበር ለማስወገድ የተቀረፀ ስትራቴጂ የለም፡፡

ቴዲ ከመለቀቁ ከጥቂት ሳምንታት በፊት፣ ከአዲስ አበባ የ«NPR» ጋዜጠኛ ገዌን ቶምፕኪንስ፣ አንድ ዘገባ አውጥታ ነበር፦ «ቴዲ በሙዚቀኛነት በኢትዮጵያ ውስጥ መቀጠል አለመቀጠሉ በጥያቄ የሚታለፈ ነው:: በቅርብ የወጡ ሕጎች ሀሳብን የመግለጽ ነጻነት ላይ ተጨሪ ገደቦች ይጥላሉ:: እንዲሁም የሰብዓዊ መብቶች ተሟጎች ድርጅቶች መንግስት በተረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ተቺዎቹን ማፈን የሚያስችለው ነው፤» በማለት ይከራከራሉ:: «አንድ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን ይህን አበክረው አጣጥለውታል::

ቴዲ የሕዝቡን ልብ ትርታ ማስተጋባቱን መቀጠል አለበት:: ለቴዲ የአዲስ ዘፈኖች ዝርዝር ቢኖረኝ፣ ከዝርዝሮቼ ቀዳሚው ብቸኛው ወንጀላቸው ለሕዝባቸው ነፃነትና የተሻለውን መመኘታቸው ብቻ ለሆኑ እንደብርቱካን ሚደቅሳ ላሉ የህሊና እስረኞች የሚፈስ የምስጋናና አድናቆት ሙዚቃ ነበር የሚሆነው:: ባልተገባ የታሪክ ስፍራ የተገኙ ፍራቻቸው ጭራሽ የሚቆም አይደለም ምክንያቱም አምባገነንነት በጭራሽ በታሪክ ዘላለማዊ እንዳይደል አጥብቀው ያውቃሉና ነው::

ቴዲ ከተፈታ በኋላ በ«ኢኮኖሚስት»፣ *«Movement of Jah's People»* በሚለ ርዕስ በወጣ ጽሁፍ፣ የሚከተለው ሰፍሯል፦ «አሁን የመንግስት ፍራቻ የቴዲ መፈታት ትኩረትን ወሂኒ ወድወረዳት ሞገስ ወደ ተላበሰች ወጣት የተቃዋሚ መሪ፣ ዳኛና የአንድ ልጅ እናት ብርቱካን ሚዴቅሳ የሚመልስ መሆኑ ነው:: ብርቱካን ይቅርታ አልጠየኩም ብላ ክዳለች ተብሎ በዚህ ዓመት መጀመሪያ ዳግም ከመታሰሯ በፊት፣ 18 ወራት በእስር ቆይታለች:: ደጋፊዎቿ አብዛኛውን የእስር ዓመቱን ያሳለፈችው ለብቻዋ በመታሰር ነው ብለው ይናገራሉ::»

እርግጥ፣ ለሕዝባቸው ሲሉ ነፃነታቸውን ለተነጠቁ ማዜምና መጸለይ ከእኛ የሚጠበቅ ነው:: በጨካኙ የመለስ ዜናዊ አምባገነናዊ መንግስት፣ እወነቱን ለመናገር የሚከፈል ግዙፍ ዋጋ አለ:: መልዕክተኛን ለመግደል መሞከር መልዕክተኛውን የበለጠ ገናና የሚያደርገው ነው:: የቴዲ ፈተናና ስቃዮች በጣም ከፈተኛ ተቃውሞና ቁጣ የፈጠረው አርቲስቱ በፍርድ ቤት በመዳኘት አይደለም፤ እልቅስ እውነታው እንደቴዲ ያሉ አነቃቂ ኢትዮጵያውያንን መንፈሶች ቅስም ለመስበር ግልጽ ውጥን በመኖሩ ነው:: እንደመታደል፣ ቴዲ ለዋጭና አነቃቂ መልዕክቶቹን በስፋትና በርቀት የሚያደርስ በጣም የበለጠ ኃያል ድምጽ ነው:: እንደእውነት አንበርካቢ መልዕክት የለም:: እንዲሁም ለነፃነት ታላቅ ስሜት እንደተጎናፀፈ እውነተኛ አማኝ ያለ ታማኝ መልዕክተኛ የለም:: ቴዲ አፍሮ የማይበገርና የማይናወጥ ኃያል ድምፃነቱን ማስመስከሩ አያጠራጥርም::

በመጨረሻ፣ እያንዳንዱ ሰው ካለፍርሃት፣ « ... በመጨረሻም ነፃነት ሆነ፣ ... በመጨረሻ ነፃነት ... ኃያሉ እግዚአብሔር ይመስገን ... በመጨረሻ ነፃነታችንን አገኘን . . .» እያለ የሚዘምርበት ቀን መምጣቱ የማይቀር ነው:: ለውጭ ኃይሎች ቅኝ ባለመገዛቷና ባለመወረሯ ኩሩ በሆነችው አገር፣ ግና እውነተኛ የነፃነትና የሉዓላዊነት

ትርጉም በጭራሽ አጣጥማ የማታውቀው፣ ወደፊት እነዚያን የባሪ መዝሙሮች በኢትዮጵያ መዘመራቸው የማይቀር ነው::

*/አበበ ገላው፣ የaddis Voice ድረገጽ ኤዲተርና የስታንፎርድ ዩኒቨርስቲ ተመራማሪ ናቸው/*

# የኢትዮጵያ ቡና ግብይትን ስለማሽሞንሞን

**በወንድወሰን መዝለቂያ**

መጭዎቹ ጥቂት ቀናት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ (ECA) ሥራ-አስፈፃሚዎችና መንግስት ለታላቁ ዕለት የሚዘጋጁበት በመሆኑ በስራ የሚወጠሩባቸው ናቸው:: ዕለቱም እጅግ የተፈለገውን እውቅና ለምርት ገበያው ከአሜሪካ የቡና ተቀባዮች ማሕበር (Speciality Coffee Association of America - SCAA) ለማስገኘት እና ለመንግስትም ጠቃሚ የሚዲያ ሽፋን ያስገኛል ብለው በተስፋ የሚጠብቁት ነው:: በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድረ-ገጽ ለአጭር ጊዜ በወጣና ባለፈው ሳምንት መጀመሪያ አካባቢ በተነሳ ዶክመንት መሰረት፣ ይህ በምስጢር የተያዘው ዘለት ከጥቅምት 20 እስከ 24 2009 ድረስ የሚካሄድ ነው:: መንግስት የሚቆጣጠረው ግልጽነትን ለማስተዋወቅ የሚታትረው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ፣ ግልጽ ባልሆነ ምክንያት፣ አንደበቱ ተቆልፏል፤ በመሆኑም፣ ከማሕበሩ ጋር ያካሄዷቸው ድርድሮች፣ የቡና ንግድ ስጋቶችን ለማስወገድ የወሰዳቸው ለውጦች እና ለብልሹ የቡና ሴክተሩ ቁጥጥር አስተዋፅኦውን ይህ ዳሰሳ ቅኝት ያደርግበታል::

በዚህ ዓመት መጀመሪያ፣ የቡና ንግድን በራሱ ቁጥጥር ስር ለማድረግ መንግስት የምርት ገበያውን ሥርዓት በችኮላ በተጠቀመበት ወቅት የምርት ግብይቱ አካሄድ ችግሮች የዓለም ዓቀፍ የመገናኛ ብዙሀንን አትኩሮት ተቆጣጥሮ ነበር:: የመገናኛው ብዙሀን ሳይጠበቅ ምርት ገበያውን ከማሞገስ ወደ መተቸት መለወጡ፣ መንግስት ሁኔታውን ለማለሳለስ ከንቱ መንፈራገጥ አደረገ:: የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት (ኢምገ) ሥራ አስኪያጅ ዶ/ር እሌኒ፣ ከመገናኛ ብዙኃን ጠንካራ ትችት በስተጀርባ ያሉ ገፋፊ ኃይሎችን ሳያጤኑ፣ ትችቱን ለማለዘብ ባደረጉት ሙከራ በ*«ሲያትል ታይምስ»* ቢዝነስ ሪፖርተር ለሆነችው አሊሰን (በእኔ እምነት ፍሬ-አልባ ነው) ምላሽ እስከመስጠት ደርሰው ነበር:: ኢምገ የቡና ንግድ ውስብስብነትንና የዓለም አቀፍ ባለድርሻ አካላት ያላቸውን ኃይል ያጡነው 21ኛው የማሕበሩ ዓመታዊ ኮንፍረንስ በተካሄደበት ነበር::

የኢምጎ ጉዳይ በኮንፍረንሱ የተነሳ አንድ አጀንዳ ነበር፡፡ በሚያዚያ 15/2009 በዶ/ር እሌኒ፣ ፊሊፕ ሽሉተር እና በታደስ መስቀላ የተመራ የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ኢምገንና አዲሱን የቡና ግብይት ሥርዓት አስመልክቶ ለተቀባዮች መረጃ የመስጠት ውይይት ነበረው፡፡ መልዕክተኞቹ የሥርዓቱን አስተዋጽኦ/ተሳትፎ በተመለከተ በኃላ የተከሰተውን ችግር ሲያነሱ ወዲያው የሞቀ ክርክር በተሳታፊዎቹና በአቅራቢዎቹ መካከል ተከሰተ፡፡ በተከታዩ ቀንም በተካሄደ የጠረጴዛ ዙሪያ ስብሰባ፣ የጦፈ ውይይት ተካሄደ፡፡ ከተሳታፊዎቹ አንዱ ሁኔታውን ለዚህ ፀሃፊ እንደሚከተለው አብራርቷል፡- «የዛሬው የጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት የጦፈ ነበር፡፡ እጅግ በጣም ውስብስብ፡፡ ዶ/ር እሌኒ፣ እዚህ የተገኙት ለማድመጥና መረጃ በማሰባሰብ ወደኢትዮጵያ ለማሰባሰብና ሌላ «ሁለተኛ መስኮት» ለማበጀት የተገኙ መሆናናቸውን ገልጸው ለማሕበሩና ለገዥዎች አረጋግጠውላቸዋል፡፡ ግን አሁን ምንም የለም፡፡ ገዥዎችና ገበሬዎች ከፍተኛ መዋዕለ ንዋያቸውን አፍስሰዋል፡፡ ወቅቱ አብቅቶለታል - በጣም ጥቂቶች ቡና ለማግኘት በቅተዋል፡፡ ምናልባት በመጭው ወቅት . . .፡፡ ሁሉም በጥምረት መስራት ይፈልጋል፡፡»

በውይይቱ መጨረሻ ዶ/ር እሌኒ ከማሕበሩና ከገዥዎች በዝግጅቱ ያገኙትን ተሞክሮ በመጭመቅ ግልጽ ደብዳበ ጽፈውላቸዋል፡፡ እና ችግሮችን ለመቅረፍ በማሕበሩና በኢምገ የሚመሰረት የጋራ አጥኚ ቡድን እንዲቋቋም ሀሳባቸውን አቅርበዋል፡፡ በገበያ ውስጥ ተቀባይነት ያለው ማሕበር አስቀድሞ ለጠ/ሚ መለስ ዜናዊ ስጋቱን የገለፀበትንና አስቸኳይ መፍትሄ የጠየቀበትን ደብዳቤ ልኮ ነበር፡፡

የጥናት ቡድኑ ተቋቁሞ ላለፉት ስድስት ወራት በጥብቅ ምስጢር ተይዞ ስራውን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ እንደውም ኢምገ ውይይቱ በዚህ ወር መጨረሻ እንደሚጠናቀቅ ፍንጭ ሰጥቷል፡፡ ጊዜውም ሲደርስ የኢምገ የግብይት አካሄዱን የተወሰኑ ለወጦች ይፋ ያደርጋልም ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ሆኖም ዝርዝሩ እስካአሁን ድረስ ለህዝብ ይፋ ሳይደረግ ተይዟል፡፡ ከኢምገ የተገኘው ብቸኛው ቃል ዶ/ር እሌኒ ባለፈው ወር በኢቴቪ በተፈራ ገዳሙ «Meet ETV» ፕሮግራም ላይ ቀርበው በጨረፍታ የነኩት ነው፡፡ ማሕበሩና ኢምገ ስምምነት ላይ መድረሳቸውንና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት በቡና ጥራት ምደባ ሥርዓቱን ለማሻሻል የወሰዳቸውን ለውጦች በጥቅምት መጨረሻ እንደሚያሳውቁ ጠቅሰዋል፡፡

ማሕበሩ ከኢምገ በበለጠ ግልጽና መረጃዎችን ለማግኘት የሚቻልበት ድርጅት ነው፡፡ የማሕበሩ ኤግዚኩቲቭ ዳይሬክተር ሪክ ሬህንሀርት ለዚህ ፀሀፊ በተሰጠ የኢ-ሜይል ምላሽ፣ «ከዚህ ዓመት ሚያዚያ ወር አንስቶ ከኢምገ ጋር የገበያውን ጥራት በሚመለከት እና የምርት ግብይቱ ሥርዓት እንዴት የብና አቅርቦት በማግኘታችን ላይ ተፅዕኖ አሳደረ የሚሉትን በተመለከተ በጥልቀት እየተወያየንበት እንገኛለን፡፡» ብለዋል፡፡ ዳይሬክተሩ ከሌሎች የማሕበሩ አባላት ጋር በዝግጅቱ ለመሳተፍ ወደ ኢትዮጵያ ይጓዛሉ፡፡ አሁን ግን በጉዳዩ ዙሪያ ዝርዝር መስጠት እንደማይችሉ፣ ነገር ግን፣

«ከሁሉም የንግዱ ተሳታፊዎች ማለት ይቻላል ድጋፍ እንደተደረገልንና ስኬቱ ምን ሊመስል እንደሚችል ጥሩ ግንዛቤ አለን የሚል ስሜት እንዳለን መናገር እንችላለን።» ብለዋል።

ከሁሉም በላይ ማሕበሩ የፈለገውን ሊያገኝ ይላል። ከኢምገ ጋር አመርቂ የስራ ግንኙነት በማሳለፋችን በጣም ተደስቻለሁ። እንዲሁም በአቅርቦት ሰንሰለት አማካኝነት ደረጃውን በማስጠበቅ የቡና ሴክተሩን መፍትሄ ለማበጀት በስራችን እንቀጥላለን» ብለዋል። ነገር ግን ከሁሉም በላይ አስፈላጊው፣ ለኢትዮጵያ ገበሬዎች በአቅርቦት ሰንሰለቱ አማካኝነት ከፍተኛውን እና በጣም ዘላቂ የዋጋ ምላሽ መስጠት ነው። ተወሰዱ የተባሉት ለውጦች ማሕበሩንና አባላቱን ማርካት አለማርካቱ፣ በገበሬዎች ላይ ያለውን ቀንበር ማቅለል አለማቅለሉን ጨምሮ በቅርቡ የሚታወቅ ነው። ያም ሆነ ይህ፣ ኢምገ የማሕበሩን ስጋቶች መፍትሄ ለመስጠት ያሳየው ምልክት ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ አንድ እርምጃ መራመዱን የሚያመላክት ነው።

ለጊዜው ሌላ የመገናኛ ብዙሀን የተቃውሞ ማዕበል ከኢምገና መንግስት ለመቀበል እየተዘጋጀን፣ የአለመግባባቱ መሰረታዊ መንኤ ምን መሆኑን ማወቅና ስኬቱን ከኢትዮጵያ አነፃር ያለውን ገፅታ መመልከት አስፈላጊ ነው። ዋጋን ለገበሬው በአቅርቦት ሰንሰለት አማካኝነት ማድረስ ማለት፣ የእያንዳንዳቸውን ገበሬዎች መብት መንፈግ ማለት ከሆነ ተቀባይነት የለውም። አዲሱ ሥርዓት የስሴቱን አንደኛውን ወገን ብቻ የሚመለከት ከሆነ (በሻጮችና ገዥዎች መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት ሳይፈቅድ) እንደዛ ያለው ለውጥ እየተሰራ ያለበትን የግብይት ሥርዓት ከማለባበስ የሚዘል አይደለም። በዋጋ ሰንሰለቱ ሁሉንም ተሳታፊዎች ገበያው የማያስተናግድ ከሆነ (የግል ቢዝነሶችንና ጥቅሙ ለመንግስትና በመንግስት ተዘዋዋሪ ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ጨምሮ) የኬስተሩ ዘላቂነት አደጋ ይጋረጥበታል። ይህ እይታ በቡናው ሴክተር በሚሳተፉ ብዙዎች ተቀባይነት ያለው ነው።

የኢትዮጵያ ቡና ላኪዎች ማሕበር ምክትል ፕሬዚዳንት እመቤት ታፈሰ ኪዳነማርያም ለሪፖርተር ጋዜጣ በቅርቡ እንደተናገሩት ሴክተሩ «አሁን ባለበት ደረጃ አገሪቱን እየጠቀማት አይደለም» ካሉ በኋላ ከግል ሴክተሩ ባለስልጣናት ጋር በጋራ እንዲሰሩ ጥሪ አቅርበዋል።

በተመሳሳይ፣ የቡና ገበሬዎች ሸክሙን መቋቋም እንዳዳገታቸው ይናገራሉ። ባለፈው ወር በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስትር የቡናና ሻይ ልማት ቡድን መሪ የሆኑት አቶ አለማየሁ ተሾመ፣ «የትራንስፖርት አቅርቦት ባለባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ገበሬዎች ቡናን በመተው አገሪቱ የምትጠብቀውን ጠቅላላ የቡና ምርት በመቀነስ አስተዋጽኦ ባለው የጫት ምርት ያሰማራሉ።» ማለታቸውን አዲስ ፎርቹን ጠቅሶ ነበር። በተጨማሪ አብዱልቃድር የተባሉ የቀድሞ የቡና ገበሬ፣ «ከዚህ ቀደም ቡና አለማ ነበር፤ ሆኖም ዋጋው ሲወርድ፣ የቡና ተክሉን በማስወገድ በጫት ተክል ተካሁት።» በማለት

በጋዜጣው በወጣ ተመሳሳይ ጽሁፍ ተናግረዋል። ፎርቹን እንደዛፈው፣ «አብዱልቃድር ከጫት ምርት ያገኘው ከፍተኛ ገንዘብ ብቻ አይደለም፣ በሐረሪ ክልላዊ መንግስት ሁለት ጊዜ ምርጥ ገበሬ ተብሎም ተሸልሟል። ጥራቱን የጠበቀ የጫት ምርት ወደ ውጭ በመላክ ከአንድ ኪ.ግ ጫት ምርት (ተጠቃሚዎች ለአንድ ኪሎ እስከ አንድ ሺህ ብር የሚከፍሉበት) ከ300 እስከ 500 ብር ያገኛል። ቡና ያበቅል በነበረበት ወቅት ወደ ውጭ የሚላክ ምርጥ ቡና በኪሎ ከ20 እስከ 30 ብር ብቻ ያስገኝ ነበር።» በማለት ያስታውሳል።

ሆኖም ግን የመንግስት ስራ ሁሉንም ንግድ ብእጁ ማስገባት ብቻ ነው። መንግስት የሚያስተዳድረው የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት በተያዘው ዓመት 10 ሺህ ቶን የቡና አቅርቦት ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ማቀዱን የኢምገ ዳሬክተሮች ቦርድ አባልና ጄኔራል ማናጀር የሆኑት ብርሀኔ ኃይሌ ተናግረዋል። ጉና ኃ.የተ. የግል ማሕበር 10 ሺህ ቶን ቡና እና 30ሺህ ቶን ሰሊጥ በዚህ ዓመት ለውጭ ገበያ የማቅረብ እቅዱን አስቀድሞ ነበር ያስታወቀው። ገና «የቡና ንግድን ለአምስት ዓመታት ካቆመ በኋላ ነው የኤክስፖርተሮች ቡድንን ለመጀመርያ ጊዜ የተቀላቀለው።»

ኢትዮጵያ በአማካይ 330 ሺህ ቶን ቡና በየዓመቱ ታመርታለች። ከዚህ መጠን ውስጥ ግማሽ ያህሉ ወደ ውጭ የሚላክ ሲሆን የተቀረው ለአገር ውስጥ ተጠቃሚዎች ይውላል። በባለፈው ዓመት ባጀት ዓመት (ሐምሌ 2008፣ ሰኔ 2009) አገሪቱ 134 ሺህ ቶን ቡና ወደውጭ ልካለች። ይህም ባለፈው ዓመት ወደውጭ ከተላከው 170 888 ቶን ጋር ሲነፃፀር በጣም ዝቅተኛ ነው።

መንግስት ወደውጭ የሚላከውን የቡና ምርት መጠን ለማሳደግ የሚፈልግ ቢሆንም ፍላጎቱን ለመተግበር ግን የሚከተለወ አካሄዱ የገበያውን ሰንሰለት በመቆጣጠር የቡና ነጋዴዎች የቡና ክምችቶቻቸውን ለኢምገ እንዲያቀርቡ ኃይል በመጠቀም ነው። ቡና አብቃዮችና ነጋዴዎች የተሻለ ዋጋ ለማግኘት መንግስት ከሚቆጣጠራቸው አካሄዶች ውጭ በመገበያየት የተሸለ ዋጋ ለማግኘት የሚያካሂዱት ማንኛውም ሙከራ ሕገ-ወጥ ነው። በጂማ ዞን «ሕገ-ወጥ የቡና ግብይትንና የቡና ምርት ውድመትን» ለመቆጣጠር የ37 የቡና መገበያያ ማዕከላት ግንባታ መከናወኑን ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል በቅርቡ ዘግቦ ነበር። የጂማ ዞን የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊ፣ «ከማዕከሎቹ ውጭ ቡና ሲገበያዩ የተገኙ ግለሰቦች የ20 ዓመት እስር፣ እስከ 50 ሺህ ብር ሚደርስ የገንዘብ ቅጣት» እንደሚጠብቃቸው ዋልታ የኢንፎርሜሽን ማዕከል ጽሆአል። መንግስት የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ከአምስት ሳንቲም ያነሰ ሳወጣ የውጭ ምንዛሬ ለመፍጠር ይሻል። ይህ አካሄድ በአንድ በኩል ዝቅተኛ ጥራት፣ ምርታማነትንና ምርት በተደጋጋሚ እንዲከሰት እያደረገ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ትርፍ የሌለው የዋጋ ልዩነትና የውጭ ምንዛሬ እጥረት የሚያስከትል ነው።

የኢትዮጵያ የቡና ዘርፍ ችግሮች መሰረታዊ መነሻዎች ውስብስብ ናቸው። ሆኖም በዋናነት የሚጠቀሱት፡- ጥራት ላለው ምርት የማበረታቻ እጥረት መኖሩ፣ ለካፒታልና የቡና ማጠቢያ መሳሪዎችፋንና የማጓጓዣ መንገዶችን ጨምሮ የሌሎች መሰረተ-ልማቶች አቅርቦት  አለመኖር እና የተቋማት ብቃት ማነስ የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህ ከባባድ ችግሮች ለይስሙላ የላይ ላይ ለውጦችን በገበያው መድረክ በማስተዋወቅ የሚቀረፉ አይደሉም።

የአገሪቱ አጠቃላይ ዓመታዊ ምርት ከመንግስትና ከቡና ጠጪዎች ፍላጎቶች ጋር የተጣጣመ አይደለም። በአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም ምክንያት የአገር ውስጥ የቡና መሸጫ ዋጋ ወደውጭ ከሚላከው በጣም የበለጠ ነው።  መንግስት በግዴታ ቡና ወደውጭ እንዲላክ በሚያዝበት ወቅት በአገር ውስጥና በውጭ ገበያዎች መካከል ለሚመጣው የዋጋ ልዩነት ገበሬዎችንና ላኪዎችን ትርፋማ ለማድረግ የመካስ ሀሳብን በጭራሽ አያጤነውም።

በአጭርና በመካከለኛ እቅዱ፣ የመንግስት ፖሊሲዎችና የለጋሾች ፈንዶች በምርምር ላይ ውጭ በማድረግ ምርታማነትን በመጨመርና ገበሬዎችና ነጋዴዎች በበጣም አነስተኛ ዓለም አቀፍ ዋጋ ቡና ወደውጭ በመላካቸው ክሳቸው ጥራት ያለው ምርትን በማቀላጠፍ ላይ ቢውሉ አመርቂ ይሆናል። የቡና ንግድን መንግስት መቆጣጠሩን መቀጠሉ ሴክተሩን የባሰ የሚጎዳው ነው። ኢምገ በመርህ ላይ የተመሰረተ የግብይት ሥርዓትንና የምግብ እጥረትን በማስወገድ ግቡ በመቀጠል፣ የቡና ብዝበዛን ሕጋዊነት ያላበሱ ሩቅ መመልከት የማይችሉ የመንግስት ፖሊሲዎችን ከማስቀጠል የአገር ውስጥ እህል ንግድ ዋጋን በማጠናከር ላይ ቢያተኩር የሚሻለው ነው።

# ጥቂቶች የሚያባክኑት፤ ብዙዎች በእጦት ህይወታቸው የሚያልፍለት

**በታደሰ አዴላ**

የዛሬ አስራ አምስት ዓመት ጓደኛዬ ወደ ሳውዲ አረቢያ ይሄዳል። ከጉዞው መልስ ስለአገሪቱ አጠቃላይ ሁኔታ ብዙ አጫወተኝ። በወቅቱ ጓደኛዬ ከተመለከተው ሁሉ ለአንድ ነገር ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ነበር። ይህም በአገሪቱ የተመለከተው የታሸገ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ዋጋ ነው።

ጓደኛዬ እንዳጫወተኝ አንድ ሊትር ነዳጅ በሳንቲም ደረጃ ይሸጣል። በአንፃሩ ግማሽ ሊትር የታሸገ የመጠጥ ውሃ ዋጋ ደግሞ አንድ የሳውዲ አረቢያ ብር (ሪያል)

ነበር:: ከዓመታት በኋላ የታሸገ ውሃ በፋብሪካ ደረጃ ተዘጋጅቶ ለሽያጭ ቀርቦ ተመለከትኩ:: ምርቱን ሳይ ትዝ ያለኝ የጓደኛዬ አግራሞት ነበር::

ዛሬ የታሸገ ውሃ አቅርቦት ዘርፍ በሀገራችን አድጓል ማለት ይቻላል:: ቁጥራቸው የበዛ የምርት አይነቶች በገበያ ላይ ይገኛሉ:: ከአዲስ አበባ ውጭ በተለያዩ ክልሎች የአገልግሎቱ መገኘት የአገልግሎት ዘርፉ ማደግ አመላካች ነው::

የዘርፉ እድገትም በየዓመቱ የሰባት በመቶ እድገት ማስመዝገቡን መረጃዎች ይጠቁማሉ:: በህንድ ብቻ በታሸገ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ላይ የተሰማሩ 100 (አንድ መቶ) ኩባንያዎች ሲኖሩ፣ በዓመት ወደ 70 (ሰባ) ሚሊዮን ዶላር ያተርፋሉ:: በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ በኤሺያ በሚገኙ ታላላቅ ሆቴሎች ውስጥ ለግማሽ ሊትር የታሸገ የመጠጥ ውሃ ሃምሳ ብር (አራት ዶላር) ማውጣት የተለመደ ነው::

በአንፃሩ በዓለማችን ከስድስት ሰዎች መካከል አንዱ (1.2 ቢሊዮን ህዝብ) ንፁህ የመጠጥ ውሃ አያገኝም:: በተለይ በታዳጊ አገራት ንጽህናው ያልተጠበቀ የመጠጥ ውሃ ብዙዎችን ለጤና ችግር፣ ብሎም ለሞት ይዳርጋል::

በንጽህናው ባልተጠበቀ የመጠጥ ውሃ ሳቢያ በሚፈጠረው የተቅማጥ በሽታ በየዓመቱ ሁለት ሚሊዮን የሚሆኑ (1.8 ሚሊዮን ህፃናት ህይወታቸውን ያጣሉ::)እጅግ የምንወዳቸው፣ የምንሳሳላቸውና የነገ ተስፋዎቻችን የሆኑት እድሜአቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ አምስት ሺህ ህፃናቶቻችን (4900) በየቀኑ በሞት እንነጠቃለን::

ንጽህናው ያልተጠበቀ ውሃ በታዳጊ አገራት ውስጥ ሁለተኛ የሞት ምክንያት መሆኑን ዘገባዎች ያመለክታሉ:: እንደተጠቀሰው ንፁህ የመጠጥ ውሃ ጥቂቶች ከፍተኛ ገንዘብ የሚያወጡለት፣ ውስኖች ከሚታሰበው በላይ ትርፍ የሚያጋብሱበት፤ ብዙዎች በእጦት ህይወታቸን የሚያጡበት ነው:: ይህ ለብዙዎች ታላቅ፣ የማይፈታና ውስብስብ እንቆቅልሽ ነው ለማለት ያስደፍራል::

እንቀቆቅልሹን ይበልጥ ውስብስብ የሚያደርገው ደግሞ በየዕለቱ በመላው ዓለም መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ውሃ በቧንቧ እየቀረበ ባለበት ሁኔታ ነው:: የዘርፉ ጠበብቶች ግን ትልቁ ጉዳይ ከአቅርቦት መጠኑ ይልቅ የአቅርቦት ጥራት ነው ይላሉ::

እንደዘርፍ ጠበብቶች ውሃ በቀላሉ ለብክለትና ለጉዳት የሚዳርግ ንጥረ ነገር ሲሆን በሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች በቀላለል እንደሚበከል ባለሙያዎች ያስረዳሉ:: እነዚህም:-

1ኛ በማጓጓዝ

2ኛ ከአቀማመጥ (ከማከማቸት)

3ኛ ከአጠቃቀም ናቸው::

ከፍተኛ ገንዘብ አውጥተው የታሸገ የመጠጥ ውሃ ከሚገለገሉ ሰዎች አብዛኞቹ የቧንቧ ውሃን ጥራት አያምኑም::ተመራማሪዎች ደግሞ በታዳጊ አገራት ታላላቅ ከተሞች

ሳይቀር የሚቀርበው የቧንቧ ውሃ ጥራት አጠራጣሪ እንደሆነ ያስረዳሉ:: የችግሩ ምንጭም ከውሃ በቀላሉ የመበከል ባህሪይ ጋር የተያያዘ ነው:: ከላይ እንደተጠቀሰው በታዳጊ አገራት የሚቀርበው የቧንቧ ውሃ ከአቅርቦት እስከ ፍጆታ ባለው ሂደት የመበከለ እድሉ ከፍተኛ ነው::

የማጣራት ሂደቱ አያያዝ (Filtration management)፣ የማስተላለፊያ ቧንቧዎች የብቃትና የጥራት ይዞታ (Piping system)፣ ውሃውን በማጓጓዝ ሂደት የሚፈጠር መበከል (Contamination through Transportation)፣ ወዘተ በአብይነት የሚጠቀሱ ናቸው:: ውሃ ለጤናችን መጠበቅ፣ ለጤናማነትና ለጤናማ ህይወታችን መተኪያ የሌለው፣ ከመሰረታዊያኖች አንዱ ነው::

ከውሃ ጋር የተያያዙ ተጨባጭ እውነታዎች እነዚህ ከሆኑ፣ ንፁህ የመጠጥ ውሃ ለማግኘት ከፍተኛ ገንዘብ ማውጣት አቅማችን ካልፈቀደልን ምን አማራጭ አለን?የዘርፉ ባለሙያዎች የምንጠጣውን ውሃ ጤናማነት ለመጠበቅ ቢያንስ ከአምስት የማያንሱ አማራጮች እንዳሉን ያበስራሉ::

ውሃን አፍልቶ፣ አጣርቶ መጠቀም በአማራጭነት ከሚጠቀሙት ውስጥ አንዱ ነው:: ውሃን ማከም ወይንም ውሃን አክሞ ለአገልግሎት ማዋል ሌላው በባለሙያዎች ከሚመከሩት አማራጫች ውስጥ ይጠቀሳል::

ውሃን አክሞ መጠቀም ውጤታማነቱ በሳይንስ የተረጋገጠ ሲሆን ውሃን ሊበክሉ የሚችሉ ንጥረ ህዋሶችን /ባክቴሪያዎችን ያስወግዳል:: ከውጪም አኳያ እጅግ ርካሹ ውሃን የማጣሪያ ዘዴ ነው የተመሰከረላቸው የውሃ ማከሚያዎችን በመጠቀም በማንኛ ውም ሁኔታ ሆነን የምንጠጣው ውሃ ጤናማነቱን ማረጋገጥ እንችላለን::

## ማህበረሰብና ባህል

# የመጽሐፍ ዳሰሳ

ርዕስ:- *«The Ethiopian Revolution - War In the Horn of Africa»*
ደራሲ:- ***ገብሩ ታረቀ (ፕሮፌሰር)***
ይዘት:- ***ታሪካዊ***
ዳሰሳ:- ***በሰለሞን ገ/ስላሴ***
ገጽ ብዛት:- **437**
*ታተመ*:- **ያሌ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣ ጥቅምት 5/2009**

---

**የዳሰሳ ትርጉም-** **አውራምባ ታይምስ**

ደራሲ ገብሩ ታረቀ በ«*Hobart and Swith Colleges*» ለ31 ዓመታት በመምህርነት ያገለገሉ ጡረተኛ የታሪክ ፕሮፌሰር ናቸው:: ገብሩ ለመጽሐፋቸው በመጀመሪያ የሰጡት ርዕስ «*Comrades Against Comrades - The Ethiopians in Revolution and War*» የሚል ነበር:: ምናልባት አስቀድመው ከጥቂት ዓመታት በፊት በተመሳሳይ ጭብጥ ላይ «*The Red Terror in Ethiopia - A Historical Aberration*» በሚል ርዕስ አንድ ጽሑፍ ስለጻፉ ሊሆን ይችላል ለዚሁ በሳል አዲስ ስራቸው በመጨረሻ በሰጡት ርዕስ ፀንተዋል:: ቢሆንም ሁለተኛውን ርዕሱ ከነአካቴው ሳይተዉት ለዚህ አዲስ መጽሐፋቸው ክፍል ሁለት ርዕስነት ተጠቅመውታል:: ፕ/ር ገብሩ በይበልጥ የሚታወቅላቸው ስራቸው ምናልባት «*Ethiopia: Power and Protest: Peasant Revolt in the 20th Century*» ***(1996)*** በሚል ርዕስ ያሳተሙት መጽሐፋቸው ነው::

ገብሩ መጽሀፉን ለወላጆቻቸውና እንዲሁም «ለነፃ፣ ዴሞክራሲያዊትና ሃይማኖትና ፖለቲካ ለተፋቱበት ኢትዮጵያ ለተሰዉ በጠቅላላ» በማስታወሻነት እንድትውልላቸው በትህትና አበርክተዋል:: ይህንም ማድረጋቸው ያስመሰግናቸዋል::

የተወሰኑ ግንዛቤ የጎደላቸው ሰዎች መላ የትግራይን ሕዝብ በጅምላ በመወንጀል አፍራሽ ኩሸት በሚያካሂዱበት የፖለቲካ ዘመን፣ በሕወሓት ዘመን እንኳ ለዴሞክራሲ፣ ኢትዮጵያዊነትና የሕግ የበላይነት በጽኑ የቆሙ የተወሰኑ የትግራይ ተወላጆችን በምሳሌነት በማንሳት አለማወቃቸውን ማሳወቅ ወይም የሚያራምዱት ሀሳብ ሀሰተኛ መሆኑን ማሳየት አሌ የሚባል አይደለም:: ፕሮፌሰር ገብሩ እንዲያ ያሉ ኢትዮጵያዊ ናቸው::

ገብሩ በዚህ መጽሀፍ ላይ ከአስር ዓመታት በላይ ያዋሉ ይመስላል:: በ1994 ወደ ኢትዮጵያ በመሄድ ከሁሉም የሕብረተሰብ አባላት የተውጣጡ ከ500 የሚበልጡ ሰዎችን ቃለ-መጠይቅ አድርገዋል፤ ሆኖም ራሳቸው በአዘኔታ  እንደጠቀሱት፣ ከኤርትራ ወገን ለማግኘት የፈለጉትን ትብብር ማግኘት አልተቻላቸውም:: በተጨማሪ፣ በተደጋጋሚና በበርካታ ስፍራዎች በመጽሀፉ የጠቀሷቸውን መረጃዎች ለማግኘት የሐገር መከላከያ ሚኒስቴር ትብብር ለማግኘት ችለዋል::

ገብሩ ከመነሻው፣ ባልተለመደ ጥፋተኝነትን የማመን ግልጽነት፣ የወሳኝ ክስተቶችን ግንዛቤ በተመለከተ፣ በገለልተኝነት ለመመልከት እንዳልተቻላቸው በታማኝነት ጥፋታቸውን ያምናሉ:: ነገር ግን፣ አድሎዓዊነቱን እስከተቻላቸው ለማውረድ የተለየ ጥረት ማድረጋቸውን ያረጋግጡልናል:: እና እንደሚመስለኝ በሆነ ወቅት ኢሕአፓ የነበሩ መሆናቸውን በጨረፍታ ቢጠቅሱም፣ ከሚጠበቀው በላይ ተሳክቶላቸዋል (ገጽ 79):: በሆነ ወቅት ኢሕአፓ የነበረ በጠቅላላ አሁን ለድርጅቱ የአዘኔታና የደግነት ቃላት ያወጣል ማለት ግን አይደለም::

በሕወሓትና በትግራይ ሕዝብ መካከል የነበረውን ግንኙነት ቅኝታቸው፣ የሚከተለውን ያሰፍራሉ፡- «... ነገር ግን [ሕወሓት] በጠቅላላ ያደረጋቸው በፈቃደኝነት ወይም በራሳቸው ነፃ ምርጫ የተደረጉ አይደሉም፡፡ በርካታ ተገቢ ያልሆኑና እና የማስገደድ ስራዎች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ በከፊል በማበረታቻዎች እና በከፊል በማስፈራራት፣ ግንባሩ ሺህዎችን አደራጅቷል፡፡» (ገጽ108)፡፡ ይህ ሚዛናዊ እይታ የመጽሐፉ ተቺዎች ከነበሩት ጄኔራል ጻድቃን ገብረተንሳይ (የቀድሞው ኢታማዦር ሹም) ቁጣ ካስከተሉባቸው ምልከታዎች የሚካተት ነው፡፡ በተመሳሳይ እይታ (ገጽ 76)፣ ደራሲው እንዲህ ይላሉ፣ «የግዛቱን ድህነት 'በተከታታይ የሸዋ ገዥዎች' ላይ ባላከከ የትግራይ 'ዘመናዊ' ልሂቅ፣ ሌላ ስህተት ተፈጽሟል፡፡ ለመሰል የማታለል ማመሳከሪያነት ምርጡ መፍትሄ ታሪክ ነው፡፡ ስለሆነም፣ እንጀምር፡፡» ከዚያም፣ በቀስታ የታሪክን ጥራዝ ወደማስተካከል ይዘልቃሉ፡፡

የኮሎኔል መንግስቱ ደም የጠማቸው ቀኝ እጆች መካከል፣ ከሞት በኋላ በደርግ ውስጥ ሰርጎ በመግባት ለሕወሓት ይሰልል እንደነበረ የታወቀውና ከመላኩ ተፈራ ጋር በመሆን በሺህዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን በማፅከላዊና ሰሜን ጎንደር የጨፈጨፈው ምሕረት የለሹ ኮርፖራል ገብረሕይወት ገብረእግዚአብሔር ገብሩ በመጽሐፉ ተገልጸዋል (ገጽ 77)፡፡ ደራሲው በተጨማሪ ወሳኝ የደርግ አባላት ከሆኑት መካከል አንዱ በሆኑት ሜጀር ፍሰሀ ደስታ ላይ ያፌዛሉ፤ በሆነ ወቅት፣ ሜጀር ፍሰሀ ወንዶች ከሴቶች የበላይ እንደሆኑ የሚገልጽ አስተያየታቸውን ይናገራሉ፡፡ የዚህን ጊዜ ገብሩ እንዲህ በማለት ያሾፋሉ፡- « ... ከ16 ዓመታት ኮሚኒስታዊ የሰበካ ልፍለፋ በኋላ!»

የደርግን የሰፈራ ፕሮግራም ሲዳስስ፣ የገብሩ ለውጥ አቀንቃኝ የሞራል ምሉዕነት ከነሙሉ ኃይሉ ይገለጣል፡፡ በደርግ ላይ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሲባል ብቻ ፕሮግራሙ መብጠልጠሉ የተለመደ ቢሆንም፣ ገብሩ የሰፈራ ፕሮግራሙን ሚዛናዊነትን ተላብሰው የሶሾ-ኢኮኖሚ አስፈላጊነት እንዳመጣውና እንደ እነ ሻለቃ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ ያሉ («ቀይ ሽብር» በሚል መጽሐፋቸው ይበልጥ የሚታወቁ) እና የደርግ ዓላማ ትግራይን ሕዝብ-አልባ ማድረግ ነው በማለት አበክረው የተከራከሩ የአማጺዎቹን ዓይነቶች ድጋፍ የሌላቸው ትችቶችን ቦታ አይሰጧቸውም፡፡ በአሁኑ ወቅት በጣም አሳሳቢ የሆነውን የብዝሀ-ሕይወትና የአየር ንብረት መራቆት እና የገጠሩን ድህነት ለመዋጋት ሕዝብን ወደሌላ አካባቢዎች ማስፈር እንደአንድ መፍትሄ ሕወሓት የመቀበሉን እውነታ ደራሲው በመጥስ፣ ለዚህ ጭብጥ ማጠናከሪያነት ይጠቀሙበታል፤ ሆኖም፣ «በብሔር መንግስታት» ዘመን ይህ እንዴት ሊተገበር እንደሚችል አግራሞታቸውን ይገልፃሉ (ገጽ 380)፡፡ የ1985 ረሀብና ሕወሓት በተከታይ የወሰደውን እርምጃ አስመልክቶ፣ «ሕወሓት ዓለም አቀፉን ማሕበረሰብ ለማሳመን፣ በቁጥጥሩ ስር የነበሩ በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ወደ ሱዳን እንዲሰደዱ እስከማስገደድ ድረስ ሄዷል፡፡» በማለት ተመሳሰይ ክስተትን ያስታውሳሉ፡፡ «ከዘር-አጥፊ አገዛዝ» መንጋጋ

ሕዝቡን ለማዳን ሲል መውጫቸውን ያመቻቸ መሆኑን በመከራከር፣ ብዙዎቹን የተጎሳቆሉ ገበሬዎች በዓለም አቀፍ ሚዲያ ፊት ደረደራቸው:: ይህ አገዛዙን የማዋረድ እቅዱን አሳክቶለት ሊሆን ይችላል:: ግን ያን ለዓለም ሚዲያ ይፋ ማድረጉ የማያስደስት ማጋለጥ ነበር (ገጽ 308) ::

በአስር ሺህዎች በሚቆጠሩ በአግባቡ ትምህርት ባልቀሰሙና በባልታነጹ ወጣት ኢትዮጵያውያን የተሰማቸውን ሀዘን ይገልፃሉ:: በከፊል ብሔራዊ ቀውሱ የሚመነጨው ሁሉም የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች መሪዎች የፖለቲካ ሹመኞች በመሆናቸው ነው ይላሉ (ይህን የሚጠቅሱት አንድሪያስ እሸቴን ሳይጠቅሱ ነው:: ምናልባት በጣም ግልጽ በመሆኑ በስም እርሳቸውን መጥቀስ አስፈላጊነቱ አልታያቸው ይሆናል)::

በዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ጥቂቱ ውይይት ብቻ ስለተደረገበት፣ ማለትም በሕወሓት በጦርነት ተሸንፈው ስለተበተኑ ኢትዮጵያውያን ወታደሮች አሳዛኝ እጣ፣ ትኩረት ይሰጣል:: በቃለ-መጠይቆቹ፣ አገራቸውን በጀግንነት ያላገለገሉ ይመስል እንዲሁ ካለድጋፍ ሜዳ ላይ የተበተኑትን የእነዚህን ጀግኖች ፍጹም ድህነትና ጥልቅ ንዴት አንባቢ ለመመልከት ይቻለዋል:: 20 ዓመቱን ከያዘ ጫማ ጠራጊ የቀድሞ ወታደር ጋር የተገናኙበትን አጋጣሚ ገብሩ ሲተርኩት፣ ያ እይታ ፍንትው ብሎ የሚታይ ነው:: ሕወሓት ሥልጣን ከያዘ በኃላ አገሪቱ ስለተቀዳጀችው ሰላም ስሜቱን እንዲገልጽ በፕ/ር ገብሩ ሲጠየቅ ወጣቱ መለሰ:- « ጌታዬ፤ ካለዳቦና ውሃ ሰላም ምን ዋጋ አለው?» (ገጽ 122):: በተለያዩ ወጎኖች ሆነው ሲዋጉ ለወደቁ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ማስታወሻነት፣ ሀውልት ማቆምን ሊያካትት የሚችል ብሔራዊ የእርቅ ፕሮግራም አገሪቱ መጀመር አለባት በማለት ጉዳዩ እንድናጤነው ያሳስቡናል (ገጽ 323)::

በሚያስገርም መልኩ፣ ምናልባትም ቀዳሚ ያደርጋቸዋል፣ በ1977/78 በኢትዮጵያ የተገኘው የኦጋዴን ጦርነት ድል - ጦርነቱ በሽንፈት ቢደመደም ሊኖረው የሚችለው ውጤት በማመዛዘን - በጣም ኪሚወደሰው የአድዋ ድል የበለጠ ወሳኝ ሊሆን እንደሚችል ግምታቸውን ይሰነዝራሉ (ገጽ 216)::

ከሚያደንቃቸው የሕወሓት ወታደራዊ አዛዦች መካከለ ሁለት ጄኔራሎች ውስጥ ሀየሎም አርአያ አንዱ ናቸው (ሌላኛው የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ጄኔራል ሳሞራ ዬኑስ ናቸው):: እንደግለሰብ ስኬታማነታቸው የሀየሎም ወታደራዊ ዝና መግነን የሚደነቅ ሆኖ ሳለ፣ ከደራሲው ጋር ያካሄዱት ቃለ-ምልልስ የሕወሓትን ጠባብ ብሄርተኝነት ሀሰተኛ ገጽታ የሚያሳይ ነው:: ከእርሳቸው የደርግ ባለጋራ አዛዦች መካከል የሚያደንቋቸው እነማንን እንደሆነ ደሪሲው ሲጠይቃቸው፣ በኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት ውስጥ ያገለገሉ መጠሪያ ስማቸው የትግራይ የሚመስል ሁለት ጄኔራሎችን ብቻ ይጠቅሳሉ:: እነዚህም፣ ደራሲው ቢያንስ ስለጀግንነቱ የሚነግሩን ኮሎኔል ሰርቀ ብርሀነን እና በ437 ገጽ መጽሀፍ ወስጥ ምንምነገር ያልተጻፈላቸው ብርጋዲየር ጄኔራል አርአያ ዘርአይ ናቸው::

በዚህ ነው የአገር ፖለቲካ ብሔርን ማዕከል ባደረገ ፖለቲካ የሚበከለው:: ደራሲው የመከላከያ ሚኒስቴር መረጃዎችን በማገላበጣቸውና የቀደሞና የወቅቱ ወታደራዊ አዛዦችን ጨምሮ ከ500 የማያንሱ ሰዎችን ቃለ-መጠይቆች በማካሄዳቸው ባሞጋግሳቸውም፣ አንድ ጥያቄ በአእምሮዬ ደግሞ ደጋግሞ መመላለሱን ግን አልቀረም፤ የመንግስት ዶክመንቶችንና ወታደራዊ ሰዎችን የማግኘት እድል፣ እንደ ባህሩ ዘውዴ ወይም ተሻለ ጥበቡ ወይም ሹመት ሲሻኝ ላሉ የትግራይ ተወላጅ ያልሆኑ ኢትዮጵያዊ የታሪክ ተመራማሪዎች ሊሰጥ ይችል ነበር ወይ? ምላሹ የፈለገ ይሁን፣ ገብሩ ግን አጋጣሚውን በአግባቡ ተጠቅመውበታል::

ለደራሲው ምስጋና ይሁንና፣ የ1970ዎቹን በአክራሪ ወጣቶች ላይ የተፈፀመውን ጨፍጨፋ ሲዳስሱ፣ የደርግ ርዕዮተ-ዓለም አቀንቃኞች በመዝገበ ቃላት ያካተቱትን «ነጭ ሽብር» የሚለውን የፈጠራ ስያሜ ከመጠቀም ተቆጥበዋል:: ኢሕአፓ ጠንካራ የመልሶ ማጥቃት እርምጃ ለማድረግ የሚያስችለው፣ ከመንግስት ጋርም ሆነ ከደርግ ኃይል ጋር የተመጣጠነ ጉልበት አልነበረውም:: የወሰደው እርምጃ በደርግ በተሰነዘረበት መጠነ ሰፊ ውርጅብኝ ወዲያው ስብርብሩ የወጣ የተገደበ መከላከል ነበር (ተመሳሳይ ትንታኔ በሌላ እውቅ የታሪክ ምሁር - ተሻለ ጥበቡ - በተጨማሪ ተጽፏል፤ *«Modernity, Eurocentrism, and Radical Politics in Ethiopia, 1961-19910»*ገጽ 356 ይመለከቷል)::

ገብሩ የሕወሓትና ኢሕአፓ አለመግባባቶችንና በኋላም በትግራይ የተካሄደውን ጦርነት (ገጾች 87-88) በቃኙበት ሀተታቸው፣ ስህተት ላለመፈጸም ብርቱ ጥንቃቄ ያደርጋሉ:: ደራሲው «አባይ ኢትዮጵያ» የሚለውን ሕወሓት በኢሕአፓ ላይ የሰነዘረውን የነቀፌታ መግለጫ ስያሜን ሊጠቅሱ ያቻላቸው ነበር:: እና በተጨማሪም፣ የኢሕአፓ ደጋፊ ትግሬዎች፣ «ኮራኩር አማራ» (የአማራ ቡችሎች) ተብለው ይጠሩበት የነበረውን ስድብ መቋቋማቸውን ሊጠቅሱ ይችሉ ነበር:: በጠባብ ክልላዊ ብሔርተኝነት ሲቃጠል የነበውና በፖለቲካ እይታው ኢሕአፓን የመኖሩ ስጋት አድርጎ የወሰደውና በመጨረሻ አጠላይ ጦርነት በድርጅቱ ላይ ከማወጁ አስቀድሞ፣ እንደገበሬ ማሕበራት ባሉ የኢሕአፓ ሕዝባዊ ድርጅቶች ላይ ተደጋጋሚ የትንኮሳ እርምጃዎች እስከመወሰድ ድረስ የሄደው ሕወሓት ይህ ነበር:: እና ካለእፍረት፣ ጡረተኛው የሕወሓት ሜጀር ጀነራል ፃድቃን፣ የገብሩን መጽሐፍ በዳሰሱበት ጽሑፋቸው፣ ኢሕአፓ ከትግራይ ለመወጣት የተገደደው፣ በጉሎማክዳና ኢሮብ ሕዝቦች ሕዝበ-ውሳኔ ምክንያት መሆኑን በመጥቀስ በፈጠራ ወሬ ይጠመዳሉ:: ሰፊው የትግራይ ሕዝብና ምሁራን ጠባብ ብሔርተኝነቱንና የመገንጠል እሳቤውን ማቀንቀን የሙጥኝ ማለቱን ውድቅ ባደረጉበት ወቅት፣ ሕወሓት ተስፋ ወደመቁረጥና ወደጦርነት እንዲገባ ተገዶ ነበር:: ለሁለት አስርት ዓመታት ያህል አገሪቱን እየበከላት ያለው የሚታይና የቀጠለው የሕወሓት ጠባብ ብሄርተኝነትን ከመመልከት ሌላ ምን አይነት ማረጋገጫ ለኢሕአፓ ሊቀርብ ይችላል:: ሌሎች ወደ ምዕራቡ ሲሸሹ በትግሉ የፀናው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄን (ኢሕዴን)

ከልክ ባለፈ ጻድቃን ያሞጋግሳሉ:: ጻድቃን ኢሕዴንን በአዎንታዊ ገጽታው ማስቀመጣቸው እምብዛም የሚያስደምም አይደለም:: ሕወሓት የኢትዮጵያዊነት አቀንቃኝነት ኃይል አድርጎ ካባ እንዲለብስ ያስቻለ መለስተኛ ወታደራዊ ቡድን በመሆኑ አዲስ አበባ በገባ ወዲያው፣ ማንነቱንና ስያሜውን በመጣል ወደ«አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ» ለውጥ:: ያ በትግል ሜዳ ላዳረገው አስተዋፅኦው የሚበቃው ነው::

በተመሳሳይ ደራሲው፣ የኤርትራ ጥያቄን በተመለከተ ኢሕአፓና ሕወሓት የነበራቸውን አቋም በንጽጽሮሻዊ ትንታኔ ማስቀመጥ ያስቻላቸው ነበር:: ምንም እንኳን ሁለቱ ደርጅቶች በኤርትራውያን የመገንጠል መብት የሚስማሙ ቢሆኑም፣ ለሕወሓት ያ አቋም የሚቆመው ከኢትዮ-ኤርትራ ግንኙነት ጋር የሚያያዘው የቅኝ አገዛዝ መከራከሪያ ሲሆን ለኢሕአፓ ደግሞ የኤርትራ ጥያቄ በሰፊው ***ብሔሪዊ ጥያቆ*** ላይ የተመሰረተ ነበር:: እና መገንጠል ብቸኛውና በስፋት ተቀባይነት የነበረው አማራጭ ያልነበረ ሊሆን ይችላል:: በቅኝ አገዛዝ ምልከታው መሰረት፣ ጻድቃን እንደሚያምኑት፣ ሕወሓት ኤርትራን ለመደገፍ 5 ሺህ ተዋጊዎችን እንደላከና ይህም ተግባሩ ሕወሓት ከደርግ ጋር ባካሄደው የሽሬ ጦርነት ከኤርትራውያን በበኩሉ ድጋፍ ተደርጎለታል::

ታሪካዊውን መዝገብ በቀጥታ ለማስቀመጥ፣ ከሕወሓት ጋር የነበረውን ችግር ለመፍታት ኢሕአፓ ሶስት ሀሳቦቹን አቅርቦ ነበር:- 1ኛ፣ ሌሎች አካላትም አባላት ሊሆኑ በሚችሉበት ጥምረት በአንድነት በአንድ ግንባር መስራት፤ 2ኛ፣ ሙሉ ውህደት እና 3ኛ ካለምንም ትንኮሳ የየራሳቸውን የተለያዩ ዘመቻዎች በማክበር ለየድርጅቶቻቸው «የእከክልኝ ልክክህ» ፖሊሲ መከተል:: ሆኖም የሕወሓት ያልተቋረጠ ጥያቄ የነበረው ኢሕአፓ ከትግራይ ለቆ እንዲወጣ ያነሳ የነበረው ነው:: በሚያስገርም መልኩ፣ አሁን ድረስ ኢሕአፓ የአማራ መሰረት ያለው ፓርቲ አድርገው የሚወስዱ አሉ (ለምሳሌ ጃዋር መሀመድ በኢትዮሚዲያ ከመሳይ ከበደ ጋር ያደረጉትን ምልልስ በመመልከት ያላቸውን የኢሕአፓ ገጽታ መመልከት ይቻላል):: ወጣቶችንና ብዙ ኢትዮጵያውያንን ያሰባሰበውን ፓርቲ እንዲያ ብሎ መውሰድ ቅንነት የጎደለው ነው::

ከሌሎች አብዮታዊ መሪዎች ጋር የአቶ መለስንና የአቶ ኢሳይያስን የግል ጸባዮች በማነፃፀር፣ ሁለቱም የጊኒ ቢሳው ማርክሲስት መሪና የወጣትነት እድሜው በነፍስ ገዳይ የተቀጨው አሚልካር ካብራል ምጥቁነት ወይም ውስብስብነት እንዳልነበራቸው እና እንደማይደርሱበትም ደራሲው ይነግሩናል:: ገብሩ ሲነግሩን አሚልካር ካብራል ብልሀት የተሞላበት የነፃነት ንድፈ ኃሳብ ያመነጨና ምናልባት የፍሪካ የመጀመሪያው አብዮታዊ አሳቢ መሆናቸውን ነው (ገጽ 102)::

ፕ/ር ገብሩ፣ ሊተማመኑባቸው በሚችሉ መረጃዎች ላይ በመመስረት ድንቅ መፅሐፍ ጽፈዋል:: ተዋጊዎች የተጠቀሚቸው የጦር መሳሪያዎች ዓይነትና ብዛት፣ የዘመቻ ኃይሎች፣ ክህደቶች፣ የጦርነት ተጠቂዎችንና ወጪዎችን በተመለከተ ከመጽሐፉ አስፈላጊ መረጃዎችን ማግኘት ይቻላል:: ለትክክለኛ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ በኒኳራን፣

ሞዛምቢክ፣ ኬንያ፣ ዩጋንዳ፣ ሩዋንዳ፣ አልጄሪያ፣ ማሌዢያ እና ጓቴማላ የተደረጉ የተለያዩ የሽምቅ ውጊያ ንቅናቄዎችን በመጽሐፋቸው አካተዋል፡፡ በተደጋጋሚ የኢትዮጵያን አብዮት ከኢራን አብዮት፣ የኢትዮ-ሶማሊያን ጦርነት ደግሞ በ1980 ከተጀመረው የ8 ዓመታት የኢራን-ኢራቅ ጦርነት ጋር ያነፃፅሩታል፡፡

ፕ/ር ገብሩ በዚህ መጽሐፋቸው ለኢትዮጵያ ለፖለቲካና ታሪካዊ ምርምርና ጥናት ወሳኝ አስተዋጽዖ አድርገዋል፡፡ እናም ስለአገራችን የቅርብ ጊዜ ፖለቲካዊና ወታደራዊ መረጃ ለማግኘት ፍላጎቱ ያለው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ይህንን መጽሐፍ ሊኖረውና ሊያነበው የሚገባ ነው እላለሁ፡፡

## Motivation

# መወደድ ሲኖር ...

**በባንቺወሰን ወልደየሱስ**

ያስታውቃል፡፡ ተወዶ የሚሰራ ነገርና ሳይወደድ የሚሰራ ነገር አዎ! ውጤቱ ያስታውቃል፡፡ ከጀርባ ከፍተኛ ፍቅር እንዳለ እና እንደሌለ ማንኛውም ነገር ላይ ወዲያው ምናልባት ማወቅ ባይቻልም የዚያን ነገር ውጤት በማየት ግን ማወቅ ይቻላል፡፡ ማንኛ ውንም ነገር መውሰድ እንችላለን፡፡ ግዴታ መስራት ያለብን አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ መብላት፣ መጠጣትና የመሳሰሉት፡፡ እነዚህን እንተዋቸውና ከእነዚህ ውጪ የምናደርጋቸውን ነገሮች እስኪ እናስተውል፡፡ በቀን ውስጥ የምንሰራቸውን ስራዎች ሁሉ በምን ያህል ፍቅር ነው የምንሰራቸው? አንድ ሰው የተወሰኑ ስራዎች ላይ ለዘብተኛ ይሆንና የሚፈልገውን ወይም የሚወደውን ስራ ሲሰራ ግን ያለምንም ትዕዛዝ ወይም ያለማንም ጉትጎታ በራሱ ፈቃደኝነት በደስታ ስራውን ያከናውናል፡፡ ይሄ ታዲያ ምን ያሳየናል? ከእያንዳንዱ ስራ በስተጀርባ ፍቅር ቢኖር ምን ሊሆን እንደሚችል እስኪ እናስብ፡፡ እዚህ እዚያ እየሄድን የተሳኩ መልካም ነገሮችን እንፈልግ፡፡ ካገኘናቸውም በኋላ የስኬቱን ምክንያት እንፈልግ፡፡ በእርግጥ ለስኬት ብዙ ምክንያቶች ይኖራሉ፤ ግን ከነዚያ ውስጥ ያንን ነገር መውደድ ከላይ ነው የሚቀመጠው፡፡ ስራ ማንኛውም ዓይነት ስራ ሲሆን ተወዶ ሲሰራና ሳይወደድ ሲሰራ ብዙ ጊዜ ተቃራኒ የሆነ ውጤት ነው ያላቸው፡፡

ለምሳሌ አንድ አስተማሪን መውሰድ እንችላለን፡፡ ያለውን ለተማሪዎች አካፍሎ ስራውን ብቻ ሰርቶ መውጣት የሚፈልግ ሰው ከሚጠበቅበት በላይ የመሄድ እድል አይኖረውም፡፡ ይሄ አስተማሪ ስራውን እየሰራ አይደለም ማለት አይደለም፡፡ ስራውን እየሰራ ነው፤ ግን የታለ ስራው ከሚጠይቀው ወይም ከማይጠይቀው በላይ ተጨማሪ

ጥረት ያደረገው? የታል ተማሪዎቹ ያካፈላቸውን ነገር እንደተረዱት እና እንዳልተረዱት የጠየቀው? የታል የተለያዩ ዘዴዎችን ፈጥሮ ትምህርቱን ለተማሪዎቹ ተወዳጅ እንዲሆን የጣረው? የታል ማስተማር ከሚጠይቀው በላይ ምንም ዓይነት ነገር ይሁን ሲሞክር የታየው? ይህ አስተማሪ ስራውን እየሰራ ቢሆንም ከፍተኛ ፍቅር ቢኖረው ኖሮ ግን የተነሱት ጥያቄዎች አስቀደመው አይነሱም ነበር፡፡ ለዚያ ነው የሚወዱትን ስራ የሚሰሩ ሰዎች የበለጠ ስኬታማ የሚሆኑት፡፡ በተሰማሩበት ማንኛውም የስራ ዘርፍ ላይ ችግሮችን ተቋቁመው ሁሌም ቢሆን ውጤታማ ለመሆን የሚጥሩት፡፡ ከጀርባ የሚገፋ ብዙ ፍቅር ከሌለ ግን እንደ ስራ ወይም መስራት እንዳለበት ስራ ብቻ ነው የሚቆጠረው፡፡ ማንኛ ውም ስራ አሁንም  አሁንም ቢሆን አንድ ስራ መሰራቱ መልካም ነው፡፡ እንደ ተወዳጅ ስራ መሰራቱ ግን እጅግ በጣም መልካም ነው፡፡ ለእኛ ተወዳጅ ከሆነ ነው ጋር ያለን ግንኙነት እንዴት ነው? ከሌሎች ሰዎች ጋር ካለን ግንኙነት ጋር እኩል ነውን? ይህን የምንወደውን ከሌሎች አስበልጠን አናደምጠውምን?

ብዙ ጊዜስ ከእሱ ወይም ከእሷ ግን አናሳልፍምን? ግነኙቶችን ችግር ካጋጠመው ለማስተካከል ሌላ ጊዜ የማናደርገውን አናደርግምን? ሌላ ሰው ቢጠይቀን የማናደርገው ይሄ የምንወደው ሰው ውለታ ቢጠይቀን ግን አናደርግምን? እነዚህን እና የመሳሰሉትን ነገሮች የምናደርገው ሌላ ምስጢር ኖሮ ሳይሆን ያን ሰው ስለምንወድ ነው፡፡ ስለምንወድም ከሚጠበቅብን በላይ እንኄዳለን፡፡ ይህ እንደዚህ ሆኖ ሳለ ታዲያ በስራ ላይ የተለየ ነገር ለምን ይኖራል? አይኖርም፡፡ ማንኛውም ስራ ይሁን ከጀርባው ፍቅር ካለ ልክ እንደምንወደው ጓደኞችን ነው የምናየው፣ ስራውን መስራት ስላለብን ብቻ ሳይሆን የምንሰራው ስለምንወደው ጭምር ነው፣ እዚህ ስራ ላይ ችግሮች ሲያጋጥሙን የተለያዩ ጉድጓዶችን ለመቆፈር የበለጠ ፈቃደኞች ነን፣ ይኸም ብቻ ሳይሆን እኛው ራሳችን ከስራው በፊት ቀደመን እንገኛለን፣ የመሳሰሉት፡፡

## መውደድ ሲኖር...

መውደድ ሲኖር በቅድሚያ ሁሉ ነገር ተራውን ጠብቆ ይከተላል፡፡ ስራችንን ካልወደድነው ያለንን ኃይል ሁሉ ልንሰጠው አይቻለንም፡፡ ችግሮችን ተጋፍጠን አሸናፊዎች ልንሆን አንችልም፡፡ ከየት አምጥተን ጉልበት? ከጀርባ ሆኖ ትልቅ ድጋፍ የሚሰጠን ለማንኛውም ነገር ያለን ከውስጣችን የመነጨ መውደድ ነው፡፡ ይህንን ለማረጋገጥ ሩቅ መሄድ አይጠበቅብንም፡ አጠገባችን የሚገኙትን ነገሮች ከማየትም አልፈን ማተኮር እንጂ፡፡ በከፍተኛ ፍቅር ያደጉ ልጆች፣ በከፍተኛ ፍቅር የተሰራ ማንኛ ውም ስራ፣ በከፍተኛ ፍቅር የተጠና ማንኛውም ጥናት፣ ወዘተ፡፡ በአጭሩ በፍቅር የሚደረግ ማንኛውም ነገር ሁሉ ውጤቱ ያማረ ብቻ ሳይሆን እጅግ በጣም ያማረና መልካም ምሳሌም የሚሆን ጭምር ነው፡፡ ስለዚህ ማንኛውም ነገር ላይ ልንወደው የምንችል ነገር እንፈልግል፡፡ ልንጠላቸው የምንችላቸውን ነገሮች ከምንፈልግ ይልቅ

ተቃራኒውን ብንፈልግ ውጤቱ አስደሳች ነው የሚሆነው። የበለጠ የምንወዳቸውን ስራዎች በበለጠ ፍቅር እንስራቸው። መስራት ያለብንን ስራዎች ደግሞ እነሱ ውስጥ ልንወድ የምንችላቸውን ነገሮች በመፈለግ እና እነሱን ምክንያት በማድረግ እንንቀሳቀስ። ትንሽም ይሁን ትልቅ ፍቅር እና መውደድ ያለበት ወይም የተጨመረበት ማንኛውም ነገር ስኬታማ መሆኑ የማይቀር ነው።